ሴተኛ አዳሪነት እና የሰብኣዊነት ጥያቄ በሶስት ልብ-ወለዶች ውስጥ

በ
* አያሌው አስፋው

የጥናቱ አማካሪ
ዶክተር ዮናስ አድማሱ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍለትምህርት
የድኅረ-ምረቃ መርሐ ግብር

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ሰኔ 1999 ዓ.ም.

ሴተኛ አዳሪነት እና የሰብኣዊነት ጥያቄ በሶስት ልብ-ወለዶች ውስጥ

በ
አያሌው አስፋው

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍለትምህርት
የድኅረ-ምረቃ መርሐ ግብር

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ዮናስ አድማሱ
አማካሪ

Women Admasu
ፊርማ

ዘርሁን ገብረሕይወ
የውስጥ ፈታኝ

ፊርማ

ጋቻቸው ሣህለማርያም
የውጭ ፈታኝ

Getachew S.
ፊርማ

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

ምሥጋና

ውድ ጊዜአቸውን ሰውተው፣ ደክመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይሉ በትዕግሥት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በተደጋጋሚ ጽሑፌን በማረምና በማስተካል ለረዱኝ አማካሪዬ ለዶክተር ዮናስ አድማሱ ምስጋናዬ ጥልቅ ነው።

መዝናናት እያማራት፣ ልጆቻችንን በመንከባከብ ብቻ በመታቀብ፣ እኔ እንዳልቸገር እራሷን ሰውታ ከጐኔ በመቆም የሞራል ድጋፏ፣ የሀሳብ እና የጉልበት እገዛዋ ለአንድም ቀን ሳይለየኝ ለዚህ ደረጃ ያበቃችኝ ውድ ባለቤቱ አሰገደች ንጉሤ የምንጊዜም ባለውለታዬ ነች። የልጆቼም የሳባ፣ የኤደን እና የዳንኤል ትዕግሥት መቼም መቼም ከአእምሮዬ አይጠፋም። ትዕግሥታቸው ለሥራዬ ብርታትን ስለሰጠኝ ሳላመሰግናቸው አላልፍም።

ይህንንም ምርምራዊ ጽሑፌን ሳዘጋጅም ሆነ ከዚያ በፊት የማቴሪያል ድጋፍና ምክሩ፣ በርታ አይዞህ ባይነቱ፣ ያልተሰየኝ አብሮ አደግ ጓደኛዬ ቢሆነኝ አያሌውን ሳመሰግነው ጥልቅ በሆነ ስሜት ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

አጠቃሎ

ይህ ጥናት የሴተኛ አዳሪነት እና የሰብኣዊነት ጥያቄ በሶስት ልቦለዶች ውስጥ በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። ልቦለዶቹም ሴተኛ አዳሪ፣ ሴቱም አይነጋልኝ እና መጎልየ መጎልይ ዘካዛንችስ የተሰኙት ናቸው። በነዚህ የስነጽሑፍ ሥራዎች መነሻነት የሴተኛ አዳሪዎችን የሰብኣዊነት መንጠፍ ሁነት እና ሁኔታ (facts and conditions) ሥራዎቹን አንብቦ ትንታኔ ለመስጠት አላማ አድርጐ የተነሳ ነው።

ጥናቱ ሶስት ምዕራፎች አሉት። የመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ መንስኤ ነገር፣ ዓላማ፣ የአጠናን ዘዴ እና የጥናቱ አደረጃጀት የተገለጸበትና የተብራራበት ነው። ሁለተኛው ምዕራፍ ክለሳ ድርሳን ሲሆን የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት፣ ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝትና በስሩ የሴተኛ አዳሪነት ታሪካዊ ዳራና የሴተኛ አዳሪነት ትርጉም የታየበት ነው። ሶስተኛው ምዕራፍ የጥናቱን ሰፊውን አካል የያዘው ነው። ይኼውም የጥናቱ ትንታኔ የሴተኛአዳሪነት የሰብኣዊነት መንጠፍ ሁነት በሶስቱ ልቦለዶች ውስጥ ጠቋሚ ቃላት፣ ሀረጋትና ዓረፍተነገራት መሪነት ሰፊ የፍካሬያዊ ትንታኔ የተሰጠበት ክፍል ነው። ትንታኔ ሲደረግም ሶሱቱን መጽሐፎች በተናጠል ለየብቻ እንደየአስፈላጊነቱ ደግሞ በማዳበል የታየበት ነው። በዚህ ምዕራፍ ሶስቱን ልቦለዶች ሲተነተን አንድ ዓይነት የሆነ የአተናተን ስልት አልተከተልኩም። የሴተኛ አዳሪነት የሰብኣዊነት መንጠፍ (Dehumanization) መጠን እና ልክ እንደየልቦለዶቹ ለየቅል ነው። ያቀራረብ ስልትና ቃናቸውም ይለያያል። በመሆኑም የትንታኔ አሰጣጤም ተለያይቷል። ምንም እንኳ የትንታኔው አሰጣጥ ቢለያይም ቅሉ አጠቃላይ ሁነቱ ግን በሁለቱ ልቦለዳች ላይ የተሠራውን የሚያጠናክር ነው። የመጨረሻው ማጠቃለያ ሲሆን የጠቅላላ የጥናቱ ጨመቅ ምን እንደሆነ የተገለጸበትና የሥራውን ጠቅላላ ሂደት ጠቅለል ተደርጐ የተሰተረበት ክፍል ነው።

ማውጫ

አርዕስት ገጽ

ምስጋና.....i

አጠቃሎ.....ii

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1 የጥናቱ መንስኤ ነገር.....1

1.2 የጥናቱ ዓላማ.....1

1.3 የጥናቱ ገደብ.....2

1.4 የአጠናን ዘዴ.....2

1.5 የጥናቱ አደረጃጀት.....3

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳን.....4

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት.....4

2.2 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት.....18

2.2.1 የሴተኛ አዳሪነት ታሪካዊ ዳራ.....18

2.2.2 ሴተኛ አዳሪነት ምንድን ነው?.....22

ምዕራፍ ሶስት

የሴተኛ አዳሪ የሰብኣዊነት መንጠፍ.....29

መግቢያ.....29

3.1 ሴተኛ አዳሪ.....31

3.2 ሌቱም አይነጋልኝ.....50

3.3 መነልየ መነልይ ዘካዛንችስ.....67

3.3.1 መግቢያ.....67

3.3.2 ትንታኔ.....69

3.3.3 ፍካሬ.....73
3.3.3.1 አሀድ አንድ (ምዕራፍ አንድ "ጀምበር ስታዘቀዝቅ").....73
3.3.3.2 አሀድ ሁለት (ምዕራፍ አንድ፣ "... ድርሳነ ካዛንችስ
መልክዓ ወሲብ ...! ወይስ ያመንዝራ ጎራ?).....85

ማጠቃለያ.....97
ማጣቀሻ ጽሑፎች.....100

ምዕራፍ አንድ

1. መግቢያ

1.1 የጥናቱ መንስኤ ነገር

ለጥናቱ የተመረጡት ሦስት ልቦለዶች ናቸው። እነዚህ ልቦለዶች በአብዛኛው የሴተኛ አዳሪን ሕይወት የሚዳስሱ ናቸው። ያነሱዋቸው የሴተኛ አዳሪ ገፅታዎች ከምናውቃቸው ባህላዊ አመለካከቶችና አስተሳሰቦች አንፃር በእጅጉ የተለዩ (በተለይም መነልየ መነልይ ዘካዛንችስ)፥ የይዘት አቀራረብ ይዘው አገኘኋቸው። በተጨማሪም ባህሉ ከፈጠራቸው አስቸጋሪና አሰቃቂ ሁኔታዎች ለማምለጥ በልቦለዶቹ የተቀረጹት ሴተኛ አዳሪዎች የሚያደርጉትን መፍጨርጨር የወንዱ "ተሸራሚጭ" የሚያደርስባቸው ሰብአዊነት የጐደለው ተጽእኖ ልዩ ስሜት ፈጠረብኝ። ወንዱ ውስጥ ውስጡን ባህሉን ተቃውሞ፥ የማህበረሰቡን ኋላቀር አመለካከት ጠልቶ እሱ የጠላውን ባህላዊ ተጫኝነት፥ የሚወጣው፥ በድፍረት በመጋፈጥ ሳይሆን፥ በፈረደባቸው የቡና ቤት "ሴቶች" ላይ በሚያደርገው/በሚያደርሰው ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ነው። የታፈነ አመሉን፣የተገደበ አስተሳሰቡንና የታመቀ ስሜቱን የሚያወጣው መጠጥ ቀምሶ፥ የውስጥ የተዳፈነ አመሉን በሴተኛ አዳሪዎች ላይ ያሳያል። ባህሉ ያገደውን "አታድርግ" የሚለውን "ባህላዊ ገደብ" በመጣስ በሴቶቹ ላይ "እልሁን" ይወጣል። ይህ "የእልህ መውጫ" አካኋኑ፥ ይበልጡኑ ድርሰቶቹን እንድመረምር ገፋፋኝ።

1.2 የጥናቱ አላማ

ይህ ጥናት፥ በሦስቱ የስነጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ፥ የሴተኛ አዳሪን የሰብአዊነት መንጠፍ ሁኔታና ሁነት እንዴት እንደተገለጸ፥ ጠቋሚ ቃሎችን፣ ሀረጐችን ዓረፍተ ነገሮችን፥ በፍካሬ በማምጣት ማሳየት ነው። ይህ ዋነኛ ዓላማው ሲሆን፥ የሴተኛ አዳሪን የስነልቡና ስብራት፣ የማህበረሰባዊ የአመለካከት መድሎና መገለል ያስከተለባቸውን የመንፈስ ስብራት፣ ያስከተለባቸውን የባይተዋርነት ስሜት ከባህሉና ከልማዳዊ አመለካከት አንፃር፥ ከጽሑፎቹ /texts/ እንደዋዛ፥ ጣል በተደረጉ አባባሎች አማካይነት በአንድምታ ትርጉም በመተርጐም በሰበካው የተነገሩትን፥ "በፈርሱ" ገልብጦ በማየት የልብ ወለድ የአነባበብ ብሂላችንንም፥ ምን መምሰል እንዳለበት ለማሳየት ነው። ከዚህም በተጨማሪ፥ በባህላችን

ያልተለመዱ (አሁን ግን እየታዩ ያሉ)፥ ድርጊቶች በብርሃን ታምቀው በጨለማ ሲፈነዱ በመታየታቸው፥ የማህበረሰቡን ማህበራዊ ህመም፥ በስነጽሑፎቹ እማኝነት አይቶ ለማሳየት ዓላማ አድርጐ የተነሳ ጥናት ነው።

1.3 የጥናቱ ገደብ

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በደራሲ ነጋሽ ገ/ማርያም፥ እናነ አገሩናፍር በሚል የብዕር ስም የሚታወቀው ሴተኛ አዳሪ፣ በደራሲ ስብሃት ገ/እግዚአብሔር የተደረሰው ሴቱም አይነጋልኝ እና በተድባበ ጥላሁን በተዛፈው መነልየ መነልይ ዘካዛንችስ፥ ላይ ነው። በጥናቱ፥ ድርሰቶቹ የሚያነሷቸው የሴተኛ አዳሪ የሰብአዊነት መንጠፍና የባህላዊ አመለካከት ጸናናነት፣ የባህላዊ እሴቶች ህመምና ችግር ተሰይተው ይተነተናሉ። በሦስቱ ድርሰቶች ውስጥ ከሚገኙ ሴተኛ አዳሪ ገጸባህርያት ከማህበረሰቡ እና ከወንድ "ተሸራሚጮች" ጋር በመጋጨት የሚደርስባቸውን የሰብአዊነት መንጠፍ ከስነልቡና አንፃር በማጐዳኘት ለማየት ይሞክራል። የድርሰቶቹን ቅርፅም ሆነ ባህርይ ከምመለከታቸው የሰብአዊነት መንጠፍ ይዘት ትንተና ጋር ከሚኖራቸው ተያያዥነት አንፃር ከመነሳታቸው በቀር ነገሬ ተብለው አይታዩም።

1.4. የአጠናን ዘዴ

የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ አካሄድ እንደሚከተለው ነው። በመጀመሪያ ደረጃ አጥኚው በሴተኛ አዳሪነት ዙሪያ የተፃፉትን ልቦለዶች በማንበብ፥ በቀጥታ ከሴተኛ አዳሪነት ሕይወት ጋር ግንኙት ያላቸውን ሦስት ልቦለዶች በመምረጥ ወስኗል። ይህንንም ሲያደርግ በአበይት ይዘትነት እንደ አንድ የማህበረሰቡ ክፍል ሁሉ፥ በሴተኛ አዳሪነት ሕይወት ዙሪያ የተደረሱት ድርሰቶች የሚያስተላልፉትን መልዕክት፥ ለመረዳት ደጋግሞ በማንበብ የሚያጠነጥኑትን ማህበራዊ ጉዳይ/እውነታ/፥ ለመለየት ጥረት አድርጓል። በድርሰቶቹ ውስጥ የተገለፀውን እውነታ በቤተመጻህፍት ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች ተዛማጅ ርዕሰ ጉዳዮች ጋር በማገናዘብ እውነታውን ለማረጋገጥ የተለያዩ መጻሕፍትን የጥናት ወረቀቶችን፣ መጽሄቶችን፣ ኢንሳይክሎፒዳዎችን፣ ወዘተ አንብቧል። ልቦለዶቹ የሚያስተላልፉትን ማህበረሰባዊ እውነታ በዋቢነት በማቅረብ ከልዩ ልዩ መረጃዎች ጋር በማመሳከር ሀነቶቹንና ሁኔታዎቹን /facts

& conditions/ ይፋ ለማውጣት ሞክሯል። ትኩረቱ፥ በተመረጡት ሦስት የስነጽሑፍ ሥራዎች ላይ ሲሆን ጥናቱ ቀዳማይና ካልአይ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል።

1.5. የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ ሦስት ምዕራፎችን የያዘ ነው። የመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ ሲሆን በመግቢያው፥ የጥናቱ መንስኤ ነገር፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ገደብ እና የአጠናን ዘይዔው የተገለፀበት ነው። ይህ ክፍል ወደ ጥናቱ ዋና ጉዳይ የሚያዘልቀው የመግቢያው አካል ሲሆን፥ ሁለተኛው ምዕራፍ ክለሳ ድርሳን ነው። በክለሳ ድርሳኑ ውስጥ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት፣ ንድፈሀሳባዊ ቅኝት፣ የሴተኛ አዳሪ ታሪካዊዳራ እና ሴተኛ አዳሪነት ምንድንነው? የሚሉት የተቃኙበት ክፍል ሲሆን ወደ ምርምሩ ዋና አካል ለመግባት ተዛማጅ የሆኑ ጉዳዮች የተዳሰሰበት ነው። ሶስተኛው ምዕራፍ፥ የጥናቱ ዋና አካል ነው። ይህም ትንታኔ የተደረገበት፥ የሴተኛ አዳሪዎችን የስብአዊነት መንጠፍ፥ ከሶስቱ ስነጽሑፍ ሥራዎች መረጃዎችን፥ ጠቋሚ መሪ ቃሎችን፣ ሀረጎችን፣ እና ዐረፍተነገሮችን በመምዘዝ ትንታኔ የተሰጠበትና የትንታኔውን አቢይ ጉዳይ በፍካሬ አንጥሮ በማውጣት፥ አይቶ፥ ለማሳየት የተጣረበት የጥናቱ ሰፊው አካል ነው። ይህ ምዕራፍ ሦስት የጥናቱ ሰፊው አካልና የስነጽሑፎቹ የፍካሬ ትንታኔ አከል የሚታይበት ነው።

በመጨረሻ የትንታኔውን አጠቃላይ ጨመቅ/theme/፥ ሰብስብ ሰተር፥ ተደርጐ የቀረበበት የማጠቃለያው ክፍል ነው።

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳን

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ይህ ጥናት ካተኮረበት ዋና ዓላማ ጋር በቀጥታ በሚዛመዱ አርዕስት ላይ የተጠኑ ጥናቶች አላጋጠመኝም። ይሁን እንጂ በተዘዋዋሪ መንገድ ሊቀራረቡ የሚችሉ ጥናቶች ተሰርተዋል።

ከነዚህም ጥናቶች ውስጥ፦

1. የሪቻርድ ፓንክረስት "The History of Prostitution in Ethiopia" የሚለው አንዱ ነው። ጥናቱ በ "JOURNAL OF ETHIOPIAN STUDIES" በ "July 1974" በ "Vol. XII, No. 2" ላይ የታተመ ነው። አጥኚው የሴተኛ አዳሪነትን ታሪካዊ አመጣጥ እንደሚከተለው ገልፀውታል፣

> There are, however, indications that an institution related to prostitution existed at royal camps of the middle ages, at the seventeenth century city of Gondar, as well as later at commercial centers on the periphery of the empire, while the subsequent development of Addis Ababa and other late nineteenth or early twentieth century towns witnessed the emergence, as might be expected, of modern type prostitution.
>
> (Pankhurst, 1974, 159)

ከዚህ ጥቅስ ሶስት ሐሳቦችን ማርቀቅ ይቻላል። አንደኛ፣ በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በጐንደር ከተማ ከንጉሳውያን የካንፕ ኑሮ ጋር ተቋማዊ የሆነ የሴተኛ አዳሪነት መኖሩን አመላካች ሁኔታዎች መኖራቸው ይህም ከንጉሳውያን ተንቀሳቃሽ የካንፕ ኑሮ ጋር የተያያዘና ግንኙነት ያለው የሴተኛ አዳሪነት ምልክት የነበረ መሆኑን የሚጠቁመ ፍጮች እንዳሉ የተገለጸበት። ሁለተኛ፣ በወቅቱ በሀገሪቱ የንግድ ማዕከል ሆነው በሚያገለግሉ የድንበር ከተሞች መዛመቱን ሶስተኛ፣ ቀስ በቀስ የአዲስ አበባ መቆርቆርና በ19ኛው መቶ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ክፍለ ዘመን መገባደጃና በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ በነበሩ ከተሞች ላይ ብቅ ብቅ እያለ መምጣቱን የሚያረጋግጡ ምስክሮች ናቸው። ይህም ምናልባት ለዘመናዊ የሴተኛአዳሪነት ዓይነት ማቆጥቆጥ ምክንያት ሳይሆን እንዳማይቀር ይገመታል የሚሉ ሀሳቦችን ልንይዝ የሚያስችል አገላለፅ ከጥቅሱ ውስጥ ልንመዝ ያስችለናል።

ከዚህ በላይ የተረቀቁትን ሐሳቦች ጠለቅ ብለን ስናስተነትናቸው የሴተኛ አዳሪነት (prostitution) በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ ብቅ ያለው በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከንጉሣውያን የካንፕ ሕይወት ጋር ተያይዞ እንደሆነ ነው። በመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ነገሥታት ህዝባቸውን ያስተዳድሩት የነበሩት ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ አመቺ በሆነ ሥፍራ ድንኳን በመጣል ጊዜያዊ የሆነ ርዕሰ መዲና (capital city) በመመስረት በመንቀሳቀስ የሚኖሩ ነበሩ። ከንጉሣውያን ቤተሰቦች ጋር አገልጋዮች፣ አሽከሮችና የአገሪቱን ሉአላዊነት ከሚያስከብሩት ወታደሮች በተጨማሪ ሌሎች ተራ የማህበረሰቡ አባላት ተከትለው በመንቀሳቀስ ልዩ ልዩ የሆነ የሥራ ድርሻ የነበራቸው ሲሆን ከነዚህም ሰዎች መካከል ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው ሴተኛአዳሪዎች (Prostitutes) አብረው ይንቀሳቀሱ እንደነበር በ16ኛው ክፍለዘመን የነበረውን የፓርቹጋላዊ ቄስ Francesco Alvares ን ጠቅሰው ፓንክረስት አስፍረዋል። በማከልም "Prostitutes" የሚለው ቃል ምን እንደሚገልጽ በትክክል አለመተርጉመንም ይገልፃሉ። ከዚህም ጋር በማያያዝ Alvares በልብነድንግል ካንፕ ያየውን እንዲህ ሲሉ ገልፀዋል።

> Alvares records that at the camp of Emperor Lebna Dengel (1508-1540) he saw "the tents of the prostitutes, whom they call Amaritas," i.e. አማሪት, amarit, an Amharic word defined by the Italian Linguist Ignazio Guidi at the beginning of the twentieth century as a female minstrel or dancing girl. (page, 159)

ፓንክረስት ምንም እንኳ በመነሻቸው ላይ ሴተኛ አዳሪ (Prostitution) ሲሉ ምን ማለታቸው እንደሆነ ባይገልጹም የሴተኛ አዳሪን ታሪካዊ አመጣጥ ለመግለፅ ባቀረቡት ጽሁፍ የቃሉ ታሪካዊ እድገት ምን ይመስል እንደሆነ ለማሳየት የተለያዩ የውጭ ሰዎችን እና የአገር ውስጥ ደብተሮችን በመጥቀስ ለማሳየት ሞክረዋል። ከፍ ብየ በጠቀስኩት የመጀመሪያው ጥቅስ ውስጥ በኢትዮጵያ ሴተኛ አዳሪነት ተጀመረ ለማለት የሚያስችል ጠቋሚዎች (ምልክቶች) በ17ኛው መቶ ክፍለዘመን በጎንደር ከተማ እንደሆኑ ተጠቅሷል። በሌላ መልኩ

ያግሞ በ16ኛው መቶ ክፍለዘመን የነበረው ፖርቹጋላዊ ቄስ ቀላል የማይባሉ ሴተኛአዳሪዎች ከንጉሳውያን የካንፕ ሕይወት ጋር በተያያዘ መልኩ አብረው ይንቀሳቀሱ እንደነበር እና በልብነድንግል ዘመነ መንግሥት (1508-1540) "he saw" the tents of prostitutes whom they call Amaritas "i.e. አማሪት ..." የሚል አባባል እናገኛለን። የእነዚህም "አማሪት" ትርጉም ኢጣላያዊ የስነልሳን ሰው Ignazio Guidi በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ "a female minstrel or dancing girl" "ሴት ዘፋኞች" ወይም "ዳንሰኞች"[1] በማለት ሲተረጉመው ፖርቹጋላዊ ተንኛር ግን ትርጉሙን ይቃወማል። እነዚህ ሴቶች በርካታ ቁጥር ያላቸው ሀብታምና ጥሩ ጥሩ የሚለብሱ የካምፑ ሕይወት አካል የሆኑ ጊዜያቸውን ካንዱ ካንፕ ወደ ሌላው እያሉ የሚያሳልፉ ናቸው። ስለዚህ እንዴት ይህ ትርጉም ሊሰጣቸው ይችላል በማለት ትክክለኛነቱን ይጠይቃል። ከዚህ በመነሳትም ፓንክረስት ምን ያህል እነዚህን በዘመናዊ አስተሳሰብ "ሴተኛ አዳሪ" ብለን ልንቆጥራቸው እንችላለን የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል በማለት ይገልፃሉ። ከዚህ ላይ ፓንክረስት ራሳቸው እርስ በራሱ የተምታታ ሀሳብ ይዘው የሚንዙ ናቸው የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። ምክንያቱም ከመነሻቸው ሴተኛ አዳሪ በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በጐንደር ተጀመረ ካሉ በኋላ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደግሞ በልብነድንግል ዘመን የሴተኛ አዳሪዎች ድንኳን ለማየቱ ፖርቹጋላዊውን ቄስ "Alvares"ን ጠቅሰው ይፅፋሉ። በማስከተልም የቃሉን ትርጉም "አማሪት" እንዴት ዘመናዊ የሴተኛ አዳሪነት ትርጉም ልንሰጠው እንችላለን በማለትም ይጠይቃሉ። ከዚህ አባባል በመነሳት ፓንክረስት ሊፅፉ የፈለጉት "The History of Prostitution in Ethiopia" በሚለው ርዕስ የዘመናዊ ሴተኛ አዳሪነትን ታሪክ አመጣጥ ነው ወደሚል አመለካከት ያመራል። ይህን ለማለት ደግሞ በመነሻቸው የጽሁፋቸውን ዓላማ በግልፅ አላስቀመጡም። በሌላ በኩል የቃሉን ታሪካዊ እድገትና አመጣጥ ነው ለመፃፍ የፈለጉት እንዳይባል ስለዘመናዊ የሴተኛአዳሪነትን ጥያቄ ያነሳሉ። ከዚህ በመነሳት የፓንክረስት አቋም ግልጽ ያልሆነው ለማለት ይቻላል።

የፓንክረስት ጥናት የሚያመላክተው የሴተኛ አዳሪነት አጀማመር በኢትዮጵያ ምን ዓይነት ታሪካዊ ገዞ የተከተለ እንደሆነ ነው። በጥናታቸው ላይ እንዳስቀመጡትም ከሆነ ሴተኛ አዳሪነት ለመጀመሪያ ጊዜ (ዓይነቱና ሁኔታው ካሁኑ ጋር ባይመሳሰልም) የታየው በጥንታዊቷ የጎንደር ከተማ ለመሆኑ አስረግጠው ጽፈዋል። የፓንክረስትን ምርምር መነሻ

[1] የተጠቀሰው ቃል በዘመኑ ሴቶቹ (በተለይም የሰሜን ኢትዮጵያ ሴቶች) ዳንስ ሳይሆን የሚደንሱት እስክስታ መምታት፣ ባህላዊ የሆነ የጭፈራ ስልት ማከናወን እንደሆነ ይገመታል። ነገር ግን "ዳንሰኞች" በሚል የተተረጐመው የባዕዱን ቋንቋ ትርጉም በማለዘብ ለዛሬው አንባቢ ትውልድ ግልፅ እንዲሆን ታስቦ ነው።

አድርገን ስንመለከት ሴተኛ አዳሪነት በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቅ ያለው የዛሬ 500 ዓመት ገደማ ነው ወደሚል አስተያየት ያመራናል። ስለሆነም ዓይነቱ፣ መጠኑና ሁኔታው ከዛሬው የሴተኛ አዳሪነት "ሥራ" ጋር ቢለያይም የሴተኛ አዳሪነት "ተግባር" በሀገራችን እንግዳ አለመሆኑን ለመረዳት ይቻላል። ጥናታቸውም የሴተኛ አዳሪነትን አጀማመር፣ እድገትና ታሪካዊ ገዘ ላይ ያተኮረ በመሆኑ ከኔ ጥናት ጋር በዓላማ ይለያያል። የሳቸው ጥናት "The History of Prostitution in Ethiopia" የሚል ሆኖ የሴተኛ አዳሪነትን ጥንተ አጀማመር፣ ከዚያም በሀገሪቱ ልዩ ልዩ ግዛቶች ያሳየውን የመስፋፋት ሂደትና እድገት በማሳየቱ ላይ ያተኮረ ነው። ይህንንም ታሪካዊ እድገት ለማሳየት ማንጸሪያ አድርገው የተጠቀመውበት "Prostitution" ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል በወቅቱ የኢትዮጵያን ግዛት ለማስተዳደር ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀሱ አገሪቱን ይመሩ ከነበሩት ነገሥታት ተንቀሳቃሽ የካንፕ ሕይወት ጋር በጥብቅ ቁርኝነት ከነበራቸው "the tents of the prostitutes, whom they call Amaritas" i.e. አማሪት" (Page 159) ከሚባሉት ሴቶች ጋር ነው። በዚህ ቃል የተጀመረው ቀስ በቀስ እያደገ መምጣቱን የሚያሳይ ታሪካዊ ጥናት ነው ያደረጉት። የእኔ ጥናት ግን የሴተኛ አዳሪዎችን የሰብአዊነት መንጠፍ[2] ና የማህበረሰቡን ባህላዊ አመለካከት በተመረጡት ሶስት የስነጽሑፍ ሥራዎች መነሻነት ማሳየት ነው። በመሆኑም በዓላማ እንለያያለን። ምንም እንኳ ፓንክረስት ከመነሻቸው የጥናታቸውን ዓላማ በግልጽ ባያስቀምጡም የአጠናን ስልታቸውና የአፃፃፍ ሂደታቸው የሚገልጸው የሴተኛ አዳሪነትን (Prostitutions) ታሪክ በኢትዮጵያ ምን ዓይነት ሂደት እንዳሳየ የሚጠቁም ነው። ይህንንም የሴተኛ አዳሪነት አጀማመርና የእድገት ሂደት በጥሩ ሁኔታ ከግብ አድርሰዋል የሚል አስተያየት አለኝ።

2. የላቀች ድረሴ "The Social Economic Position of Women in Addis Ababa: The Case of Prostitution" የሚለው በ1978 እ.ኤ.አ. ለፒኤችዲ ዲዘርቴሽን የቀረበው ነው። ላቀች ሴተኛ አዳሪነትን ማተኮሪያ አድርጋ <u>በአዲስ አበባ</u> የሴቶች የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ኑሮ ይዞታ ምን እንደሚመስል ያሳየችበት ሥራ ነው። ላቀች ይህንን የሴተኛ አዳሪነትን ጉዳይ ሰፋ ባለው የአዲስ አበባን ሴቶች የማህበራዊ ኑሮና የኢኮኖሚ አቅም ይዞታ በሚመለከተው አጠቃላይ ርዕስ ውስጥ ነው። ትኩረቷ ኑሮዋቸውን ከሁለት ሊቆራኙ ከሚችሉ ገጽታዎች አንፃር ማየት ነው። ይኼውም ከማህበራዊ እና ከኢኮኖሚያዊ

---

[2] ይህን ሐረግ የወሰድኩት ዮናስ አድማሱ "ሀዲስ አለማየሁና የማህበራዊ ሂስ ሥልታቸው" በሚል ርዕስ በ1992 ዓ.ም. ከጻፉትና የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ መጽሔት ከታተመው ሥራ ላይ ነው።

አንባር ነው። ትኩረቷ ሴተኛ አዳሪነት ይሁን እንጂ ማንአሪያዋ "ሴቶች" ናቸው። ስታነባዕርም ሴቶች ወደ ሴተኛ አዳሪነት ሥራ የሚሠማሩት የተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች ሲደርስባቸው መሆኑን በመግለጽ ነው። እነዚህም ማህበራዊ ችግሮች ከባል ጋር መፋታት፣ ከቤተሰብ ጋር መጣላት፣ ከትምህርት መውደቅ ወዘተ. የመሳሰሉት ሲሆኑ እነዚህ ማህበራዊ ችግሮች ለምጣኔ ኃብታዊ ችግር የሚደርጓቸው ናቸው። ከዚህ ምጣኔ ኃብታዊ ችጋር ለመላቀቅ ለጊዜውም ቢሆን ክፍት የሥራ ቦታ የሚገኘው ሴተኛ አዳሪነት ስለሆነ ወደዚህ "ሥራ" ሰተት ብለው ይገባሉ። ስለሆነም የማህበራዊ ችግር በሴቷ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ለምጣኔኃብታዊ ችግር የሚዳርጋት በመሆኑ ወደ ሴተኛ አዳሪነት ሕይወት እንድትገባ ያደርጋታል። በዚህ መሠረት የማህበራዊ ችግሮች እና ምጣኔኃብታዊ ጥገኛነቶች ለሴተኛ አዳሪነት መፈጠር ምክንያት ሊሆኑ እንደቻሉ ትጠቅሳለች። የላቀች ጥናት "ሶሲዮሎጂያዊ" ላይ ያተኮረ ሲሆን የእኔ ስነጽሑፋዊ ላይ ያተኮረ ነው። ሁለቱ ጥናቶች የሚለያዩበትና የሚገናኙበት ነገር አላቸው። ሁለቱም ጥናቶች ትኩረት አድርገው የተነሱት ሴተኛ አዳሪነትን ነው። የላቀች ሴተኛ አዳሪዎችን ከማህበራዊ-ምጣኔኃብታዊ አንባር በመመልከት "ሥራውን" ለመስራት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚንቀሳቀሱበትን ቦታ ሁሉ ከሚከሰቱበት ሁኔታ አንባር ከፍላ ታሳያለች። ይህንን ስታደርግ ግን በማህበረሰቡ ዘንድ ሊደርስባቸው የሚችለውን ልዩ ልዩ የተዛባ አመለካከትና የመገለል ሁኔታ አላሳየችም። ትኩረቷ ስንት ዓይነት ሴተኛ አዳሪዎች አሉ? የሚል ዓይነት ነው። ይህም አከፋፈል የሴተኛ አዳሪዎችን ምጣኔኃብታዊ አቋምና አቅም ከግምት ባስገባ መልኩ ነው። ይህ አከፋፈል ከሴተኛ አዳሪዎችም መካከል የደረጃ ልዩነት ያለ መሆኑን አመላካች ነው። በመሆኑም እኔ ከማተኩርበት ጥናት አንባር የሴተኛ አዳሪዎች የሰብአዊነት መንጠፍ ደረጃ ያለው መሆኑን አመላካች በመሆኑ ከዚህ የደረጃ አመዳደቧ አንባር ልንጋራው የምንችለው ሁኔታ አለ። ሆኖም የእሷ ምጣኔኃብታዊ ሲሆን የእኔ ከማህበራዊ አመለካከት አንባር የተተኮረበት በመሆኑ አሁንም ልዩነቱ የጎላ ነው።

ላቀች የአዲስ አበባን የሴተኛ አዳሪነት ደረጃ ስታጠና ስድስት ዓይነት ሴተኛ አዳሪዎች እንዳሉ ጠቁማለች። እነሱም፦

1ኛ. በመንገድ እየተዘዋወሩ ደንበኛ የሚያገኙ

2ኛ. ትናንሽ ቤቶች ተከራይተው ደንበኞችን በመጠበቅ ከዚያ በሚያገኙት ብቻ የሚተዳደሩ

3ኛ በትላልቅ ወይም ትናንሽ ሆቴሎች ተቀጥረው ገላቸውን በመሸጥ የሚተዳደሩ።

4ኛ. ማታ ማታ በየዳንስ ቤቱ በመሄደና ከእንግዶች ጋር በመጫወት ከቀናቸው በዚያው የሚሄዱ

5ኛ. አነስተኛ መጠጥ ቤት ከፍተው የገመት ተግባር በመፈጸም ኑሮኣቸውን የሚደግፉ

6ኛ. ትላልቅ ቡና ቤቶች ከፍተው ሴቶችን በመቅጠር የሚያሰሩና እራሳቸውም በሚያደርጉት የገመት ተግባር ገቢ የሚያገኙ ናቸው።

ይህን ከላይ የተጠቀሰውን አከፋፈል ላቀች ስትከፍል መሠረት ያደረገችው የሴተኛ አዳሪዎችን ምጣኔኃብታዊ አቅም ግምት ውስጥ አስገብታ ነው። ይህን ለማለት የሚያስችለው ራሷ ከገለጸችው በተጨማሪ የደረጃዎቹን የአካፋፈል ቅደም ተከተል በመመልከት ብቻ ለማገንዘብ የሚያዳግት አይመስልም። የዚህ ዓይነት አከፋፈል እኔ በማጠናው ስነጽሑፍ "በመጎልየ መጎልይ ዘካዛንችስ" ከገጽ 74-92 ድረስ ተጠቅሶ ይገኛል። ሆኖም የሁለቱ አከፋፈል ከላይ እንደጠቀስኩት መሠረታዊ መነሻቸው ይለያያል። በአከፋፈሉ ዓይነትና መነሻ ይለያዩ እንጂ ሁለቱም የሴተኛ አዳሪዎችን "ሥራ" ለማከናወን የተለያዩ ደረጃዎችና ምጣኔኃብታዊ አቅሞች ላይ ልዩነት ያለ መሆኑን በማሳየት ረገድ ተመሳሳይ ያደርጋቸዋል። ሰፊው ልዩነታችን ግን የጥናታችን ዓላማና የአጠናን ዘዴያችን ላይ ነው።

3. በማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር "የገመት አዳሪነት ጠባይ፣ መነሻና ችግር በኢትዮጵያ አስር ከተሞች" የተደረገ የመስክ ጥናት 1968 ዓ.ም.፣ ንጉሴ ተፈራና አለማየሁ ወጋዩ፣ "ማህበራዊ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው"፣ መስከረም መጽሔት ቅጽ 3፣ ቁጥር 12፣ መጋቢት 1975 ዓ.ም.፣ እንዲሁም አልማዝ ደጀኔ፣ "ሴተኛ አዳሪ በኢትዮጵያ፣ እቱመላምቺ፣ 1967/68 ዓ.ም. በዚሁ በሴተኛ አዳሪነት ሕይወት ዙሪያ መጠነኛ ጥናቶች አካሂደዋል።

4. በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ድግሪ ተመራቂ ተማሪዎች ሴተኛ አዳሪነትን በተመለከተ የተወሰኑ የዲግሪ ማሙዋያ ጽሁፎች ሰርተዋል። ይሁን እንጂ ሁሉም ሥራዎች የሚጠቁሙት ፣ሴተኛ አዳሪነትን አስከፊ ሕይወት፣ ሴተኛ አዳሪዎች ከገጠር ከተማ ሊገቡ የቻሉበትን መንስኤ እና ሴተኛ አዳሪነትም እየተስፋፋ መምጣት ሊያስከትለው የሚችለውን እና እያስከተለ ያለውን ችግር በመጠቆም መፍትሔ ሊሆኑ ይችላሉ ያሉትን ከጥናታቸው ያገኙትን ሀሳብ ያመላከቱበት ብቻ ነው። በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለባችለር ዲግር ማሟያነት ከተዛፉት ጥቂት

ADDIS ABABA UNIVERSITY ALS LIBRARY

ሥራዎች በስተቀር ከላይ የተጠቀሱት የሌሎች ሥራዎች ትኩረት የመስክ ጥናት በማድረግ አገኘን ያሉትን ደረቅ እውነታ ያተቱበት ነው። ዲማያቹ ግን የሴተኛ አዳሪነትን ሕይወት እንደ ርዕስ ጉዳይ አድርገው በተዓፋ ልቦለዶች ላይ በመመርኮዝ ሴተኛ አዳሪ ገጸባህርያትን ወስደው አጠቃላይ ሰብእናቸውን ከማህበራዊና ከኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ጋር በማያያዝ ለመመልከት ችለዋል።

5. በአማርኛ ልቦለድ ላይ ከሴተኛ አዳሪነት ሕይወት ጋር ተያያዥነት ያለው ሥራ በ1976 ዓ.ም. በፀዳለ ዘውዴ "ገመና አዳሪነት በአርባና በሃምሣ አስርታመታት የአማርኛ ልቦለዶች" በሚል ርዕስ የቀረበው አንዱ ነው። የዚህ የጥናት ወረቀት አላማዎች ሶስት ናቸው። እነሱም የገመና አዳሪነትን ችግር ለመዋጋት ስነጽሑፍ ያበረከተው ድርሻ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ፣ ሁለተኛ በደራስያን ለችግሩ የተሰጠውን ትኩረት የቱን ያህል እንደሆነ ለመገመት፣ ሶስተኛ ከዚህ በመነሳት ለወደፊቱ በስነጽሑፍ መስክ ሊደረግ የሚገባውን የሥራ ድርሻ ለመጠቆም ነው፣ የሚሉ ናቸው። እነዚህን ሶስት ዓላማዎች ከስነጽሑፍ ተግባር አንፃር ስንመረምራቸው ምን ያህል ተቀባይነት አላቸው? የሚለውን በመጠየቅ የዓላማዎቹን ተገቢነት እንመርምር። ከላይ የተጠቀሱት ዓላማዎች በቀጥታ የሚመለከቱት የማህበራዊ ኢኮኖሚ የጥናት ጉዳይ እንጂ ስነጽሑፋዊ ጥናት አይደሉም። የአንድ ስነጽሑፍ አበይ ተግባር የማህበረሰቡን ሕይወታዊ እንቅስቃሴና በማህበረሰቡ ውስጥ የሚካሄደውን ሰዋዊ ተራክቦ (Personal interaction) ከብዙ በጥቂቱ ጨልፎ ማሳየት ነው። የደራሲውም ዓላማ ቢሆን የድርሰቱ መቼት አድርገው የወሰደውን አካባቢና ማህበረሰብ እንደተገነዘበውና እንደታዘበው መልሶ ለማህበረሰቡ ማሳየት ነው። የስነጽሑፉም ተግባር የሚሆነው እነ ቄሌክ እንደሚሉት "Its prime and chief function is fidelity to its own nature (page, 37)" ነው። ስለዚህ ፀዳለ ዓላማ ብላ ያስቀመጥቻቸውን ሐሳቦች ለመቀበል ያስቸግራል። በእኔ በኩል የአንድ ልቦለድ ዓላማ እነዚህን ይይዛል የሚል አቋም የለኝም። ምንም እንኳ የስነጽሑፍ ተግባር ወይም አላማ "የማስተማር ተግባር" ሊኖረው ይገባል የሚሉ ክፍሎች ቢኖሩም የስነጽሑፍ ዓላማ የማስተማር ብቻ ነው ብዬ ስለማላምን የፀዳለንም ዓላማዎች በበኩሌ አልቀበልም። አጥኝዋ በሶስተኛ ደረጃ ያስቀመጥችውን ዓላማ በሚገባ ስንመለከት "ከዚህ በመነሳት ለወደፊቱ በስነጽሑፍ መስክ ሊደረግ የሚገባውን የሥራ ድርሻ ለመጠቆም ነው" የሚለውን አንድ ደራሲ በማህበረሰቡ ውስጥ ሲኖር የታዘበውን፣ የታየውንና ስሜቱን በክፉም ይሁን በበጎ መልኩ የነካውን ጉዳይ በብዕሩ ቀርፆ መልሶ ለማህበረሰቡ ያሳያል ወይም ያቀርባል እንጂ በትዕዛዝ ርዕስ ተቀንብቦለት ቃላት

ተቆንኖለት ሊጽፍ አይችልም። የስነጽሑፍ አድባር ስትቀርበው ውስጡ ሲነካ ነው የሚጽፈው። ስለሆነም የአንድ ስነጽሑፍ የሥራ ድርሻ ይህን መምሰል ወይም ይህን መከተል አለበት ተብሎ የሥራ መርህግብር ሊወጣለት የሚችል አይመስለኝም። ደራሲውንም ሆነ ደራሲው የሚጽፍበትን ጥሬሀብት ከሌላ አካል በትዕዛዝ መልክ የሚተላለፍ ከላይ ወደታች የሚወርድ የትዕዛዝ እዝ የሚከተል የሕግ ድንጋጌ የለውም። ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የምርምር ሥራዋን ከግብ ለማድረስ የተነደፉት አላማዎች ራሳቸው ከስነጽሑፍ ተግባርና ባህርይ አኳያ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው ለማለት የሚያስችሉ አይደሉም።

የፀዳለ ጥናት አራት ክፍሎች ያሉት ነው። ይኼውም የዝሙት አዳሪነት መንስኤ፣ የዝሙት አዳሪነት ጠንቆች፣ የዝሙት አዳሪነትና የህብረተሰቡ ግምት እና ዝሙት አዳሪነትን ለመዋጋት የተደረጉ ሙከራዎች የሚሉ ናቸው። በነዚህ ክፍሎች አማካይነት የመረጠቻቸውን አራት ልቦለዶች መነሻ አድርጋ ጥናቷን ሠርታለች። ለዝሙት አዳሪነት መንስኤ ናቸው ያለቻቸው የጣሊያን ወደ ሀገራችን መግባትና የከተሞች መስፋፋት፣ ያለእድሜ መዳርና ትዳራቸውን ፈተው የኢኮኖሚ ችግር የሚገጥማቸው ሴቶች እና በልዩ ልዩ ምክንያት ከወላጆቻቸው ጋር የሚጣሉ ወጣት ሴቶች እንዲሁም በፈተና ዝቅተኛ ውጤት በማምጣት የሚወድቁ ሴት ተማሪዎች ሲሆኑ እነዚህ ምክንያቶች ለዝሙት አዳሪነት መንስኤ ናቸው። ስለዚህ ምንም ዓይነት ስልጠናና ወረት የማይጠይቀው ክፍት ሥራ ይኼው ስለሆነ ወደዚህ ተግባር ይሰማራሉ ትላለች። የዝሙት አዳሪነት ጠንቆች ያለቻቸውንም "ዝሙት አዳሪነት በኢኮኖሚ፣ በቤተሰብ አቋም፣ በጤናና በሞራል ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል (ገፅ፣ 6)።" በማለት ከገለፀች በኋላ በኢኮኖሚ በኩል ብንመለከት ራሳቸውን ችለው ቢኖሩም በምርት ተግባር ላይ ስለማይሰማሩ ምንም የሚያስገኙት ትርፍ የለም። ዝሙት አዳሪዎች በቅርፅ ካልሆነ በስተቀር በይዘት የዚህ ህብረተሰብ የባዘኔ ክፍል አባላት መሆናቸው የታወቀ ነው በማለት በባዘኔነት በመመደብ ምንም ፋይዳ ያለው ሥራ የማይሠሩ መሆናቸውን ዝቅ አድርጋ ትመለከታቸዋለች። በዝሙት አዳሪነት ምክንያት ትዳር ሊፋለስ ይችላል። የልጆችም አስተዳደግ የተዛባ ሊሆን ይችላል። ከዚህ ላይ ጉዳዩን ስናጤን ወደ ዝሙት አዳሪዎች ሚስት ያላቸው ወንዶች ስለሚሄዱና ስለሚቀብጡ ባልና ሚስት ይጣሉና ትዳራቸው ሊፈርስ ይችላል። ከነሱም የተወለዱት ልጆች ችግር ውስጥ ሊወድቁ ይችላሉ የሚል አስተያየትን የሚያመለክት ነው። ሀሳቡ እውነታ ያለው ነው። ነገር ግን ሌላ የሚያመላክተው ጥያቄ የሚያስነሳ አስተያየት አለ። ይኼውም ዝሙት አዳሪዎች

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ወደ ባለትዳሮቹ ወንዶች ቤት ሄደው ነው ይህንን ችግር ሊያመጡ የቻሉት ወይስ ባለትዳሮቹ ወንዶች ወደ ዝሙት አዳሪዎቹ ቤት ወይም የሥራ ቦታ ሄደው የሚለው ተጠየቃዊ (logic) ጥያቄ ይነሳል። ስለዚህ ለዝሙት አዳሪዎች መንስኤ ሊሆኑ የቻሉት ያው ከህብረተሰቡ ከመነጨ በሌላ በኩል ደግሞ ጠንቁ ተመልሶ ህብረተሰቡን ከጐዳ ዝሙት አዳሪዎች እና ዝሙት አዳሪነት መኮነን አለበት? ይህ ነው መጠየቅ ያለበት። ፀዳለ ይህን ያሰበችው አይመስልም። ይህ ጉዳይ በእኔ ሥራ ውስጥ በፍካሬ ነጥሮ የሚወጣ ነው። የማህበረሰቡን የተዛባ አመለካከት "ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮህ" ዓይነት መሆኑን ለማሳየት የሚጣርበት ሲሆን ከፀዳለ አሠራር ጋርም የሚለየን ይኼው የአሠራር ብሂል አንዱ ነው ለማለት ይቻላል።

"ዝሙት አዳሪነት በጤና በኩል የሚያስከትለው ዋናው ችግር የአባለዘር በሽታ ማሰራጫ መሆኑ ነው። በዚህ ሙያ የተሰማራችው ሴት ከብዙ ሰዎች ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት ስለምታደርግ ይህ በሽታ በቀላሉ ሊዛመት ይችላል። የእሷ በዚህ በሽታ መያዝ ደግሞ ብዙ ሰዎችን ሊበክል ይችላል። (ገፅ፣ 7)" በማለት ዝሙት አዳሪዋን የበሽታ አስተላላፊ ህዋስ እንደሆነች አድርጋ ትገልፃለች። ይህም ማህበረሰቡን ትበክላለች በማለት ታሠርፃለች። ይህ ነው የሁለታችንን የጥናት ሂደት ልዩነት ይበልጥ የሚያጐላው። ፀዳለ አቋም ይዛ ዝሙት አዳሪነት በጤና በኩል በተለይም የአባለዘር በሽታ ማሰራጫ እንደሆነ አድርጋ ስታስረግጥ መነሻው ከየት እንደሆነ የዘነጋችው ይመስላል። ለምን ቢባል? "በዚህ ሙያ የተሰማራችው ሴት ከብዙ ሰዎች ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት ስለምታደርግ ..." የሚለውን መሪ ቃል ሆነ ብላ ትታዋለች አንድም ከሴቷ ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት የሚፈጽሙት ሰዎች ("ሰዎች" የተባሉት መቼም ወንዶች ናቸው) ከህብረተሰቡ የወጡ ሳይሆኑ ከሌላ ዓለም የመጡ ፍጡራን ናቸዉ ማለት ነው የሚል የአንድምታ ጥያቄ ሊያስነሳ እንደሚችል አላጤነችውም። "ሰዎቹ" እሷ ከምትሠራበት የማህበረሰብ አካል ከሆኑ ለምን ዝሙት አዳሪዋ ብቻ ሰበብ ልትሆን ትችላለች? ዝሙት አዳሪዋ በራሷ መቼም በሽታውን ፈጠረችው ልንል ካልቻልን በስተቀር ይህ አባባል ተቀባይነት የለውም።

"የዝሙት አዳሪነትና የህብረተሰቡ ግምት" በሚለው ንኡስ ርዕሷ ያቀረበችው አስተያየት "በአጠቃላይ ... ህብረተሰቡ ስለዝሙት አዳሪነት ያለው ጥላቻና ነቀፌታ አፋዊ እንጂ ልባዊ አይመስልም። ... የሚያወግዘው ወገን ሁሉ ውግዘቱን ተግባራዊ ቢያደርግ ኖሮ ለዝሙት አዳሪነት መቀነስ እያደረም መጥፋት ብዙ በረዳ ነበር። (ገፅ፣ 8)" በማለት አስተያየቷን ትሰጣለች። ምንም እንኳ ዝርዝር መረጃ ሳትሰጥ ማጠቃለያ ላይ ብትደርስም

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

ከሰጠችው ሀሳብ ጋር እስማማለሁ። ምክንያቱም በአፉ የሚናገረውን የነቁፊታና "የጥላቻ" ሁኔታ በተግባር ቢያውለው ኖሮ ሴቷ ከማን ጋር ልትዘመት ለዝመት አዳሪነት መሃያ ትሆማራ ነበር? ለዝመት አዳሪነት "መሃያ" መፈጠር ህብረተሰቡ ራሱ አስተዋፅኦ አበርክቷል የሚለውን አባባል እኔም የምጋራው ነው። ስለሆነም ዝመት አዳሪነትን በማስፋፋት በኩል ህብረተሰቡ ራሱ ድርሻ አለው።

አጥኚዋ በመጀመሪያው ክፍል በንኡስ ክፍል አራት ያቀረበችው ዝመት አዳሪነትን ለመዋጋት የተደረጉ መከራዎች በማለት ያቀረበችው ከአብዮቱ ፍንዳታ ወዲህ የችግሩን አስከፊነትና አሳሳቢነት በልዩ ልዩ ጽሑፎች አስተያየቶች፣ ትችቶችና መፍትሔ ይሆናሉ የተባሉ ሀሳቦች በመቅረብ ላይ መሆናቸውን በመግለጽ " ... ዝመት አዳሪነትን ከአዲስ አበባና ከአገሪቱ በመላ ፈጽሞ ለማጥፋት በሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መዋቅር እንዲሁም በውስጡ የሚገኙትን ሴቶች ስፍራ በሚመለከት መሠረታዊ ለውጥ ማድረግ ያስፈልጋል። (ገፅ፣ 9)" በማለት በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የማህበራዊ ጉዳይ መምሪያ በ1968 ዓ.ም. ያዘጋጀውን ጥናት ጠቅሳ ታጠቃልላለች። ይሁን እንጂ በምን መልኩ ከአዲስ አበባም ሆነ ከአገሪቱ የዝመት አዳሪነትን ተግባር ማጥፋት እንደሚቻል ያስቀመጥችው የመፍትሔ ሀሳብ የለም። በደፈናው "መሠረታዊ ለውጥ ማድረግ ያስፈልጋል" የሚል "አብዮታዊ መሪ የመፈክር" ሀሳብ ነው ያቀረበችው። ጥናቷ የ "ሶሲዮሎጂ" ትንተና ከሆነ አልቀረ የመፍትሄ ሀሳብ የምትለውን ማመለከት ነበረባት የሚል አስተያየት አለኝ።

ፀዳለ ከላይ የተገለጹትን የጥናቱን አላማ ሆነ አላማዋን ከግብ ለማድረስ የተጠቀመችባቸው አራት የልቦለድ ሥራዎችን ነው። እነሱም <u>እንደወጣች ቀረች</u> (1941)፣ <u>የእንባ ደብዳቤዎች</u> (1952)፣ <u>ሴተኛ አዳሪ</u> (1956) እና <u>አባቴን ንገሪኝ</u> (1958) የተሰኙትን በመምረጥ ነው። በእነዚህ ልቦለዶች መነሻነት የዝመት አዳሪነት ሕይወት ምን እንደሚመስል ተንትናለች። ትንታኔዋም እያንዳንዱን ልቦለድ ከዘማ ገጸባህርያት አንፃር የታሪኩን ፍሰት ተከትላ ልቦለዶቹን ከይዘት አኳያ ጨምቃ ማቅረብ ነው። በሌላ አገላለጽ በልቦለዱ ውስጥ የተሳለችውን ዘማ ገጸባህርይ ከመጀመሪያ እስከ ታሪኩ ማለቂያ ድረስ የደረሰባትን ችግር፣ ወደ ዝመት ሊያስገባት የቻለውን መንስኤ ነገር፣ ከገባች በኋላ ያሳለፈችውን የስቃይ ሁኔታ የልቦለዱን አቀራረብና ይዘት ባለወጠ መልኩ ያቀረበችበት ነው። በዚህ መልኩ ታሪኩን ጠቅለል አድርጋ ካስተዋወቀች በኋላ የተጠቀሱት ልቦለዶች ዝመት አዳሪዎች ላይ የሚደርሱ ችግሮችን አሳይተዋል፣ ደራሲያኑም የማህበረሰቡ ዋና

ችግር የሆነውን ዝመት አዳሪነትን በድርሰቶቻቸው አሳይተዋል፣ እንዲሁም አንዳንዶቹ የመፍትሔ ሀሳብ ሰጥተዋል በማለት ትገልፃለች።

አክላም በልቦለዶቹ ከተሳሉት ዝመት አዳሪ ገጸባህርያት አንፃር ሲታይ ለዝመት አዳሪነት ምክንያት የኢኮኖሚ ችግር እንደሆነ ትጠቅሳለች። ከዚህ ላይ አጥኚዋን ወደ ጥያቄ የሚያስገባ አስተያየት አለኝ። እሱም ልቦለዶቹን ነው የምትተነትነው ወይስ የሶሲዮሎጂ ጥናት ነው የምታደርገው የሚል ጥያቄ ነው። በእኔ በኩል ልቦለዶችን ሳይሆን አጥኚዋ የምትተነትነው የሶሲዮሎጂ ጥናት የምታካሄድ ናት የሚል አመለካከት አለኝ። ለዚህም አስተያየቱ መነሻ የሆነኝ ጥናቱን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ሳየው የምታነሳው ሀሳብ በሙሉ ልቦለዳዊ ትንታኔን የተከተለ ሳይሆን የሶሲዮሎጂ ጥናት የተከተለ አካሄድና አሠራርን የያዘ ሆኖ ስለአገኘሁት ነው። ይህን ስል ልቦለድን ሶሲዮሎጂካዊ የአጠናን ሂደት እንዲይዝ ማድረግ አይቻልም ማለቱ አይደለም። ይህ ጥናት ከእኔ የጥናት ሥራ ጋር የማይገናኝና ልዩነት ያለው መሆኑን ለመጠቆም እንጂ።

ይህ ጥናት "ዝመት አዳሪነት በአርባና ሀምሳ ዐስርታት የአማርኛ ልቦለዶች" የሚል ሆኖ ዋና ትኩረቱ ስነጽሑፉ የዝመት አዳሪነትን ችግር ለመዋጋት ያበረከተውን ድርሻ፣ በደራስያን በኩል ለችግሩ የተሰጠውን ትኩረት እና ለወደፊቱ ስነጽሑፍ ሊያበረክት የሚችለውን የሥራ ድርሻ ለመጠቆም የሚሉት ላይ ነው። ጥናቱ እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በአርባዎቹና በአምሳዎቹ አስርት ዓመታት በታተሙት አራት የአማርኛ ልቦለዶች ላይ ትንትኔ በመስጠት ያተኮረ በመሆኑ ከኔ ጥናት ጋር በአላማም ሆነ በአሰራር ዘዴ ፈጽሞ ይለያያል። የእኔ ጥናት ሶስት በሴተኛ አዳሪ ሕይወት ላይ የሚያጠነጥኑ ልቦለዶችን (ሴተኛ አዳሪ፣ ሌቱም አይነጋልኝ እና መጎልየ መጎልይ ዘካዛንችስ) ወስዶ የሴተኛ አዳሪዎች የሰብአዊነት መጎጠፍ እና የማህበረሰቡን በነዚህ ሴቶች ላይ ያለውን የተዛባ ባህላዊ አመለካከት ምን እንደሚመስል ማስረጃዎቹን ከድርሰቶቹ ውስጥ እየነቀሱ በማውጣት አንድምታዊ የሆነ ትንታኔ በመስጠት ማሳየትና ማስተንተን ነው።

6. ከሴተኛ አዳሪዎች ጋር ተያያዥነት ያለው ሌላው ጥናት የደጅኔ ማንደፍሮ "የሴተኛ አዳሪዎች የስም ለውጥ በአዲስ አበባ"፡ የሚለው በ1987 ዓ.ም. የቀረበው ዲማጽ ተጠቃሽ ነው። ጥናቱ በአራት ምዕራፎች የተከፈለ ሆኖ ስለሰው ስም አሰያየም ልማድና ተግባር፣ የሰው ስም ጥንታዊ አመጣጥና ለውጥ እንዲሁም የሴተኛ አዳሪዎች ተለዋጭ ስማቸውና ስማቸውን እንዲለውጡ ያደረጉዋቸው ምክንያቶች በማንሳትና በመጨረሻም የማጠቃለያ ሀሳብ በመስጠት የቀረበ ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

አጥኚው ሴተኛ አዳሪዎች የስም ለውጥ ከሚያደርጉባቸው ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹ ከአገር ቤት ይዘውት በመጡት ስም በቀጥታ የሚጠሩ ከሆነ ከወላጆቻቸው ተጣልተው የመጡት ወላጆቻው በስምአቸው አጠያይቀው እንዳይደርሱባቸው ለማምለጫ፣ ከባሎቻቸውም ተጣልተው ወይም ተፋተው የመጡትም እንደዚሁ። ሌላው ምክንያት ደግሞ መጠሪያ ስማቸው ከስተማው የስያሜ ዘይቤ ጋር የማይጣጣም ሆኖ ካገኙት ከስተማው "የስልጣኔ" ሂደት ጋር ለመመሳሰል የመጀመሪያ ስማቸውን በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ ሊለውጡ እንደሚችሉ ሲገልጹ ከነዚህ ምክንያቶች በተጨማሪ ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ መልኩም ስማቸውን የሚቀይሩ ሴተኛ አዳሪዎች ያጋጠሙት መሆኑን ይናገራል። ለምሳሌ መስለምነትን የሚገልጹ ስያሜዎች ወዲያውኑ በሌላ ስም የሚተኩ እንደሆኑ ባደረገው ቃለምልልስ መረዳቱን ይገልፃል።

የደጅኔ ጥናት ዓላማ ለምን ሴተኛ አዳሪዎች ስማቸውን እንደሚለውጡ ማወቅ ነው። ለዚህም የሚለውጡበትን ምክንያት ባደረገው ቃለመጠይቅ አግኝቷል። ጥናቱም ያተኮረው በእውነት በሥራው ላይ የተሰማሩ ሴተኛ አዳሪዎችን በመጠየቅ ነው። የእኔ እና የደጅኔ ጥናት በአላማም ሆነ በአሰራር የተለየ ነው። እኔ የማጠናው በተመረጡ ሶስት ስነጽሑፎች ውስጥ ያሉትን ምናባዊ ሴተኛ አዳሪዎች ሰብእና ላይ በመሆኑ የምንለያይበት ነጥብ ነው። በእኔ ጥናት ላይ የአንዲት ሴተኛ አዳሪ የስም ለውጥ ቢያጋጥመኝ ለስሟ መለወጥ ምክንያት የምስጠው ትንታኔ ደጅኔ አገኘሁት በሚለው ጥሬ ትርጉምና ምክንያት አይነት አይደለም። እኔ የምመለከተው በሰበካው ሳይሆን "ፈርሱን" ገልብጬ ከልዩ ልዩ ሁኔታዎችና ሁነቶች ጋር አገናኝቼ የሁኔታዎችን መከሰቻ የሁነቶቹን ማስረጃ ከዚያው ከጽሑፎቹ (texts) ውስጥ ጠቋሚ ቃላት ወይም ሐረጋት አለዚያም ዓረፍተነገሮችን መዝገር በነቃሽነት በማቆም ነው። ስለሆነም በዚህ የአሰራር ብዛል ልንለያይ እንችላለን።

7. በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ተያያዥነት ያለው ጥናት በ1979 ዓ.ም. በደጅኔ ወ/ትንሳኤ ቀርቧል። ደጅኔ "ማህበረሰባዊ እውነታና የአቀራረብ ቴክኒክ በአሥራ ዘጠኝ ሃምሳዎቹ የአማርኛ ቤሣ ልቦለዶች ውስጥ" በማለት ባቀረበው በክፍል አንድ ስር "ተደጋጋሚ ማህበረሰባዊ ጭብጦች በአስራ ዘጠኝ ሃምሳዎቹ የአማርኛ ቤሣ ልቦለዶች ውስጥ" በሚል ንኡስ ርዕስ ዝሙት አዳሪነትን ሲያነሳ ሴቶች ወደ ዝሙት አዳሪነት ሕይወት የሚሰማሩበት ምክንያት ዝሙት አዳሪነት በህብረተሰቡ ላይ የሚያስከትለው ጠንቅ፣ የዝሙት አዳሪነት መንስኤዎች ምን እንደሆኑ ገልጿል። ከቤሣ ልቦለዶቹ በመነሳት ዝሙት አዳሪነት ከኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች የሚመነጭና በዚሁ ኑሮ የሚሰማሩ

ሴቶች ሕይወታቸው የተሳሳቀለና በመጨረሻም የከፋ እንደሆነ በመጥቀስ ያጠቃልላል። የደጀኔ ጥናት ያተኮረው "ማህበረሰባዊ እውነታና የአቀራረብ ቴክኒክ በአስራ ዘጠኝ ሃምሳዎቹ የአማርኛ ቤሣ ልቦለዶች ውስጥ" በሚል ላይ ሆኖ ቤሣ ልቦለዶችን ብቻ በመመልከት በተጠቀሰው ሃምሣዎቹ ዓመታት ተደጋጋሚ ሆነው ከሚቀርቡት ማህበረሰባዊ ጭብጣዊ እውነታዎች አንዱ ዝሙት አዳሪነት መሆኑን በመጥቀስ ይህ ጭብጥ ተደጋግሞ በተለያዩ ቤሣ ልቦለዶች መምጣቱ በወቅቱ ደራስያንን ያሳሰበ ጉዳይ እንደሆነ ይገልፃል። በእርግጥ አሳሳቢነቱ እንዳለ ሆኖ ለምን ሊያሳስባቸው ቻለ? የሚለውን ጥያቄ አንስቶ ግን ምክንያቱን አይነግረንም። ወይም ይህንን የሚያመላክት ፍንጭም አይመላክተንም። የጥናቱ ትኩረት በወቅቱ በቤሣ ልቦለዶቹ ውስጥ ምን ምን ማህበራዊ እውነታዎች ተነሱ? በእንዴትስ ያለ የአቀራረብ ቴክኒክ ቀረቡ የሚሉት ላይ ብቻ ያነጻጸረ ነው። በመሆኑም ከእኔ ጥናት ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም። የእሱ ጥናት እንደአብዛኛዎቹ የተጠቀሱት ጥናታዊ ጽሑፎች ሶሲዮሎጂያዊ ነው። የእኔ ጥናት ግን ከዚህ መለየቱን ቀደም ብየ ጠቅሻለሁ።

8. የአሰፋ መሉጌታ "የከተማ ህይወት በአምስት ደራስያን የልቦለድ ሥራዎች" በ1980 ዓ.ም. ባቀረበው ዲማጽ ሴተኛ አዳሪነትን በተመለከተ አንስቷል። ጥናቱ ሁለት ምዕራፎችን የያዘ ነው። የመጀመሪያው ምዕራፍ የከተማ ሕይወት በትምህርት፣ በዝሙት አዳሪነት፣ በባህል ግጭትና በርዕዮተ አለማዊ ትግል በልቦለዶች ውስጥ መቀረጹን የሚዳስስ ነው። አሰፋ፣ በጥናቱ የመጀመሪያው ምዕራፍ ዝሙት አዳሪነትን እንደ አንድ ጉዳይ አንስቶ ተመልክቷል። ዝሙት አዳሪነትን ከከተማ ሕይወት ጋር በማዛመድ ያሳያሉ ያላቸውን ስራዎች በመምረጥ ለማየት ችሏል። ጥናቱ ሀዲስን፣ ሰመመንን፣ ወንጀለኛው ዳኛን እና የቀይ ኮከብ ጥሪን በመመልከት ዝሙት አዳሪነት በልቦለዶቹ ምን እንደሚመስል ቃኝቷል። ከነዚህም ሥራዎች በመነሳት ዝሙት አዳሪነት ከማህበራዊ ወይም ከኢኮኖሚያዊ ቀውሶች የሚመነጭ አስከፊ ሕይወት መሆኑን ገልጿል። ይህንን ማጠቃለያ ሊሰጥ የቻለው በልቦለዶቹ ውስጥ የተጠቀሱት ዘማ ገጸባህርያት ከተረኩበት እና ከተሳተፉበት ድርጊታዊ ክንዋኔዎች በመነሳት ነው። በመሆኑም አጥኚው ጥናቱን ያቀራኘው ከሶሲዮሎጂ የአጠናን ዘዴ ጋር በመሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር የሰፋ ልዩነት ያለው ሆኖ ይገኛል።

9. የአስካለ ለማ "ገፀ-ሴት በአማርኛ ልቦለድ ውስጥ" በሚል በ1974 ዓ.ም. የቀረበው ዲማጽ ሌላው በሩቁም ቢሆን ተያያዥነት ያለው ጥናት ነው። አጥኚዋ ከስምንት የልብወለድ ስራዎች ሴት ገጸባህርያትን በመውሰድ የሴትን ባህርያት የተመለከተችበት ነው። ሴቶች ከሚታይባቸው ልዩ ልዩ ባህርያት ውስጥ በዝሙት አዳሪነት የተሳለች ዘማ ገፀባህርይስ ምን

ዓይነት ባህርይ ሊኖራት እንደሚችል የተመለከተችበት ሲሆን ደራስያንስ ምን ዓይነት ባህርይ እንድትይዝ አድርገው እንደቀረጿት ለማሳየት ከየልቦለዶቹ በመንቀስ አውጥታ አሳይታለች። ከእኔ ሥራ ጋር ያለው ተያያዥነት የራቀ በመሆኑ ስለገፀ-ሴት ባህርያት በጥልቀት ማየቱ አስፈላጊ ባለመሆኑ ከዚህ ላይ አላነሳውም።

10. የደምሰው ገ/ኢየሱስ፣ "ሴተኛ አዳሪነት በአራት የአማርኛ ረዥም ልቦለዶች ውስጥ" በሚለው በ1996 ዓ.ም. የቀረበው ዲማጽ ሌላው ተጠቃሽ ሥራ ነው። ይህ ጥናት አራት ምዕራፎች ያሉት ነው። ሁለተኛው፣ ሶስተኛው እና አራተኛው ምዕራፍ በሴተኛ አዳሪነት ምንነት፣ መንስኤ፣ አጠቃላይ ሰብእና እና የሴተኛ አዳሪነት ሕይወት በተመረጡ ረዥም ልቦለዶች ዙሪያ እንዴት ያለ ገጽታ እንዳለው የተመለከተበት ነው። የተመረጡትም ረዥም ልቦለዶች የህሊና ደወል፣ ወገግታ፣ ቆንጆዎቹና ሌቱም አይነጋልኝ የተሰኙት ናቸው። የሴተኛ አዳሪነትን ሰብእና ለማሳየት ከየልቦለዶቹ ሴተኛ አዳሪ ገጸባህርያትን በመውሰድ ነው የተጠቀመው። በዚህም መሠረት ከህሊና ደወል ሽታየና ዝናሽ፣ ከወገግታ፣ ማርታና ስንዱ፣ ከቆንጆዎቹ፣ ዘውድነሽና የምሥራች፣ ከሌቱም አይነጋልኝ ማሚት እሸሩሩ፣ ጠንፍየለሽ እና ትርሲት የተባሉትን ሴተኛ አዳሪ ገፀባህርያትን በመውሰድ የሴተኛ አዳሪዎችን ሰብእና እና ሕይወት እንዲወክሉ ተደርጓል። በእነሱም ንግግርና ድርጊት ዙሪያ የሰብእናቸውን ምንነት፣ የሕይወታቸውን አስከፊነት ለማሳየት ሞክሯል። ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይ ሊያደርገው የሚችለው ልቦለዶቹን በማንበብ የሴተኛ አዳሪዎችን ስብእና እና ሕይወት በገፀባህርያቱ አማካይነት ብያኔ ለመስጠት በመሞከሩ ነው። የሴተኛ አዳሪዎችን የሰብእና ምንነት የሚደርስባቸውን አስከፊ ችግር በወሳይ ገፀባህርያት አማካይነት ለማሳየት ጥሯል። ይህ አካሄድ በመጠኑም ቢሆን ከኔ ጥናት ጋር የሚጋራው ነው። ነገር ግን የአጠናን ስልታችንና የጥናት ትንታኔ አካሄዳችን አንድ አይደለም። የእኔ የትንታኔ ስልት ከልቦለዶቹ በተጠቀሱ የገፀባህርያት የንግግር ቃላት፣ ሀረጋት ወይም ዐረፍተነገራት ውስጥ ያላቸውን ፍካሬያዊ ትርጉም በአንድምታ በመፈከር እማሬያዊ ትርጉማቸው ላይ ሳይሆን የፍካሬ ፍቻቸውን "በፊርሱ" ገልብጦ ባህላዊ እና ማህበረሰባዊ የትርጉም አንድምታቸውን ማሳየት ነው። በዚህ በኩል ከደምሰው የትንታኔ አሰጣጥ ጋር እንለያያለን።

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

2.2. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

2.2.1. የሴተኛ አዳሪነት ታሪካዊ ደራ

ሴተኛ አዳሪነት በኢትዮጵያ መቼ እንደተጀመረ፥ በትክክል ባይታወቅም አዲስ መጥ እንዳልሆነ ይገመታል። አንዳርጋቸው ተስፋዬ "የሴተኛ አዳሪነት የሚያስከትለው ችግር" በሚል ርዕስ በ1959 ዓ.ም. በቀድሞው የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ማህበር መጽሔት ባቀረቡት ጽሑፋቸው ስለሴተኛ አዳሪነት "... በቂ ጥናት ስላልተደረገ ጊዜውንና አጀማመሩን ለመወሰን አዳጋች ነው። ሆኖም ሴተኛ አዳሪነት (አመንዝራነት) አዲስ አለመሆኑን አንዳንድ አገር ጐብኝዎች በጽሑፋቸው በሰጡት ማስረጃና እንዲሁም ከሽማግሌዎች በአፍ ከሚተረከው ለመረዳት ይቻላል" በማለት ሲገልጹ ይኼው የመጣጥፉ አቅራቢ አጀማመሩን ዲ. ቱጋ የተባለውን ደራሲ በስም በመጥቀስ የሚከተለውን ሀሳብ አስፍረዋል።

> ዲ. ቱጋ የተባለ ደራሲ እንደ አውሮጳ አቆጣጠር በ1871 ዓ.ም. እንደጻፈው መንገደኞች /ነጋዴዎች/ በየመንገዳቸው ላይ የሚያስቀምጧቸው ሴቶች እንዳሉና እነዚህም ሴቶች ለሚሰጡት አገልግሎት እንደሚከፈላቸው ገልጿል። እነዚህም ሴቶች በአንድ (ወንድ) መንገደኛ ስለማይወሰኑ ሴተኛ አዳሪዎች መሆናቸው አይካድም። እንዲሁም ደግሞ ብዙ ሰዎች እቁባት ያስቀምጡ እንደነበር ይነገራል። በዚህም መልክ ይቀመጡ የበሩት ሴቶች ከወዳጆቻቸው በየዓይነቱ ስጦታ እንደሚያገኙ አያጠራጥርም። ምንም እንኳን ሴተኛ አዳሪዎች ነበሩ ለማለት ባያስደፍርም የግብረ ሥጋ ግንኙነታቸው እንዳገልግሎት ተቆጥሮ ዋጋ ማስገኘት መጀመሩ ለሴተኛ አዳሪነት የመጀመሪያውን እርምጃ ይሏል።
>
> (አንዳርጋቸው፣ 1959፡ 24)

ከላይ ከተጠቀሰው ጽሑፍ ሁለት ሀሳቦችን ማርቀቅ ይቻላል። እነሱም አውሮጳዊው ጸሐፊ በ1871 ዓ.ም እንደጻፉት ለሴተኛ አዳሪነት መጀመር ነጋዴዎች ወይም መንገደኞች በየሄዱበት አካባቢ የሚያስቀምጧቸው ሴቶች ለነጋዴዎቹ ወይም ለመንገደኞቹ የሚሰጡት የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳገልግሎት እየተቆጠረ መምጣቱ፤ ለሴቶቹ ጥቅም ማስገኘት መቻሉ ካስቀመጡዋቸው መንገደኞች ወይም ነጋዴዎች ውጭ ከሌላም ጋር ድርጊቱን

መፈጸማቸው አይቀሬ መሆን እንደሴተኛ አዳሪዎች ሊያስቆጥራቸው ቻለ። ሌላው ሁለተኛው ሀሳብ ደግሞ "ብዙ ሰዎች ("ሰዎች" የሚለው ቃል ወንዶች ለማለት እንደሆነ ግልፅ ነው ከሚል አስተያየት በመነሳት ነው)፥ እቁባት ያስቀምጡ እንደነበር ይነገራል" ከሚለው አገላለፅ የሚወጣ ነው። "እቁባት" ማለት አንድ ወንድ ከ"ህጋዊ" ሚስቱ ውጭ በድብቅ ያስቀመጣት "ህጋዊ" ያልሆነች ከሚስት ባልተናነሰ ሁኔታ ብዙ ጥቅማጥቅሞች በአስቀማጩ ወንድ የሚደረግላት ሴት ናት። የቤቷን ወጭ ሁሉ የሚሸፍነው አስቀማጩ ወንድ ነው። በድብቅ ካልሆነ ከዚህ ወንድ ውጭ ከሌላ ወንድ ጋር በይፋ "ለመቅበጥ" በፍጹም አትችልም። አስቀማጩ ወንድ ልዩ ልዩ ስጦታ በገንዘብ አልያም ባይነት ያደርግላታል። ይሁን እንጂ የተለያዩ ነገሮችን ከወንዱ ብታገኝም እንደሴተኛ አዳሪ ሊያስቆጥራት አይችልም። ማህበረሰቡም" የእገሌ ቅምጥና ይላል እንጂ እንደ ነውር አይቆጥርባትም። ወንዱንም እንደ "ባለጌ" ወይም ባህል ረጋጭ ጋጠወጥ ቆጥረው አያገሉትም። በጥንታዊት ኢትዮጵያ የተለመደ ከመሆኑም ባሻገር ባህላዊ ፈቃድን ያገኘ ተግባር ነበር ለማለት ይቻላል። ሴቷ ምንም እንኳን የጦላ ነቀፌታን ባያስገኝባትም ኑሮዋን የምትደጉመው ባስቀማጩ ስጦታ በመሆኑ ከወንዱ ጋር በምታደርገው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ግንኙነት በመሆኑ "ሥጋዋን" አበርክታ የምታገኘው ያገልግሎት ዋጋ መሆኑ አይቀሬ ነው። ስለሆነም ሴቷ ለወንዱ "ገላዋን"፤ ወንዱ ደግሞ በምላሹ ገንዘቡን ከሰጠ በመካከላቸው ያለው ግንኙት "ሰጥቶ የመቀበል" ዓይነት ነው። ይህም ተግባር ቀስ በቀስ ፀሐፊውም እንዳሉት "የሴተኛ አዳሪነት የመጀመሪያው እርምጃ ነው" ለማለት የሚያስችል ሀሳብን እንድናረቅ ያደርጋል።

ከዚህም ሌላ የማንም ቅምጥ ወይም እቁባት ሳይሆኑ ጠላና ጠጅ በመሸጥ የሚተዳደሩ ሴቶች ንግዳቸው እንዲነሳላቸው በወዳጅነት ስም ከተወሰኑ ወንዶች ጋር የገዘሙት ተግባር ይፈጽሙ እንደነበር ይታመናል።

> ...ጠጅ ከቤት መጠጥነት አልፎ የገበያ ሽቀጥ መሆን ሲጀምር ኮማሪዎች በሚል ስም ጠጅ ነጋዴ ሴቶች በየከተማው መጠጥ ቤት በመክፈታቸው በመጠጥ ሳቢያ ሌላም ተጨማሪ አገልግሎት ለተወሰኑ ወንዶች መስጠት እንደጀመሩ ይነገራል። ምንም እንኳን ወዳጅነት የሚለው ስሜት ቢያመዝንም፥ ለሴተኛ አዳሪነት መግቢያ መሆኑ ሊዘነጋ አይገባውም።
>
> (አንዳርጋቸው፤ 1959፤ ገፅ፤ 24)

እነኚህ መጠጥ የሚነግዱ ሴቶች በቀጥተኛ መንገድ ከደንበኞቻቸው የሚቀበሉት ገንዘብ ወይም ስጦታ አልነበራቸውም። ነገር ግን የደንበኞቻቸውን ቁጥር በማብዛት መጠጡ እንዲነሳላቸው ያደርጉ ነበር። መጠጥ ከምትሸጠው ሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት፥ የሚፈጽሙ ወንዶች መጠጥ ለመጠጣት ከጓደኞቻቸው ጋር የሚሄዱት ወደ ለመዷት "ኮማሪት" ጋር ስለሚሆን በዚህ መልክ ሴቷ ከተለያዩ ወንዶች ጋር መቀራረቧና መላመዷ አይቀሬ ይሆናል። በዚህ መልክ ቀስ በቀስ ኮማሪዋ ብዙ የወንድ ወዳጆች ይኖሯታል። ይህም ለሴተኛ አዳሪነት መፈጠር በር ከፋች ሊሆን እንደቻለ የሚያመለክት ሁኔት ነው።

ሪቻርድ ፓንክረስት "The History of Prostitution in Ethiopia" በሚለው ጥናታቸው የሚከተለውን አስፍረዋል።

> There are, however, indications that on Institution related to prostitution existed at royal camps of the middle ages, at the seventeenth century city of Gondar... (Page፣159)

ከፓንክረስት ጽሑፍ የምንረዳው በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በንጉሣውያን ቤተሰብ ግቢ (royal camps) በጐንደር ከተማ ከሴተኛ አዳሪነት ጋር ተያያዥነት ያለው ተግባር ተቋማዊ በሆነ መልኩ ለመኖሩ አመለካቾች እንደነበሩ ነው፡ በማከልም በሀገሪቱ የንግድ ማዕከል ሆነው ያገለግሉ በነበሩ የድንበር ግዛቶች (periphery of the empire) ሴተኛ አዳሪነት መኖሩንና ቀስበቀስ እያደገች በመጣችው በአዲስ አበባና በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማለቂያና በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በተቆረቆሩ ከተሞች ውስጥ ስር እየሰደደ ለመምጣቱ ብሎም ለዛሬው ዘመናዊ ለሚባለው ሴተኛ አዳሪነት ዓይነተኛ መሠረት መሆኑን ለመገመት አያዳግትም በማለት አስተያየታቸውን ፓንክረስት አስፍረዋል። (ገፅ፣ 159) ከፓንክረስትም አገላለፅ የምንረዳው የሴተኛ አዳሪነት ተግባር በአገራችን አዲስ መጥ አለመሆኑንና የረዥም ዓመት እድሜ "ባለፀጋ" መሆኑን ነው።

ሴተኛ አዳሪነት መቼ ተጀመረ ለሚለው ጥያቄ በእርግጠኝነት ቁርጥ ያለ መልስ ለመስጠት አስቸጋሪ ቢሆንም የአጀማመሩን ሁኔት ግን በሁለት መልኩ ጠቅለል አድርጐ ለማስቀመጥ እንደሚችል የፓንክረስትና የአንዳርጋቸው ጥናታዊ ጽሑፎች መነሻ ሊሆኑ ይችላሉ። ይኸውም የመጀመሪያው የሴተኛ አዳሪነት "ዘር የተበተነው" በጐንደር ከተማ በጥንታዊ ንጉሣውያን ቤተሰብ ግቢ ተቀማጭ በነበሩ "ጋለሞታዎች" ወይም ባሎቻቸውን ፈተው በተቀመጡ "ድረ-ፊት" ሴቶች ለወንዱ በሚሰጡት የግብረ ሥጋ ግንኙነት አገልግሎት

በሚደረግላቸው የአገልግሎት ዋጋ ክፍያ አንዱ እና የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛል። ሁለተኛው ደግሞ ጠላና ጠጅ እየነገዱ ይኖሩ በነበሩ ሴቶች አማካይነት ነው። ይህም ጠላና ጠጅ ነጋዴ ሴቶች ንግዳቸው ይነሳላቸው ዘንድ መጠጣቸውን ለመጠጣት ከሚመጡት ወንዶች ጋር በሚፈጽሙት የዝሙት ተግባር ምክንያት ለሴተኛ አዳሪነት መጀመር ሌላው እርምጃ እንደነበር ለመገመት አያዳግትም። እነዚህ ኮማሪ ሴቶች ለጠጅና ጠላ ንግዳቸው መነሳት ሲሉ "ወዳጅ" እያሉ አብሮዋቸው "የሚቀብጥ" ጠጭ ወንድ መያዛቸው ቀስ በቀስ ለሴተኛ አዳሪነት መጀመር ዓይነተኛ አስተዋጽኦ ለማበርከቱ ከዛሬው ዘመናዊ የቡና ቤቶች፣ የመጠጥ ቤቶችና ከሴት "የግሮሰሪ" ባለቤቶች ለመረዳት ይቻላል። የጥንቱ ጠጅና ጠላ ሻጭ ሴቶች ከጠላና ከጠጅ ንግዱ ባሻገር ከወዳጆቻቸው በሚያገኙት ተጨማሪ የተለያዩ ስጦታዎች ኑሮዋቸውን ይደጉሙ ነበር። የዛሬዎቹም ሴት የመጠጥ ቤት ባለቤቶችም ይህንን ይፈጽሙታል። የመጠጥ ቤት ባለቤት በመሆናቸው "የተከበሩ" የሚል ስም ስላስገኘላቸውም "ከተራዎቹ" ሴተኛ አዳሪዎች ለየት ባለ መልኩ ከወንዶች ጋር ዝሙት በመፈፀም የተሻለ ገቢ እንደሚያገኙ ግልፅ ነው። በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱ የጥንታዊ ሴቶች ይፈጽሙት የነበረው ("በቅምጥ መልክም ሆነ "በወዳጅነት" ስበብ) የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከአገልግሎት ዋጋ ክፍያ ጋር ተያያዥነት የነበረው በመሆኑ ለዛሬው ሴተኛ አዳሪነት መፈጠርም ሆነ መስፋፋት የመሠረት ድንጋይ ሆኗል ለማለት ያስችላል። ዛሬም ቢሆን የሴተኛ አዳሪነት "ሙያ" በይበልጥ ተስፋፍቶና ይበልጥ ተቆራኝቶ የሚገኘው መጠጥና የመጠጥ ውጤቶች በሚነገዱበት ሥፍራ ነው። ይህ ራሱ በሁለተኛ ደረጃ የተጠቀሰውን የሴተኛ አዳሪነት የአጀማመር ሂደት ግምት "ትክክል" ነው ለማለት የሚያስችል ነው።

እንደ አውሮፖውያን ዘመን አቆጣጠር በ1636 ዓ.ም ጎንደር ለኢትዮጵያውያን ነገሥታት ርዕሰመዲና ሆና መቆርቆር በርካታ የሆኑ የሥራ መስኮች በቋሚነት የሥራ እንቅስቃሴያቸውን ወደ ጎንደር አዛውረው ማካሄዳቸው፣ የተለያዩ የሥራ መስኮችም ለመክፈትና እያበቡ ለመምጣት ምክንያት እንደሆነች ፓንክረስት በተጠቀሰው ጥናታዊ ጽሑፋቸው ገልጸዋል። አያይዘውም እንደሌሎቹ የሥራ መስኮች የሴተኛ አዳሪነትም "The women whom Alvares had referred to as 'prostitutes' a century or so earlier now doubtless transferred their activities to Gondär. (page 160)" በማለት ይገልፃሉ። በንጉሣውያን ቤተሰብ ግቢ (ቋሚ ባልነበረው ተንቀሳቃሽ የድንኳን ከተማ) የተከሰተው የሴተኛ አዳሪነት "ሙያ" ጎንደር በቋሚነት የንጉሣውያን ርዕሰመዲና ስትሆን ወደዚሁ መዛወሩንና እንቅስቃሴውን መቀጠሉ የማያጠራጥር መሆኑን ፓንክረስት

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። ይህም የሴተኛ አዳሪነት "ሙያ" ይበልጥ ስር እየሰደደ የሄደው በከተማና የከተማነት ባህርይ ባላቸው ቦታዎች እንደሆነ አመላካች ነው። የከተሞች መስፋፋት ለሴተኛ አዳሪነት "ሙያ" ማደግና መጨመር ዓይነተኛ ምክንያት ሆኗል ለማለት ያስችላል። ፓንክረስት አያይዘውም፥ ለሴተኛ አዳሪነት በኢትዮጵያ መስፋፋት በጥናታቸው መደምደሚያ ላይ የሚከተለውን አስፍረዋል።

> The coming of the Italians, who included hundreds of thousands of soldiers and workers, thus inaugurated an era of extensive, highly developed prostitution, the legacy of which continues in Asmara, Addis Ababa and other Ethiopian towns to this day. (page, 178)

በማለት ሴተኛ አዳሪነት በአስመራ፣ በአዲስ አበባና በሌሎችም ከተሞች በግልፅ እየተስፋፋና እያደገ መምጣቱን ሲገልጹ ለዚህ መስፋፋት የጣሊያን ወራሪ ሠራዊትና ሠራተኞች ወደ ሀገሪቱ መግባት ዓይነተኛውን ሚና መጫወታቸውን አክለው ገልፀዋል።

2.2.2. ሴተኛ አዳሪነት ምንድን ነው?

የሴተኛ አዳሪነትን ታሪካዊ ዳራ ከፍ ሲል በተገለጸው ጽሑፍ ለማየት ተሞክሯል። በዚህ ክፍል ደግሞ የሴተኛ አዳሪነትን ምንነትና ትርጉም ከተለያዩ ሰነዶችና ጥናታዊ ጽሑፎች እንዲሁም ከመዝገበ ቃላት የተሰጠውን ትርጉም በማጣቀስ ለጥናቱ ተስማሚ የሆነውን ትርጉም ለመውሰድና ለማሳየት ይሞክራል። የቃሉን ታሪካዊ እድገትም በጥልቀትም ባይሆን በግርድፉ ለማመላከት ይጣራል።

ሴተኛ አዳሪ የሚለውን ቃል የደስታ ተክለ ወልድ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት በገጽ 1210 ላይ "መበለት፣ ባል አልባ፣ ብቻዋን የምታድር፣ የምትኖር" በማለት ይፈታዋል። ከዚህ የመዝገበ ቃላት ትርጉም የምንረዳው ነገር አለ። ይኼውም የቃሉ ትርጉም በታሪካዊ ሂደቱ ከዝሙት ተግባር ጋር ምንም ግንኙት ያልነበረው መሆኑን ነው። የ"ሴተኛ አዳሪ" የመጀመሪያ ትርጉም "መበለት" "ባል አልባ" የሆነች ብቻዋን ያለባል በመኖር ራሷን የምታስተዳድር ሴት መሆኗን የሚጠቁም ፍች የያዘ ነው። ሴቷ ባል(ወንድ) ላይኖራት ብቻዋን እየኖረች ራስዋን በተለያዩ ሥራዎች ብዙውን ጊዜ የ"መሸታ" (ጠላና ጠጅ

በመንገድ) ሥራ ለራሷ ፈጥራ የምትኖር ናት። የቃል ትርጉም በታሪክ ጉዞ ዘመን ይለወጣል። በመሆኑም ከላይ የተገለፀው "ሴተኛ አዳሪ" የሚለው ቃል የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም ያዘጋጀው የአማርኛ መዘገበ ቃላት ሌላ ትርጉም ሰጥቶት እናገኛለን። ይኸውም ሴተኛ አዳሪን "በሽርመጥና የምትተዳደር ሴት፣ ሸርመጣ" (ገፅ፣ 134) በማለት ይተረጉመዋል። በመጀመሪያ ባየነው መዝገበ ቃላት የነበረው ፍች ተለውጦ በዚኽኛው ላይ የተለየ ፍች መያዙን እንገነዘባለን። የዚህ ለውጥ ምክንያቱ ቃሉ በጊዜ ሂደት ትርጉሙን የለወጠ መሆኑን የሚያስረግጥ ነው። በጊዜ ሂደት "ሴተኛ አዳሪ" የሚለው የደስታ ተክሌ ወልድ መዝገበ ቃላዊ ፍች ተለውጦ በገጽ 1100 ላይ "ቅሬ" ብለው ለሚጠሩት የቃል ትርጉም "ሴተኛ አዳሪ" በማለት ለፈቱት ቃል ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን። "ቅሬ" ማለት "አጠሪ ዘፋኝ" አርኽ፣... ጋለሞታ፣ ሴተኛ አዳሪ፣ ሸርመጣ"... ወዘተ. በማለት ይፈቱታል። ከዚህ ልንረዳው የምንችለው ነገር ዛሬ "ሴተኛ አዳሪ" የሚለውን ቃል በምንረዳው መልኩ የድሮው ተመሳሳይ ቃሉ "ቅሬ" የሚል እንደነበር ሲሆን በቀጥታ "ሴተኛ አዳሪ" የሚለው ቃል ግን ትርጉሙ የዛሬው ተመሳሳይ ትርጉም "ሸርመጣ" የሚለው ከገመቱት ጋር ግንኙነት ያለው አለመሆኑን ነው። ነገር ግን በደስታ ተክለ ወልድ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት አተረጓጎም የዛሬው "ሴተኛ አዳሪ" የሚለው የቃል ትርጉም አቻ ትርጉም የድሮው "ቅሬ" የሚለው ነው ለማለት ያስደፍራል። ምክንያቱም ለ"ቅሬ" የተሰጠው ፍች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም ያወጣው መዝገበ ቃላትም የሰጠው ትርጉም ደስታ ጋር ተመሳሳይ ነው። ደስታ "ሴተኛ አዳሪ" ብለው ለሚጠሩት ቃል የሰጡት ቃል "ባል አልባ" "ብቻዋን የምታድር"፣ ወዘተ. ይበሉ እንጂ "ቅሬ" የሚለውን ሲተረጉሙ ግን "ሴተኛ አዳሪ" "ሸርመጣ" በማለት ትርጉማቸውን አብራርተዋል። ስለዚህ ከዚህ የምንረዳው ከፍ ሲልም "በሴተኛ አዳሪነት ታሪካዊ ዳራ" ላይም እንደተብራራው ብቻዋን የተለያዩ ሥራዎችን ፈጥራ ትኖር የነበረችው "ባል አልባ" ሴት የተፈጥሮ ግዳጇ አስገድዷትም ይሁን ነሮዋን ለመደገም ወይ ልቧ ከፈቀደው አለዛም ከሥራ ውጤታ ተጠቃሚ ወንድ ጋር "መቅበጥ" "መወዳጀታ" አይቀሬ ስለነበር የመጀመሪያ የ"መበለት" ቃል ትርጉም ቀስ በቀስ በደስታ አተረጓጎም ወደ "ቅሬነት" በዘመናዊ ፍቺው ወደ "ሴተኛ አዳሪነት" መለወጡ አይቀሬ እየሆነ ለመምጣቱ አመላካች ነው። ለዚህም ይመስላል "መበለት" ብለው የተረጎሙትን የ"ሴተኛ አዳሪ" ፍች ለ"ቅሬ" ለሚለው ማንዘራሽ፣ መሸተኛ፣ አቅራሪ፣ ጋለሞታ፣ ... ሸርመጣ ብለው ለተረጎሙት ቃል "ሴተኛ አዳሪ" በማለትም አክለው ፍች መስጠታቸው።

ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

ከሁለቱ መዝገበ ቃላት የምንረዳው ጉዳይ "ሴተኛ አዳሪ" የሚለው ቃል "ሸርመጣ" ማለት መሆኑን ነው። "ሸርመጣ" የሚለው ቃል የአረብኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙም "ገላዋን ለገንዘብ በመለወጥ ወይም በማከራየት የእለት እንጀራዋን የምታገኝ ሴት" (እናነ አጐናፍር ገፅ፣ 7) መሆኗን ትገልፃለች። በመሆኑም የሸርመጥና ተግባር ከዝመት ጋር የተያያዘ ሲሆን ቃሉም ድርጊቱ ነውር በባህል የማይደገፍ ተግባር ለመሆኑ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት "ነውር ጌጧ" በማለት ይፈታዋል። ስለዚህ "ሸርመጣ" የሚለው ቃል ነውርነትን የሚገልፅ ቃል ነው። ለምን ከዝመት ተግባር ጋር የተያያዘ ስለሆነ እና ዘማዊነት ደግሞ በባህሉ የማይፈቀድ ነውር ነው ተብሎ በባህል የተከለከለ ድርጊት ነውና። ይህ ቃል በጊዜ ሂደት "ከሴተኛ አዳሪነት" ጋር የተያያዘ በመሆኑ ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸው መስለው ይታያሉ። ነገር ግን "ዝመት አዳሪ" እና ሴተኛ አዳሪ" የሚሉት ቃላት በታሪካዊ የቃሎቹ አመጣጥ ላይ ስንመለከት የተለያዩ መሆናቸውን እንረዳለን። "ሴተኛ አዳሪ" የሚለው ቃል ሰዎቹን የሚገልፅ ገላጭ ቃል ነው። በታሪካዊ ሂደቱ ከዝመት ጋር ያልተያያዘ ስመሆኑ ከዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት በተገለጸው "መበለት"፣ "ባል አልባ" "ብቻዋን የምታድር፣ የምትኖር" የሚለው ፍች ጠቋሚ ነው። የዚህም ልዩ አንድምታ ደግሞ "በዓለ ቤት/ባለቤት/ወንድ/ባል" ሳይኖራት ብቻዋን እየኖረች ራስዋን የምታስተዳድር ብዙውን ጊዜ ደግሞ "መሸታ" የምንለውን ሥራ ለራሱዋ ፈጥራ የምትኖር ሴት ማለት ነው። የቃል ትርጉም በጊዜ ሂደት ይለዋወጣል። "ዝመት" የሚለው ቃል የሕገን እንኳ ትቶን፣ በሃይማኖት በምግባሩ ረገድ ካየነው "ነውርነትን" የሚገልጽ ስለሆነ "ገላጭ" (ዲስክሪፕቲቭ) ሳይሆን "ዳኚ" "ከልካይ" "አነዋሪ" (judgmental or condemnatory) ነው። ስለሆነም ሁለቱ ቃሎች ትርጉማቸው የተለያየ ነው። የሁለቱን ቃሎች ትርጉም መለያየት ከዚህ ላይ ያነሳሁት በክለሳ ድርሳኔ ውስጥ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትን ላይ "የዝመት አዳሪነት" የሚል ቃል ያለበትንም የጥናታዊ ወረቀቶችን ሥራ ከኔ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳሳይነትና ልዩነት እያልኩ ስጽፍ ስለነበር ሁለቱ ቃሎች (ሴተኛ አዳሪነትና ዝመት አዳሪነት) በትርጉም አንድ ወጥ የሆነ አቻ ፍች አላቸው የሚል የተሳሳተ ግምት አንባቢ እንዳይወስድ በማሰብ ነው።

በዚህ ጥናታዊ ወረቀት ሴተኛ አዳሪ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እና ምን ምን ተግባሮችን የሚያከናወኑ ሴቶች ናቸው ሴተኛ አዳሪ የሚለውን ትርጉም የሚሰጣቸው የሚለውን በማየት አንድ ቁርጥ ያለ ብያኔ ለመስጠት የሚከተሉትን ምሁራዊ ብያኔዎች በቅድሚያ ማየቱ ተገቢነት ያለው ይመስለኛል።

ሴተኛ አዳሪነት የሚለው ሃረግ አንዲት ሴት ገንዘብ ወይም የተለየ ጥቅም ለማግኘት ሰውነቷን (አካሏን) ለፈቃደ ሥጋ ግንኙነት አሳልፋ የምትሰጥበትን ተግባር ያመለክታል። በዚህ የማህበራዊ ገፅታ ሴቷ እንደ መተዳደሪያ ወይም እንደመሥ ከተዳደረችበት ማህበረሰቡ በሴተኛ አዳሪነት ይፈርጃታል። ይህንን የሴተኛ አዳሪነትን ጽንሰ ሀሳብ ቦንገር እንዲህ በማለት ይገልጹታል። "ሴተኛ አዳሪነት ማለት አንዱ የማህበራዊ እውነታ ሆኖ ሴቶች አካላቸውን ለወሲብ ተግባር አሳልፈው ሲሸጡና እንደመተዳደሪያ ሲጠቀሙበት ነው (Bonger, 1964፡ 324)።" ስለዚህ ለሴቶች ሴተኛ አዳሪነት ገንዘብ ለማግኘት የሚረዳ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ድርጊት ነው ማለት ነው። የዚህን የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሁኔታ በተመለከተ ኢሊየትና ኢ. ማርት የተባሉ የማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪዎች ሲያብራሩ

> ሴተኛ አዳሪነት ማለት ልቅ የሆነ ለገንዘብ ማግኛ የሚረዳና ሁለት በስሜት የተለያዩ ሰዎች የሚያደርጉት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የፈቃደ ስጋ ግንኙነት ድርጊት ነው። ይህንን ስንል ግን በፈቃደኝነት ላይ ተመስርተው የግብረስጋ ግንኙነት እንደሚያደርጉት ፍቅረኛሞች ፍቅርና መተሳሰብ እንዳልሆነም ልናውቀው ይገባል (Elliot, 1956:155)። (አፅንኦቱ የኔ)

ልቅ የሆነ ሲባል ከብዙ ሰዎች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀምን የሚያመለክት ነው። በዚህ ገደብ በሌለው የዝሙት ተግባር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አንዲት ሴት ከተሰማራች እና ለነሮዋ የሚያስፈልጋትን ገቢ በሙሉ ወይም በብዛት የምታገኘው ይህንን በመተግበር ከሆነ ሴተኛ አዳሪ የሚለው መጠሪያ ሊሰጣት እንደሚችል ንጉሴ ተፈራና አለማየሁ ፀጋዬ (1975፣ 91) በሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተጠናውን ጥናት መሰረት አድርገው የሚከተለውን ይጠቅሳሉ።

> ዝሙት አዳሪ[3] ማለት ለጥቅም ወይም ለገንዘብ ስትል በዝሙት አዳሪነት ተግባር ላይ የምትገኝ ወይም የምትተዳደር ማለት ሲሆን ተጠቃሽዋ ለነሮዋ የሚያስፈልጋትን ገቢ በሙሉ ወይም አብዛኛውን የምታገኘው የዝሙት ተግባር በመፈፀም የሆነ እንደሆነ ነው (ንጉሴና አለማየሁ፣ 1975)።

[3] ዝሙት አዳሪ የሚለው ቃል በዚህ አውድ /context/ ሴተኛ አዳሪ የሚለውን ገላጭ ቃል ፍች የያዘ ነው። የሴቶችን ተግባር ለመግለፅ የገባ ሲሆን አካላቸውን ለገንዘብ ሲሉ ለወሲብ ፊላጊ ወንድ የሚያቀርቡ ወይም የሚቀርቡ የሚለውን ትርጉም የያዘ እንጂ ከላይ ሁለቱ ቃሎች በትርጉም ይለያያሉ የሚለውን አባባል የሚቃረን እንዳልሆነ ይታወቅ።

ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

አንዲት ሴት ከፍቅረኛዋ ወይም ከቋሚ ወዳጇ ሌላ ገንዘብም ሆነ ሌላ ጥቅም ለማግኘት ብላ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ተግባር ከፈፀመች በሴተኛ አዳሪነት ለያስፈርጃት እንደሚችል "ኢንሳይክሎፒዲያ ብርታኒካ" ቅጽ 9፣ 1993፣ 737" እንደሚከተለው ይገልፃል።

> Prostitution - the practice of engaging in relatively indiscriminate sexual activity, in general with individuals other than a spouse or friend, in exchange for immediate payment in money or other variables.

ስለዚህ ከላይ ካየናቸው የተለያዩ ብያኔዎች በመነሳት ሴተኛ አዳሪነት አንዲት ሴት ለኑሮዋ ወይም ለመተዳደሪያዋ የሚያስፈልጋትን ገንዘብ ለማግኘት ስትል ቁጥራቸው ካልተወሰነ ወንዶች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የምትፈጽምበት ተግባር ነው። ሴተኛ አዳሪነት "ሙያ" ወይም "ሥራ" ነው ለማለት ይቻላል። ይህንን "ሙያ" የምትሰራው ሴት "ሴት አዳሪ" የሚል መጠሪያ ሊሰጣትም እንደሚችል ጥርጥር የለውም። ነገር ግን እነዚህ "የፈረደባቸው" ሴቶች "ሴት አዳሪ" በሚለው ስያሜ ብቻ የሚጠሩ አልሆነም። በርካታ ስያሜ አላቸው። ለዚህ ጥናት ከተመረጡት መጻህፍት መካከል በተለይ አንዱ <u>መጎልየ መጎልይ ዘካዛንችስ</u> ውስጥ የእነዚህ ሴተኛ አዳሪዎች መጠሪያ ብዙ ነው።፡ "ደንበኞቻቸው" በተለያየ ሁኔታ ለተለያየ ምክንያት ለተለያየ ሙያ የሚጠሩበት የሴቶቹ ስም ብዙ ነው። ስለሆነም የተወሰኑትን በመምዘዝ በምን ሁኔታ፣ ለምን ምክንያት፣ ለምንስ ሙያ እያቀያየሩ እንደሚጠሯቸው እንመልከት።

> ... ህብረተሰቡ በውስጠ ወይራ "<u>የቡና ቤት ሴት</u>" ሲላቸው፣ ካዛንችስና መሰሎቹ ግን ... "<u>ሽሌ</u>"፣ "<u>ሴተኛ አዳሪ</u>"፣ "<u>ሽርሙጣ</u>" ... ዘመናዊው ደግሞ "<u>ባርሌዲ</u>" የሚላቸው። (ገፅ፣ 4)

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት ለሴተኛ አዳሪ ሴቶች የተሰጣቸው ልዩ ልዩ ስም ነው። ካዛንችስ የሚመጣው ወንድ "ተሸራሚጭ" ለሴተኛ አዳሪዋ ያወጣላት የተለያዩ ስያሜዎች ናቸው። በአንድ መጠሪያ ብቻ ተወስና የምትቀር ሳትሆን ወንዱ "ተሸራሚጭ" ደስ እንዳለው እየለዋወጠ በተጠቀሱት ስሞች ሊጠራት ይችላል። ሴተኛአዳሪዋም መጠሪያ ስሜ አይደለም አትልም። የስሟ መብዛት ውስጧን ቢያቃጥላትም

የሚለጥፍላትን የስም "ታርጋ" ከመቀበል ውጭ የምታመጣው ለውጥ የለም። እነዚህ ስያሜዎች አጠቃላይ የሆኑ ውስጣቸው ንቀትን ያዘሉ ለሴተኛ አዳሪዋ ተለይተው የተሰጡ የመጠሪያ ስያሜዎች ናቸው። ህብረተሰቡ በውስጠ ወይራ በተፈጥሮ እና በህግ መብት የተሰጣቸውን "ሴት" የሚለውን መጠሪያቸውን "ተከታይ" አድርገው የተለያየ ስያሜ ይለጥፉባቸዋል። ገላቸውን ለሽያጭ ማቅረባቸው ሳያንስ የስማቸው መብዛት ራሱ የሚያመለክተው የሰብኣዊነታቸውን መንጠፍ ፈረጀ ብዙነት አመላካች ሁነት ነው። እነዚህ ስመ ብዙ ሴተኛ አዳሪዎች ገላቸውን "ለግር" ሲያቀርቡ ገገርያቸው ወንድ "ተሸራሚጭ" ልክ እንደ "መ.ያ" መጠሪያቸው ስመ ብዙነት ለአካላዊ ብልታቸውም የተለያየ ስያሜ ሰጥተዋቸዋል። ደረጃም መደበውላቸዋል። ይህም "ለመ.ያቸው" ልዩ ልዩ መጠሪያ እንደሰጡዋቸው ሁሉ ለ "ብልታቸውም" "የጥራት ደረጃ" አውጥተውላቸዋል። እነዚህ የፈረደባቸው "ሴቶች" ወንዱ "ተሸራሚጭ" ለወሲብ ሲመርጣቸው በወጣላቸው "የጥራት ደረጃ" መሠረት እና ዓይነት ነው። ለአብነት ያህል ከመጽሐፉ ልጥቀስ

ታጥቦ የተቀሸረ አንደኛ ደረጃ የሲዳሞ [4]"እንትን"
ያልታጠበና ያልተፈለፈለ ሰባተኛ ደረጃ የሲዳሞ "እንትን"
ይልተፈለፈለ አንደኛ ደረጃ የሰላሌ "እንትን"
ተፈልፍሎ የታጠነ ሁለተኛ ደረጃ የጎንደር "እንትን"
ታጥቦ ያልተፈለፈለ ባለአንቱና የገኛም
ሁለተኛ ደረጃ "እንትን" ... የተቀባ፣
የተሞሸረና ለስልሶ የተቆላ አንደኛ ደረጃ
የአዲስ አበባ "እንትን" ... ተለቅሞና
ተቀሸሮ የተቆነደደ ሁለተኛ ደረጃ
የትግራይ "እንትን" ... ታጥቦ የተቆላና
የተፈጨ አራተኛ ደረጃ የድሬ "እንትን"
... ታምሶ የተቀሸረ አንደኛ ደረጃ የወለጋ
"እንትን" ... (ገፅ 28-29)

[4] "እንትን" የሚለው መዘክር ተውላጠ ስም የሚወክለው የሴቶችን የብልት ስም ነው። ከመጽሐፉ በግልፅ በስመ. ይጠራል። እዚህ ላይ ግን በ "ባህሉ" በግልጽ ስለማይጠራ ለማለዘብ ስል መዘክር ተውላጠ ስሙን "እቶትንን" ተጠቅሚያለሁ።

የካዛንችሱ ወንድ “ተሸራሚጭ” ለሴተኛ አዳሪዋ የሚያወጣላት ልዩ ልዩ ስያሜ ብቻ ሳይሆን “... በቁመት-በስፋት፣ በመጠን-በልክ-በወርድ-በእምነት-በባህል-በብሔር-በጎጥ-በአመለካከት-በአሰጣጥ አይነት ... (ገፅ፣ 28) ሁሉ ስያሜ እና ደረጃ ያወጣላታል። የሴተኛ አዳሪዋ ስም “በሽ ነው”፣ “ነፍ”። (ገፅ፣ 29) ይህ ሁሉ ስመ ብዙነት የሚጠቁመው የሴተኛአዳሪዋን የሰብአዊነት መንጠፍ ምን ያህል መጠነ ሰፊ እንደሆነና ፈረጀ ብዙ እንደሆነ ነው። ይህች “ገላዋን” ለገንዘብ ስትል ለማሻ የምታቀርበው ሴተኛ አዳሪ አንድ “ገላዋን” (ብልቷን) ቢሆንም እንደብዙ የሸቀጥ ዓይነት ተቆጥሮ ስያሜው በዝቷል። መጠሪያው በርክቷል። ደረጃም ወጥቶለታል። ስለዚህ ሴተኛ አዳሪ ማለት “ገላዋን” ለገንዘብ ስትል “ለችርቻሮ የምታቀርብ “ዘመናዊ ባርያ” ናት ለማለት ይቻላል። እንደ ጥንቱ የባርያ ንግድ በሌላ ሰው ታፍና ለገበያ ባትቀርብም በዘመናዊነት “ነፃነት” በልዩ ልዩ ችግሮችና ምክንያቶች በራሷ ፈቃድ “ለነፃነት-ባርነት” የተዳረገች “ሴት” ናት ለማለት ያስደፍራል።

ምዕራፍ ሶስት

3. የሴተኛ አዳሪ የሰብኣዊነት መንጠፍ

ዐራዳ ለኪራይ ቤት የፈለጋችኹ
ዘማለች ምናልባት በውል እያያችሁ።
ደስታ ተክለወልድ

መግቢያ

ይህን የኢትዮጵያ ታላቅ ሰው ቅኔ የጽሑፌ መነሻ ያደረግሁት ከላይ በርዕስነት ያቀረብኩትን ጉዳይ ያጠናክርልኛል ከሚል እምነት ነው። የሴተኛ አዳሪን "የሰብእና መንጠፍ" ቁምነገር፣ መጠንና ልክ ለማስተንተን በጭብጥነት እንደአብነት የሚመዘዙ ሀሳቦች ከመረጥኳቸው ሶስት ድርሰቶች ውስጥ ሊቁ በቅኔያቸው የተናገሩትን ቁምነገሮች ይዘው ይገኛሉ የሚል እምነት ይገፎ በመነሳቱ ነው። የተመረጡት ሶስት የስነጽሑፍ ሥራዎች <u>ሴተኛ አዳሪ</u>፣ <u>ሌቱም አይነጋልኝ</u> እና <u>መጎልየ መጎልይ ዘካዛንችስ</u> ናቸው። ስነጽሑፎቹ በውስጣቸው ያዘሉትን ፍሬ ሀሳብ ሳስተነትን በተናጠል እያንዳንዳቸውን እንደየዘመን መንፈሳቸው፣ እንዲሁም በማዳበል በሚያስተላልፉት አጠቃላይ ጭብጥ መሠረት ይሆናል። ስነጽሑፎቹ የሴተኛ አዳሪን የሰብእና መንጠፍ መጠንና ልክ ያቀረቡበት ስልት አንድ አይነት አይደለም። የየራሳቸው ስልት ያላቸው ሲሆን በሀሳብ ረገድ የተለያየ አመለካከትም ይዘው የሚገኙ ናቸው። በመሆኑም እንደየልዩነታቸው ስልት ለየብቻ፣ እንደተመሳሰይነታቸው ደግሞ በጋራ የሚተነተኑበት መንገድ በዚህ ሥራ ውስጥ ይታያል።

በልማዱ አንድን ስነጽሑፍ ስናነብና አስተያየትም ሆነ ትችት ስንሰጥበት በጭብጡ ይዘት ላይ፣ ወይ በቅርጽ እና አወቃቀሩ ላይ በመመርኮዝ በነዚህ በሁለቱ ቁምነገሮች ላይ የጠለቀ ትንታኔ እንሰጥበታለን፣ ካልሆነም ከዚህ ሁሉ ጣጣ ምን ዶለኝ በማለት እንደወረደ ተቀብለን እንደየአዕምሮ ክበብ አድማስ ስፋትና ጥበታችን አስተያየታችንን እንሰጥበታለን። "ምርጫዎቻችን ግን" ዮናስ እንዳሉት "በዘፈቀደ እጣ ጥሎ ይህን ይጎርሀ የሚያስብሉ ሳይሆኑ በአንባቢዎች መጠነ ርእይና ዝንባሌ፣ አንዳንዴም በወቅታዊ ፍላጐት የሚወሰኑ ናቸው (1992፣77)።" በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት ሶስት የስነጽሑፍ ሥራዎች ላይ ጐልተው የወጡ ወይም ፊት ለፊት የተባሉና ያልተባሉትን ሀሳቦች ፈልፍሎ በማውጣት

ከተራኪው፣ ከገፀባህርያቱና ከሁኔታው ጋር የሀሳብ ክርክር ይደረጋል። የሀሳብ ክርክሩም በግልቡ ሳይሆን "ፈርሱን" ገልብጦ በመተርጎምና በመፈክር ነው። ፍካሬውም በምዕራፉ መግቢያ አናት ላይ ሊቀ ሰዋስው ደስታ ተክለወልድ በዘረፉት ቅኔ "ዐራዳ ለኪራይ ቤት የፈለጋችኹ/ዘማለች ምናልባት በውል እያያችሁ" እንዳሉት የሴተኛ አዳሪዎችን ሰብእና ትብያ መልበስ፣ ሰው ሆነው ተፈጥረው በሚያራምዱት የሕይወት መስመር ሳቢያ እንደ "ቁስ" መቆጠር ለማሳየትና ለማስተንተን ነው። ይህንንም የ "ሰብእና መንጠፍ" ሊያሳሉና ሊያሳዩ ይችላሉ ያልኩዋቸውን ጭብጦች ከተመረጡት ስነጽሑፎች በመምዘዝ ለማሳየት ስሞክር ነቃሾቼ ደራሲዎቹ፣ የታሪኩ አራማጆች ራሳቸው ገጸባህርያቱ እና ዘመነ ይሆኑኛል በማለት ነው። እንደምን ቢሉ? ደራሲው የድርሰቱን ጥሬሀብት የሚያገኘው ከማህበረሰቡ ነውና፤ ገጸባህሪያቱስ ቢሉ? የደራሲው ፉጡራን በመሆናቸው "ተቀመጡ በወንበሬ፣ ተናገሩ በክንፈሬ" ያላቸው አፈቀላጤዎቹ ናቸውና። ዘመኑስ ቢሉ? የድርጊቶች ሰንሰለታዊ ጉዞ እንደፈሳሽ ውሃ ሰትት ብለው የሚጓዙት በአገዛማናት ውስጥ በመሆኑ ታሪኮች የሚከናወኑት በጊዜ ቅደም ተከተል ነውና። እነዚህ ዋቢ ጠበቆቼ ይሆናሉ የሚል እምነት ስላለኝ ነው። ይህንንም እምነቴን ከግብ ለማድረስ

> ልብ ወለድን ማንበብ ማለት በፊት ለፊት ከተነገረን ጀርባ ያለውን ትርጉምና አንድምታ (meaning and significance) ፈልፍሎ ማውጣት ማለት ነው። ይህንን ተግባር ፍካሬ (interpretation) እለዋለሁ። የፍካሬ ወይም የትርጓሜ ነገር ዓላማው ምስጢሩን ከተለያየ አቅጣጫ በተለያየ ደረጃ በተለያየ አፈታት ፈልፍሎ ምስጢሩ እንደምን ሆኖ ሥጋ እንደለበሰ (ወይም በዘመኑ ፈሊጥ ቅርፅ እንደያዘ) አይቶ ማሳየት ነው
>
> (ዮናስ፣ 1992፣ 78-79)።

እንዳሉት አንድምታውን አጥብቀን በመጠየቅ ቁምነገሩን ከስሩ መፈለጋችን የምስጢሩን "ፈለግ" ከአንድ በላይ ሊሆን መቻሉን ማሳየታችን ነው።

እኔም ይህንን ስልት ተከትዬ ስሠራ በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ የሊቁን ቅኔ "ዐራዳ ለኪራይ ቤት የፈለጋችሁ" እና "ዘማለች ምናልባት በውል እያያችሁ" የሚሉት ስንኞች ግልብ ነገር ግን ጥልቅ የሆኑ እውነታዎች ምፀት የመሰሉ ትንቢት አከል አመለካከቶችን ከተመረጡት ሶስት የድርሰት ሥራዎች ለማስተንተን ነው። የነዚህ ድርሰቶች ምፀታዊ ጠቅላላ ምስጢር እንደየስነፅሑፎቹ መድበል ለየቅል ነው።

ዐቢይ መንደርደሪያየ ድርሰቶቹ በሰበካው ከሚነግሩን ወይም ከሚነበቡን ውጭና ጀርባ ያልበሰሉ የሚመስሉ ጥሬ ቃላት አማካይነት የታጀቡ በምፀት የታመቁ የነገረ ሰብ ጣጣዎች እናገኛለን የሚል ነው። ይህን የነገረ ሰብ "ጣጣ" በሶስቱ ስነጽሑፎች ውስጥ በአንድ ዓይነት የሀሳብ ፍሰት የአመለካከት ትኩረት በተመሳሳይ ስልት አናገኘውም። ስለሆነም ደራሲያኑ ካተኮሩበት ሁነት አንፃር በመጽሓፎቹ (texts) ውስጥ ከተገለጹት ሀሳቦች በመነሳት ከዘመኑ መንፈስ (spirit) አኳያ ትንታኔ አክል የሀሳብ ክርክር ይገጠማል። የሀሳብ ክርክሩንም በየስነጽሑፎቹ ውስጥ ተሰግስገው በሚገኙ "አይመስሌ" ወይም እንደ ዋሣ ጣል የተደረጉ ቃላትን፣ ሐረጎችንና አባባሎችን በፍካሬ በማምጣት የሴቲኛ አዳሪዎችን የሰብአና መንጠፍ ከማህበራዊ፣ ከኢኮኖሚያዊ፣ ከፖለቲካዊ እና ከልማዳዊ አስተሳሰቦችና አመለካከቶች አንፃር አጉልቶ ለማሳየት ይጣራል። ይህም ሲደረግ ሶስቱን ድርሰቶች ለየብቻ በመውሰድ የፍካሬ ትንታኔው ይሰጣል።

3.1 ሴቲኛአዳሪ

<u>ሴቲኛአዳሪ</u> የተሰኘው ልቦለድ በ1956 ዓ.ም. እናኑ አጐናፍር በሚል የብዕር ስም የተደረሰ ነው። መጽሐፉም ሲነበብ ብዙም ያልተወሳሰበና እንደ ጋዜጣ ጽሑፍ ፊት ለፊት የሆነ አንብቦ ለመረዳትም ብዙም የማያስቸግር ድርሰት ነው። ድርሰቱ ስለምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ቢነሳ መልሱ የሚገኘው ተራኪዋ ስለማህበረሰቡ አቋም "የበሽታውን ስሜት ሕመምተኛው መናገሩ ቀርቶ አስታማሚው እንደሚናገር ሆኖ ስላገኘሁትና እኔ በዚሁ ሽርመጥና በተባለው ተግባር ከተሰማሩት ሴቶች አንዷ በመሆኔ ... ሐሳቤን፣ ስሜቴንና የጠራቀምኩትን የነሮ ኤክስፒሪያንስ ... በወረቀት ላይ ማስፈር ጀመርኩ (ገጽ፣ 7-8)" ገማለት በምትሰጠው ዲስኩር ላይ የተመሰረተ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም።

ድርሰቱ ሴትነትን፣ ሴቲኛ አዳሪነትንና እናትነትን ከፍ ብሎም የማህበረሰቡ የነሮ ሥርዓት ባህል ጭንብሉ ተገፎ የታየበት ነው። የተነሳው ማህበራዊ ችግር አርባ ሁለት ንመታት ቢያስቆጥርም ዐደቱ ዛሬም የሕይወታችን አንድ ክፍል ነው። ትላንት እናኑ እና ነብሀት ገብረእግዚአብሔር ባሉበት ዘመን የተተረከው እና የተመዘዘው የሕይወት ክር እጅግ ወፍሮ እጅግ ረዝሞ ከዛሬ መድረሱን በተድባበ ጥላሁን <u>መንልየ መንልይ ዘካዛንችስ</u> መገለጡን ለማየት ተችሏል። ሶስቱም የሚያነሱት የሴትነት፣ የእናትነት፣ የማንነት ጥያቄ

በሴተኛ አዳሪዎች ብሶትና መከራ እና በወንዶቹ "ሽርሙጦች" ግብዝነት፣ መታበይ፣ አስመሳይነትና አታላይነት በትክክል ተንጸባርቋል ለማለት ይቻላል።

በእናኑ፣ በስብሃት እና በተድባበ የተነሳው "የማህበረሰብ ቅብጠት" እና የሚታው ልዩነት ምላጭ አያሳልፍም። ትላንት ውቤ በረሀና ገዳም ሰፈር የነበረው "ሽርሙጥና" ዛሬ ካዛንችስ ገብቷል። እናኑ ቀደም ብላ እንደገለፀችው፡-

> የሴተኛ አዳሪዎችን ቁጥር ለመቀነስ የሚቻለው የአስተዳደጋችንና የቤተሰብ ኑሩዋችን የሚጠነክርበትና የሚሻሻልበት ዘዴ የተገኘ እንደሆነ ነው። ጋብቻችን እንዲጸና፣ የልጆቻችን ትምህርትና አስተዳደግ የተሟላ እንዲሆን፣ ወላጆች፣ መምህራንና የቤተክርስቲያን መሪዎች ተባብረው ለዚህ ለሶሺያል ፕሮብሌም መፍትሔውን ካላገኙ በስተቀር፣ የሽርሙጥና ተግባር እየባሰ መሄዱ አይጠረጠርም (ገፅ፣ 77-78)።

የየዕለት ዑደቱ ተመሳሳይ፣ የየዘመኑን የወንድና የሴት "ሽርሙጥና" አግዝፎ የሳለ እና ሥጋ ለብሶ ነፍስ ነስቶ የታየበት እውነታ ነው። ሁሉም ለየበቀሉበትና ለየሚኖሩበት ዘመን ማህበረሰብ አብሮት የሚኖረውን ሀቅ በማግዘፍ ያለበትን ቦታና መልክ በትልቁ እንዲታይ አድርገዋል። በዚህ ላይ "የመሸራሞጡ" አይነት ከዖታ ጀምሮ እንደየአሻራችን መለያየቱን ፊት ለፊት ነግረውናል። "መሸራሞጡ" የሴቱም የወንዱም የጋራ ሆኖ ሳለ ሙያዊ መጠሪያው ለሴቶች ብቻ መሰጠቱን "የለም" ያሉን ፀሐፍት፣ የራሳችንን ሥራ ራሳችን የምንፀየፍ፣ እውነትና ክብራችን በቀን ብርሃን እውን መሆኑን ታዝበው ነግረውናል። "ሰው መሳይ በሽንገሎ" የሚለው የእናኑ ትዝብት ለዚህ ትልቅ ምስክር ነው።

በመግቢያው ላይ ስሟን ለመግለጽም ሆነ የረዷትን በስም ጠቅሳ ለማመስገን ያልደፈረችበትን ሁኔቴ ወስደን ብናጤን ከላይ የተገለጸውን አባባል ያጠናክረዋል። ማህበረሰቡ የሴተኛ አዳሪን የሕይወት መስመር በግልፅ ቢኮንንም፣ ድርጊቱን አውግዞ ሲተወውና ከተግባራዊ ተሳትፎ ራሱን ሲያቅብ አይታይም። እናኑ በትረካዋ የማህበረሰቡን ማንነት ትሁት በሆነ ምፀታዊ አገላለጽ እንዲህ ስትል ትገልጸዋለች (ገፅ፣ 5-6)።

እናኑ አገኖፍር የተባለው ልብወለድ ስም የብዕር ስሜ ነው። መጠሪያ ስሜን ገልጨ ያልባፍኩበት በቂ ምክንያት አለኝ። አንደኛው የእኔ የሕይወት ታሪክ በምግባርና በሞያ ከሚመስሉኝ ሴቶች የተለየ ስላልሆነ፤ የመጽሐፉ መልእክት የሁላችንም የሕይወት ታሪክ እንዲሆን በወል ስም ለማበርከት ነው። ሁለተኛው ምክንያት፤ አስቦና አዙሮ የሚመለከት ፍጡር ሁሉ፤ (ሴተኛአዳሪም ብትሆን) መታማትን፤ መነቀፍንና መሳቂያ መሳለቂያ መሆንን ስለማይፈቅድ፤ እኔም በበኩሌ የሕይወቴን ታሪክ ለአንባብያን አበርክቼ፤ መጠሪያ ስሜን በሆዴ እንድይዘው ይኸው አመዛዝኖ የመተው ስሜት አስገድዶኛል (አጽንኡቱ የኔ ነው)።

ይህችን ጥቅስ መነሻ አድርገን ነገሩን ከስሩ ስንመለከተው እውነትም ሰው ራሱ ለፈጠረው ሥርዓት (ወግ፤ ልማድ፤ ባህል ለማለት ነው) አስረኛ መሆን ማለት ይኼው ነው። ወግና ልማድን ሰው በጊዜ ሂደት ከፈጠረው በኋላ ለዚሁ ባህል ተገዥ ይሆናል። በዚሁም ደንብና ሥርዓት ይገዛል። ባህል ሰዎች ሊፈጥሩት የሚችሉት ነው። ሰዎች ለማደግ፤ ለመለወጥና ለመሻሻል በሚያደርጉት ያልተቋረጠ ጥረት በየጊዜው የሚፈጥሯቸው ማናቸውም እንቅስቃሴዎች ሁሉ ተጠቃለው ባህላቸውን ይሆናሉ ለማለት ይቻላል። ይህን አስመልክተው ሀይለገብርኤል ዳኜ የሚከተለውን ብለዋል።

> ሰዎች በሰፊም ሆነ በጠባብ ማህበራዊ ኑሮ ተሳስረው በሚገኙበት ሥፍራ ሁሉ ሌሎችም አስፈላጊ ድርጊቶች ይፈጠራሉ። ለኅዘን፤ ለደስታ፤ ለሃይማኖትና ለሌሎችም የኑሮ ስልቶች ደንብና ሥነሥርዓቶች ይበጁላቸዋል። ይብዙም ይነሱም ከላይ የተጠቀሱት ደንቦችና ድንጋጌዎች በድምሩ ባህል ይባላሉ (1961፤57)።

ባህል ማለት ተፈጥሮአዊ ክስተት ሳይሆን በሰዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚገኝ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሕይወት ነው። ይህ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሕይወት ሰዎች ከፈጠሩት በኋላ በጊዜ ሂደት ፈጣሪው ተመልሶ ሊታሰርበት፤ ሊወገዝበት ይስተዋላል። ሰው የፈጠረው ሥርዓት መልሶ በራሱ ላይ ይሰለጥንበታል። ሰው ተመልሶ መደረግና መደረግ በሌለባቸው ባህላዊ ሥነምግባሮች ራሱን በራሱ ያስገዛና አፈንጋጩን ደንብና ሥርዐት አፍራሽ "ጋጠወጥ"፤ "ስድ"፤ "መረን"፤ ለባህል የማይገዛ፤ "አጉራ ዘለል"፤ ወዘተ. በማለት

ያሸማቅቀዋል። ባህሉንና ሥርዓቱን ጠብቆ የማይጓዘውን በልዩ ልዩ የማህበራዊ ባህላዊ ደንቦች (social traditional codes) አማካይነት ልክ እንዲገባ ያደርገዋል። ይህንን ካልፈጸመ ያወግዘዋል፤ ያገልለዋል። ለዚህም ነው እናነ በመግቢያዋ ላይ ስሟን ለመግለፅም ሆነ የረዷትን በስም ጠቅሳ ለማመስገን መሳቀቅ መሸማቀቋ። የተሰማራችበት "መ.ያ" ማህበረሰቡ ያልተቀበለው በባህሉ ውስጥ አታድርግ ተብሎ የተደነገገው ስለሆነ ራሷም "መሳቂያ መሳለቂያ" ብቻም ባትሆን የጣት መቀሰሪያ ላለመሆን የረዷትንም ሰዎች "ለአንባብያን በማወጅ ለነሱ ሐሜትና ኃፍረት ያስከትልባቸው ይሆን (ገፅ፤ 6)" በማለት ጭንቀትም፤ ምፀትም የተላበሰውን አስተያየቷን የምትሰጠው። ከዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባው ሌላው ጉዳይ "ሴተኛ አዳሪ" መባልና የሴተኛ አዳሪ ሕይወት በማህበረሰቡ አመለካከት የሚያሳፍርና የሚያዋርድ እንደሆነ ነው። ማህበረሰቡ ለነሱ ያለው አመለካከት ንቀት የተመላበት ነው። ለዚህ ነው "መጠሪያ ሰሜን በሆዴ እንድይዘው ይኸው አመዛዘኖ የመተው ስሜት አስገድዶኛል" በማለት የተናገረችው። ይህችን ሐረግ በውል ካጤንናት "አመዛዘኖ የመተው ስሜቱ" ሌላ የሚጠቁመው ነገር ያለ መሆኑን እንድናስብ ያደርገናል። ይኼውም "መጠሪያ ስሟ" ሌላ ስም ያጣቅሳል። በስሟ የሚያፍሩ በድርጊታ "ውስጣቸው የሚጐዳ" የባህል ተገዢዎች አሉ። እነሱም ቤተሰቦቿ። "በመ.ያው" ተሰማርተው ለሚገኙ የሴተኛ አዳሪዎች ቤተሰቦችም የመጨረሻው "ውርደት" ስለሚሆንባቸው በሌሎች የማህበረሰቡ አባላት የተናቁና የተጠሉ ይሆናሉ። መጠቃቀሻ በመሆን በተገኘው የማህበረሰባዊ ማህበራዊ ተራክቦ (social interaction) ሁሉ በነገር ወጋ፤ በአሽሙር ነካ ይደረጋሉ። ይህም ሁኔታ ሴተኛ አዳሪዎችን ሁለት ስለት ባለው ሰይፍ ላይ የወደቁ ፍጡራን ያደርጋቸዋል። የቤተሰብ ውርደት የመጣው በነሱ ምግባር በመሆኑ ከቤተሰባቸው በኩል የሚደርስባቸው መገለል፤ ሁለተኛው ደግሞ አጠቃላይ የማህበረሰቡ ንቀት፤ ማግለልና ከባህል የወጡ ተደርገው መቆጠር ስቃያቸው መብዛቱ ብቻ ሳይሆን ይገቡበት፤ ይጠንበት፤ መሸሸጊያ ጥግ ያጡ "ዛፍ ያጣ ጉሬዛ" (ራሷ ተራኪዋ እንዳለችው) ያደርጋቸዋል። ይህንን የማህበራዊ ወግና የልምድ "ባርነት" ለመላቀቅ ከባርነቱም "ነፃ" ለመውጣት አካባቢ ቢለቁ ሳፈር ቢለውጡ የባሰ እንጂ የተሻለ አያገኙም። ንቀቱ፤ ጥላቻው፤ ውርደቱ ይባስ ሲጎላ ይስተዋላል።ይህንን አስመልክቶ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን እንዲህ ይላል።

... እማማና አባባ እንኳን፡ ካንድ ልቤ ... እኩል የሚያውቁኝ፣
ገበቅ እንዳልኩ ሳልነሳ ተንበርክኬ ሲመርቁኝ፣
እዚያው ተጠቃቅሰው አሙኝ፣
በዓይንና በግንባር ጥቅሻ ከዘመድ አዝማድ ጋር በሉኝ።

(እሳት ወይ አበባ፣ ገጽ፣ 71)

ይህች፥ ከፀጋዬ ገብረመድህን <u>ማነው... "ምንትስ"</u>? ከሚለው የተቀነጨበችው ስንኝ በሴተኛ አዳሪዎች ላይ የሚደርሰው የተዛባ ማህበራዊ አመለካከት ምን ያህል የከፋ እንደሆነ ቁልጭ አድርጋ የምታሳይ ናት። እናነ በትረካዋ ያስቀመጠችውን ሁነት የምታጎላ ተስማሚ ማስረጃ ናት። ሴተኛ አዳሪዎች የሚደርስባቸው ማህበራዊ ውግዘት የሥጋ ዘመዶቻቸው ሳይቀሩ የሚጋሩት መሆኑን አመላካች ናት።

"ሴተኛ አዳሪ ማለት ሸርሙጣ ማለት ነው" በማለት የምትጀምረው እናነ ታሪኳን የምትቀጥለው "ሸርሙጣ የተባለው ቃል ከአረብኛ የተወረሰ ሲሆን፤ ትርጉሙ ገላዋን ለገንዘብ በመለወጥ ወይም በማከራየት የዕለት እንጀራዋን የምታገኝ ሴት ናት (ገፅ፣7)" ትላለች። ሐሳቡ ከሴትነት ጋር የተዳኘ ቢመስልም የወንዱን "ሸርሙጣ" ፍችም አክላ ታብራራለች። "የወንድ ሸርሙጣ ሴሰኛ፣ አመንዝራ ወይም አለሌ እየተባለ ከሴት ወደ ሴት የሚረማመድ ወንደላጤ ወይም ያገባ ሰው ነው (ገፅ፣ 7)" በማለት በሁለቱ ፆታዎች መካከል ያለውን የሸርሙጥነት ልዩነት የሻጭና የገዢ፣ የአከራይና ተከራይ መሆኑን ታስገነዝባለች። ሴቷ ገላዋን ለገንዘብ ብላ ለሽያጭ የምታቀርብ ሲሆን ወንዱ ግን በገንዘቡ የፈለገውን "ገዘቶ" እንደፈለጋት ሊያደርጋት የሚችል መሆኑን ያሳያል። ገንዘቡን ያወጣባትን "የሴትነት ገላ" እንዳሻው እንደፈቀደው ውስጣዊ የስሜት ፍላጉቱን ሊወጣበት ሲችል እሷንም እንደ "ሰብኣዊ ፍጡር" ሳይቆጥር በሴትነት ገላዋ መደሰት መርካት ብቻ ሳይሆን ኢ-ሰብአዊ የሆነ ድርጊትም ሊፈጽምባት እንደሚችል እናነ በተደጋጋሚ ትጠቅሳለች። ሴትነት በተለይም ሴተኛ አዳሪነት እዳ ነው። ሴተኛ አዳሪን ገንዘብ ያለው ሁሉ "ይገዛታል" ወይም "ይከራያታል" እንጂ ሴተኛ አዳሪዋ ገገርዋንና ተከራይዋን የመምረጥ መብት እንኳ የላትም። ገበያ እንደወጣ የቀንድ ወይም የጋማ እንስሳ፣ ዐይኗ፣ ጥርሷ፣ ወገቧ፣ ቂጧ ታይቶና ተገምግሞ ዋጋ ተቆርጦላት ብቻ ወንዱ ወዳዘጋጀው መጠለያ መውሰድ ብቻ ነው ያላት እድል። ራስን መሸጥና ማከራየት አካልን ብቻ አይደለም። ሰውነትን፣ ማንነትን፣ ሴትነትን ጭምር መሆኑ በልዩ ልዩ የጽሑፉ (text) ክፍል ተገልጿል። ተራኪዋን ለጠጅ ቤት

አሻሻጭነት የምትቀጥራት ሴት "ስምሽ ደስ አይልም (ገፅ፣ 13)" የምትላትን መገዘን ብንመለከት ከቀጣሪዋ ግብዝነት በላይ ትርጉም ይሰጣል። ወደ ሴተኛ አዳሪነት በሚደረገው ጉዞ ላይ የማንነት መሸርሸር አሀዱ የሚልበት ነው። ተራኪዋ ስሟን ጠልታው አታውቅም፤ ወደ ሴተኛ አዳሪነት ሕይወት ለመቀላቀል ግን ክብሯን፣ ንጽህናዋን፣ ባህሏን ብቻ ሳይሆን ለዘመናት ወዳው አብራው የኖረችውን ስሟንም ጭምር እንድትፍቅ ያስገድዳታል። በዚህ በቃሽ ሳይላትም ከሰፈር ሰፈር፣ ከቡና ቤት ቡና ቤት ስትዘዋወር እሷነቷንም፣ ስሟንም እየሠራች ታፈርሰዋለች። በፈጠራ ስም ተጠርታ ራስን ከበቀሉበት ማህበረሰብ መሸሸግና ካሉበት ዘመንና ቦታ የሚስማማ አዲስ መጠሪያ ማውጣት <u>በሌቱም አይነጋልኝ</u> ውስጥ ይስተዋላል።

ሴተኛ አዳሪዎች ተሸጡም ተከራዩም የመኖር ተስፋቸው ከድር የቀጠነ በመሆኑ ተመሳሳይ የሕይወት መስመር ተከትለው የሚጓዙ በመሆናቸው የሁሉም ሕይወት አንድ አይነት ዑደት የተከተለ ነው። ይህንን ሁነት የሚያሳይ ሀሳብ ከመጽሐፉ በመጥቀስ ሁኔታውን ላጠናክር፤

> እኛ በነበርንበት በአጠና ሠፈር አምስት ዓይነት ነገሮች ጐን ለጐን ይሸጡ ወይም ይለወጡ ነበር። አንደኛው ጥሬ ሥጋ፣ ሁለተኛው ጠጅ፣ ሶስተኛው ሽርሙጣ፣ አራተኛው መድኃኒት፣ አምስተኛው የመቃብር ሳጥን።
>
> (ገፅ፣ 16-17)

ተራኪዋ የሴተኛ አዳሪዎችን ሕይወት ምን ያህል የዘቀጠ መሆኑን ለማንፀራያ የተጠቀመችባቸውን ቃላት ወስደን በጥልቀት እንመልከተው። "እኛ በነበረንበት በአጠና ሠፈር" በማለት የሠፈሩን ስም በውል ከገለፀች በኋላ አምስት ነገሮች ጐን ለጐን ይሸጡ ወይም ይለወጡ ነበር ብላ "ሽርሙጥናን" ያነሳፀረችው ከጠጅ፣ ከጥሬ ሥጋ፣ ከመድኃኒት እና ከመቃብር ሳጥን ጋር ነው። እነዚህ ቃሎች እንደሚታወቀው የግኡዝ ነገር ስያሜዎች ናቸው። "ሽርሙጣ" የተሰኘው ቃል ግን የሚገልፀው ቀደም ብላ ተራኪዋ እንደገለፀችው የሚወክለው "ሴተኛ አዳሪ" የሚለውን ነው። "ሴተኛ አዳሪ" ማለት ደግሞ በመሠረቱ የምትተዳደረው ገላዋን ሸጣ ቢሆንም ምድቧ ከሰው ነው። ነገር ግን ተራኪዋ "ከነገሮች" ጋር መመደቧ የሚያመላክተው ትልቅ የኢሰብኣዊነት ችግር ያለ መሆኑን ነው። ቃሎቹንም የተጠቀመችባቸው በተራ ትርጉማቸው ዘወትር በሚታወቁበት የእማሬያዊ ፍቻቸው አይደለም። በፍካሬያዊ ትርጉማቸው እንጂ። ቃሎቹን ደርድረን ብንመለከታቸው

አደራዳራቸው "ጥሬ ሥጋ"፣ "ጠጅ"፣ "ሽርሙጣ"፣ "መድኃኒት" እና "የመቃብር ሳጥን" የተሰኙ ናቸው። እነዚህን በፍካሬ ስንተረጉማቸው በመጀመሪያ ሴተኛ አዳሪዎች ትኩስ የሚያስጎመገቡ፣ የሚያማልሉ፣ ከፍ ሲሉም የሚቀመሱ፣ የሚጣጣሙ፣ ቀጥለው የሚሸጡ፣ የሚለወጡ በመጨረሻ የነገን ተስፋ እንዳጠለጠሉ የሞት መንገደኞች መሆናቸውን ለማሳየት በሁሉም የማህበረሰቡ ክፍል በተለመዱት እና በሚታወቁት ቁሳዊ ስሞች አሞካሽታ ማቅረቧ ሴተኛ አዳሪዎች ምን ያህል "ከሰው ተራ" ወጥተው ማንፀሪያ ቃላዊ መገላጫዎቻቸው እንኳ ሰዋዊ ባልሆነ በሰው የመገልገያና የመጠቀሚያ ቁሳዊ ስሞችን መጠቀሟ አመላካች ነው። በሌቱም አይነጋልኝም ውስጥም "ሴት እንደ ጥብስ ሥጋ ነች፣ ልክ እንደበሰለች አውጥተህ ሀኝ አለዚያ ወዲያው ታራለች (ገፅ፣ 71)" በማለት ሴትን ቶሎ "መብላት" ተገቢ መሆኑን ያሳያል። የሚበላ፣ የሚታኘክ፣ የሚጠጣ፣ የሚጣጣም፣ የሚሸጥ፣ የሚለወጥ የሰዎች መገልገያና መጠቀሚያ በሰዎች የተሠራ ወይም በተፈጥሮ የተገኘ ግኡዝ ዕቃ ብቻ ነው። ይህን የምታውቀው እናነ ለሰዎች ቀረብ ወዳለው በባህል በሰፊው በሚታወቀው "ሥጋና ጠጅ" ሴተኛ አዳሪዎችን መድባ ማቅረቧ ሴተኛ አዳሪዎችን ማዋረድ ማቃለሏ መናቅ መድፈሯ ሳይሆን ማህበረሰቡ ምን ያህል ሴተኛ አዳሪዎችን ዝቅ አድርጎ ሰብአዊነታቸውን ከዕቃ እንኳ አሳንሶ ከሚበላና ከሚጠጣ ነገ በሰውነት ውስጥ በሚካሄደው መካኒካዊ እና ኬሚካላዊ የምግብ መንሸራሸር ተካሂዶባቸው እንደሚወድቀው "ቆሻሻ" እንደሚቆጥራቸው ያጠይቃል።

በነሮ አስገዳጅነት ከሕይወት እስከሞት ተሰምረው መኖር አለመኖርን የሚያምጡት ሴተኛአዳሪዎች ማህበረሰቡ ከተፈጥሮ ሰውነት ለይቶ "ሽርሙጣ" የሚል በውስጡ ንቀትና ውርደትን ያዘለ የስድብ ቃል ያወርድባቸዋል። ከባህሉና ወጉ አግልሎ በንቀትና በውርደት ዐይን የሚመለከታቸው እሱ ራሱ በእንቡጥነታቸው ቀጭቶ በሴትነታቸው ተሞሽሮ መልሶ የስም ቅጭት ይሰጣቸዋል፤ ይፀየፋቸዋል።

ሴተኛ አዳሪዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ተንቀውና ዝቅ ተደርገው ቢታዩም የራሳቸው የሆነ ምኞት፣ ተስፋ፣ መሻሻል፣ መለወጥና መኖር የየዕለት የሕይወታቸው ስንቅ ነው። ነገር ግን ምኞት ተስፋቸውን ተሻሽሎ የመኖር ርእያቸውን ከሚሰሩበት "የመ.ያ መስክ" እነሱ ጋ "ለመማገጥ" በይፋም ሆነ በድብቅ በሚመጡት የወንዶች ግልምጫ፣ ንቀት፣ ስድብ እና ዱላ ምክንያት ከተስፋቸው ብርሃን ልቆና ደምቆ ያሰናክልባቸዋል። ተስፋቸውን የሩቅ ምኞታቸውን የሚያጨልምባቸው ስበቡ ብዙ ነው። በሥራቸው ምክንያት ከብዙ ወንዶች

ጋር በሚያደርጉት የግብረሥጋ ግንኙነት በአባለዘር በሽታዎች ይይዛሉ። ይህም በብዙ መልኩ ይጐዳቸዋል።

> ... ገላዬ አልፎ አልፎ ኩፍ ብሎ ማበጡን አይቼ በጣም ደነገጥኩ። አራት ቀን ያህል ተጠቅልዬ ከተኛሁ በኋላ፤ የሰውነቴን ሁናቴ ለወይዘሮ ባዩሽና ሊጠየቁኝ ለተሰበሰቡት የጐረቤት ሴቶች ገልጬ አሳየኋቸው። ወይዘሮ ባዩሽ "ያው መሆኑ ነው" አሉ። ከጐረቤቶቹ አንዷ "አተራ ከሆነ ቶሎ ይረግፋል" አለች ሌላዋ ተመልካች ቀጠል አድርጋ "ምን አለው ብላችሁ ነው እሱ አበባ ነው፤ አውቆ ይረግፋል" ከአለች በኋላ፤ እኔ ራሴ እንኳን ሐኪም ጎረቤት ሳያውቅብኝ ከዚህ በሽታ የተላቀቅሁት የዛሬ አምስት ዓመት ነው" አለች።
>
> (ገፅ፤ 21 አጽንኦቱ የኔ)

"አተራ ከሆነ ቶሎ ይረግፋል"፤ "እሱ" አበባ ነው አውቆ ይረግፋል" በማለት በሽታዋን ማቃለላቸው እውቀታቸው በልምድ፤ ፍርሀታቸው በተስፋ ማጣት እርምጃቸው በድህነት ስለተዘጋ ምንም ማንም ቢሆን ለመሸከም ጫንቃቸው ደንዳና ነው። የጫንቃቸው "መደንደን" የስቃያቸውን ብዛት፤ የመናቃቸውን መጠን ምን ያህል የወፈረ፤ የደለበና ከልክ ያለፈ መሆኑን ያስገነዝበናል። ግልፅነት የጐደለው ባህል እና ሥርዓት አግር ተወርች አስሮአቸው እውነታውን ከባህል "አፈንጋጭ"፤ "ሥርዓት ረጋጭ" እያላቸው እንዳይገነዘቡ አድርገዋቸው ይገኛል። ባህላችን ሴተኛ አዳሪዎችን አግልሎ ነገር ግን የባህሉ ፈጣሪዎች እነሱን እየተከታተሉ በሴትነታቸው (በገላቸው) ሲደሰት፤ ሲዝናና፤ ሲቀብጥ ይስተዋላል። መልሶ ግን ያወግዛቸዋል፤ ይንቃቸዋል። በአስከፊ የሕይወት ውጣ ውረድ የተዘፈቁትን ሴተኛ አዳሪዎችን የባሰውኑ ህሊናቸውንም ሆነ አካላዊ ማንነታቸውን የሚፈታተን የወሲብ ስሜት እንዲያቋድሱዋቸው በወሲብ የታወሩ ወንዶች እንዳሉ በ መነልየ መነልይ ዘካዛንችስ ማየታችን ምን ያህል ባህላችን "ረከሰ" እያሉ የሚደሰኩሩትን የባህልና ወግ ተቆርቋሪዎች እንድንታዘብ ያስገነዝበናል። ይህንን በተመለከተ በሰፊው ወደፊት የምናየው ነው።

ሴተኛ አዳሪዎች በአሰሪዎቻቸው የሚታዩት እንደሸቀጥ ዕቃ እንጂ እንደ ሰብአዊ ፍጡር(human) አይደለም። የሴተኛ አዳሪዎች (አሻሻጮች) ሕይወት መስዋዕት ተገብሮበት የአሰሪዎችን ሕይወት ያደላድላል። ይህንን አስመልክታ እናኑ "... የተደረደረውን መጠጥ ሁሉ ለመጠጣትና ለማስጠጣት ፈቃድ እና ችሎታ ያላት አሻሻጭ፤ የነጋዴዎች ሁሉ ሀብትና ሲሳይ ናት (ገፅ፤ 25)" ትላለች። ሴተኛ አዳሪዎች (አሻሻጮች) ለአሰሪዎች የሀብት

ማድለቢያ "ሽቀጦች" ወይም "ቁሶች" ናቸው። በውበታ የምታስመገርውን፣ በወጣትነታ የምታማልለዋን ቀንበጥ ሴት እራሳቸው ፈልገው ወይም በደላላ አፈላልገው በቡናቤታቸው ውስጥ ሲያስገቡ ሲሳያቸው እንደሚከፈት፣ ሀብታቸው እንደሚበዛ አስቀድመው አልመውት ነው። የሴተኛ አዳሪዋም ተግባር የተደረደረውን የመጠጥ አይነት እንደየጠጪው ፍላጐት በማቅረብ፣ በማግባባት አብራ የመጠጣት ችሎታ ሊኖራት የግድ ነው። አብራ እየጠጣች በመጠጡ ብዛት ውስጣዊ አካላቷ ቀስ በቀስ እሳት ውስጥ እንደገባ ጅማት እየተኮማተረ ለዘላቂ ሕመም ይዳርጋታል። ዘመኑ ይለያይ እንጂ "... ገብጋባዎቹ ጨካኞቹ-ርኩሶቹ-አረመኔዎቹ ... የካዛንችስ ቡና ቤት ባለቤቶች ... በእነሱ አካል ሽያጭ መኪና ያማርጣሉ ... (ተድባበ ፣ 1992)" የሚለው ትዝብት ልብ ሊባል ይገባዋል ። የሰብአዊነት መንጠፍ (Dehumanization) ነጥሮ የሚወጣውም እዚህ ላይ ነው። ገንዘብ እንጂ የሰው ልጅ ሰውነት (humanity) ዋጋ እንዳጣ የሚያስገነዝበው ይህ እውነት የህሊናችንን በገንዘብ መጋረድ ክማጠየቁም በላይ የሴተኛ አዳሪዎች ሰብአዊነት ከ "ሰው ተራ" ዝቅ ብሎ እንደሸቀጥ የተቆጠረበት የቡና ቤቶች የገቢ ማስገኛ የሸቀጥ ዕቃ (commodity) ሆኖ መቆጠሩን ያሳያል። የለየለት "የባርያ ንግድ" መልክና ስሙን ቀይሮ የተገለጸበት ነው ለማለት ያስችላል።

በማህበረሰቡ የተንሰራፋው አጉል ልማዳዊ አመለካከት እኛነታችንን ቀፍድዶ ስለያዘን ክቡር ለሆነው የሰውልጅ ሕይወት ደንታቢስ እንድንሆን አድርጐናል። ሴታ ድህነትን ሸሽታ ወይም በአጉል ባህል ተገድዳ በመዳሯ ወይም በመደፈሯ ይህን ልማዳዊ ድርጊት በመፍራት ወደ ሌላ አገር ትሰደዳለች። ክስደት የሚገጥማት ኑሮ ደግሞ ሰፊ ምርጫ ያለው ሴተኛ አዳሪነትነውና "ዘው" ብላ ትገባበታለች። አሁንም ሌላ "ጣጣ" ሌላ ችግር"፡ ችግሩም ሆነ ጣጣው ከየትም የመጣ ሳይሆን ያው ካገሯ ያስወጣት ባህል የተባለው ሰው ሠራሽ ሥርዓትና ደንብ ነው። ብትሸሸው፣ ልታመልጠው ብትሞክር አልተቻላትም። የባሰ "ስመ ሰባራ" የሚያደርግና አንገት አስደፍቶ የሰው "ቁስ" ወደሚያደርግ እንጥፍጣፊ ሰብአዊ ባህሪ ወደማያስቀር ሰንካላ ሕይወት ውስጥ የሚዶላት ሆኖ ያርፋል። ተስፋን ሰንቃ የወጣችው፣ ባህላዊ አመለካከት አንገቷን አስደፍቶ ውስጧን ያሸፈታት ሴት የጠበቃት ሕይወት ከድጡ ወደ ማጡ ይሆንባታል። ሕይወታ ዝንቅ ተስፋዋ ቀቢፀተስፋ ይሆንባታል። ይኼ ነው ብላ ለመተንበይ አትችልም። የሴትነት ገላዋን እንደእንስሳ ገዢ ከላይም ከታችም ገምግሞ "የምትወጣበትን" የምታወጣውን የገንዘብ ልክ በ "ጨምር" "ቀንሺ" ተከራክሮ "በእስቲ ይሁን" ተስማምቶ ይሏት ይሄዳል። የእነዚህ ወንዶች የውስጥ እውነት ገንዘቡን ከፍለው

ከወሰዷት በኋላ እንኳንስ በእንግዳ ደራሽ ይቅርና በራሳቸውም ተፈልጐ አይገኝም። አንድ ሰው እልፍ ነው። እዚህ መካሪ፣ አስተማሪ፣ ጨዋ፣ እዚያ ተመካሪ፣ ተማሪ፣ ባለጌ ነው።

> ... በውቤ በረሃ የሚኖሩት ሴቶች ሁሉ ራሳቸውን ሆነው ለመኖር የማይችሉ መሆኑ ገባኝ። እንደሲኒማ አርቲስቶች የሚኖሩት በመምሰልና በመመሰል ነው። ለመወደድና በወንዶች ዘንድ ተፈላጊ ሆኖ ለመገኘት የሚደረገው ጥረት፣ ጊዜንም ገንዘብንም የሚያባክን ነው። ለምሳሌ አነጋገራቸው በዜማና በፈሊጥ ነው። ሲራመዱ ይምሸከሸካሉ። ወይም ይደንሳሉ። አለባበሳቸው፣ እንዲሁም የስማቸው መለወጥና መታደስ ከጊዜውና ከሥፍራው ጋር እየተመሳሰለ ስለሚሄድ፣ ከጋራዥ እየታደሰች እንደምትወጣ መኪና ዘወትር አዲስ ይመስላሉ (ገፅ፣ 31)።

የሴቶች ስም ለውጥም የመምሰልና የመመሰሉ አካል ነው። በሁለት መንገድ። አንድ ገቢ አግኙቶ ነገን ለመተንፈስ ከዘመኑ የከተሜነት መንፈስ ጋር ለመዋሀድ፣ ሁለተኛ ማህበረሰቡ ለዘቀጠ ሕይወታቸው እንደሰው ተፈጥረው ሰብአዊነትን በመነፈጋቸው ተጠያቂና ምክንያት ያልሆነ ይመስል ራሳቸውን አሸዋ ውስጥ እንደሰጎን ቀብረው ከእሱ ለመደበቅ የሚያደርጉት የመምሰልና የመመሳሰል ሁነት ነው። ይሁን እንጂ ወንዶቹም ሆኑ ሴተኛ አዳሪዎቹ ከራሳቸው መደበቅ ችለዋል ወይ? የሚል የአንድምታ ጥያቄ እንድናነሳ ያስገድደናል።

ከላይ የመዘገዘኳትን የተራኪዋን አባባል ከልብ አስተውለን በአንድምታ ስንፈክረው ሴቶች የዘወትር ተግባራቸው ውስጣቸውን ደብቀው ላይ ላዩን "መታደስን"ይመርጣሉ። ተፈላጊነታቸውን ለማጉላት፣ ከጊዜና ከሥፍራ የሚስማማ "መመሳሰልን" ያዘወትራሉ። ነገር ግን የስም ለውጡ ወይም የሰብእና ለውጦች የተዳፈነውን ማንነታቸውን ያስለውጣል ወይ? የሚል ጥያቄ እንድናነሳ ያደርገናል። የተዳፈነውን ማንነታቸውን የተሰበረውን ስምና ልባቸውን አይለውጥም። ይህንንም ከዚያው ከተጠቀሰው አባባል "ሲራመዱ ይምሸከሸካሉ" የሚለውን እንደዋዛ ጣል የተደረገ ሐረግ ስንመለከት መምሰል መመሳሰሉ መሆንን የማይተካ መሆኑን ውስጣቸው የተሰበረ ለመሆኑ አመላካች ነው። ሲራመዱ ከተምሸከሸኩ ይህ ከየት የመጣ ነው? አንድ ሰው ቀጥ ብሎ ራሱን ችሎ የሚራመደው ውስጣዊ እሱነቱ ድፍረትን ኩራትን ሲያገኝ ነው። እነዚህ ሴቶች ግን ውስጣቸው በወግና በደንብ (በማህበራዊ ደንብ) የቦከቦከ ስለሆነ ለመምሰል በሚያደርጉት መገደር "መምሸክሸካቸው" ውስጣዊ

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

እነሱነታቸውን አጋልጠባቸዋል። በመምሰል ለመታደስ ቢጥሩ እንኳ በልማዳዊ በትር የቆሰለው ውስጣዊ ሰብእናቸው "እየገሸ" ማስቸገሩን የሚያጠይቅ ነው።

እናነ ኂላቀር የባላገር ኑሮ፣ ልማድና ባህል ትሸሻለች። ይከተላታል። አክስቷ ዘንድ ተቀምጣ የሰላም አየር መተንፈስ አለመች እንጂ በከተማ ያለን ዘመድ ለማግኘት ውጣ ውረዱ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሚሆን አላሰበችውም። በአክስቷ ፈንታ የተሳፈረችበት ቀስ እያለ ይገሙት የነበረው የጣሊያ መኪና ለአታላዩ ወንድ ዳረጋት። ገጃም ተወልዳ ያደገችው ተራኪዋ ባል ያገባችው በአሥራ ሁለት ዓመቷ ነው። ከዚሁ ከመጀመሪያ ባሷ ጋር ሶስት ዓመት ተቀምጣ ባሷንም ቤተሰቦቿንም ጥላ ከደሴ አዲስ አበባ ኮበለለች። አክስቷን ፍለጋ። ከመጽሐፉ ከገፅ ስምንት እስከ ገፅ ዘጠኝ ድረስ ባለው የተረኩ አካል ውስጥ አንዳንድ የሕይወቷን የወደፊት እጣ ፈንታ ምን ሊመስል እንደሚችል የሚጠቁሙ አመላካች ቃላት፣ ሐረጋትና አባባሎችን እየመዘዘኩ ላሳይ።

> ወሩ ሐምሌ እንደነበረ አስታውሳለሁ። ዶፍ ይወርዳል። ከጭነቱ በላይ ሠፍረን ዝናም ይቀጠቅጠን ከነበረው አሥር ሰዎች መካከል ሴቶቹ እኔና አንዲት አረጋዊት ሴት ብቻ ነበርን። ከተሳፋሪዎቹ ውስጥ አንድ እድሜው መካከለኛ የሆነ ራሰ በራ ሰው ጠጋ በሎ በፊት ስሜን፣ ቀጥሎ የሕይወት ታሪኬንና እንዲሁም ከዚህ ቀደም አዲስ አበባን አውቀው እንደሆነ አጥብቆ ጠየቀኝ። (አጽንኦቱ የኔ ነው)

በዚህ አላበቃም። ተራኪዋም ታሪኳን ሳትደብቅ መናገሯን ሲረዳ ያሳየውን ሁኔታ እንዲህ ስትል ትገልፃለች "የሰውየው ፊት ፈገግ ብሎ ጥርሱ ብልጭ አለ። አንድ ጥርሱ ሸራፋ መሆኑን ተመለከትኩ (አጽንኦቱ የኔ)።" የተራኪዋ የወደፊት እጣ ፈንታ ገና ከተረኩ መጀመሪያ ላይ ምን ሊሆን እንደሚችል ወሩ "ሐምሌ"፣ "ዶፍ" እና "አንድ ጥርሱ ሸራፋ" የተባሉት ቃላት እና ሐረግ ጠቋሚ ናቸው። ሐምሌ ወር የዝናም ወቅት መሆኑ ግልፅ ነው። ተምሳሌቱ (symbolic representation) ደግሞ ችጋርና ስቃይን የሚያመለክት ነው። "ዶፍ" ኃይለኛ የዝናም ዓይነት ሲሆን ተራኪዋን የመከራ "ዶፍ" የሚጀምራት ገና በጉዞ ላይ እንዳለች ነው። ይህም ተስትኂት በየቡና ቤቱ እየገባች የሚደርስባትን የችጋር፣ የሰብአዊነት ውርደትና የማንነት ጥያቄ አመለካች ነው። የመጀመሪያው አታላይ ወንድ ማንነቱን ውስጣዊ እሱነቱን ያሳየው ገና ከሚገናኙት መኪና ላይወርድ ለመሆኑ ለፈገግታ የከፈተው ጥርስ አንዱ "ሸራፋ" መሆኑ ነው። ይህም የሰውየውን አታላይነት አስመሳይነትና ተገዳሪነት

ብቻ የሚጠቁም ሳይሆን የጠቅላላ የማህበረሰቡ ወንዶች በትእምርትነት የሚወክል ነው። ይኼውም "እድሜው መካከለኛ" "ራሰበራ" የሚሉት ሀረጋት የሚቆሙት የባህሉን ወንዶች ማንነት የሚያጠይቁ ናቸው። ተራኪዋ በተረኩ ሂደት እንዳስቀመጠችው ባል ያገባችው በአሥራ ሁለት አመታ ሲሆን ከባሏ ጋር የተቀመጠችው ደግሞ ሶስት አመት ብቻ ነው። ስለዚህ የተራኪዋ እድሜ አሥራ አምስት ዓመት መሆኑ ነው። ይህችን የአሥራ አምስት አመት እንቡጥ የእድሜ ባለፀጋው "እድሜው መካከለኛ" እና "ራሰበራ" የተባለለት ወንድ አታሎ ቤቱ ሲያስገባትና ሲያሻው "ሚስት" ሳያሻው "ገረድ" እያደረገ ሁለት ዓመት ተኩል በቃላት እየሸነገለ እስረኛ እንዳደረጋት ትገልፃለች። ከዚህ ላይ በአንድምታ ነጥሮ የሚወጣው ሁነት ርህራሄ የሌለው የባህላችን ሁለት ገፅ ያለው ስለት ነው። ይህም የወንዶቻችን አስመሳይነት፣ አታላይነት እና ጨካኝነት።

ሚስትና ገረድነቷን ሳትለይ ለሁለት ዓመት ተኩል የስካር ዓመል ስታርቅ የቀየችው ተራኪዋ ጊዜያዊ ባሏን ትታ ከገባችበት ቤት ራሷን ይዛ ወጣች። ነሮዋም ከድጡ ወደ ማጡ የምንለው ዓይነት ሆነ። የሴተኛ አዳሪነትን "ሀሁ" ልትቆጥር የጠጅ ቀጅነትን ሥራ በአጠያያቂነት አገኘች። ይህንንም በማግኘቷ "እድሌ ተቃና" (ገፅ፣ 11) አለች። ለምን ቢሉ በዘመኑ የሴተኛ አዳሪነት ሕይወት ለብዙዎቹ የገጠር ሴቶች አማላይ ነበር። ያም ሆነ ይህ ግን ሰላምን አላገኘችም።

ማህበረቡ ያስከዳት ማንነት፣ ሰው መሆን፣ እንደሰው የመቆጠር ህልም መቋጠርና መፈታት የየቀን ህልሟ መሆኑን ተራኪዋ በየመጽሐፉ (text) ገፆች በአጽንኦት ታትታለች። እናትነት፣ ትዳር፣ ሥራ ማግኘት ... እውን ባይሆኑም ለመጨበጥ ትጥራለች፣ ትንጠራራለች፣ ግን አትደርስባቸውም። ራስን የመሆን ተስፋ ጠፍቶ፣ ማስመሰሉ እያየለ፣ ቀስ እያለም ተስፋዋ ተስፋ ቢስ ሆኖ ሲቀር ነው የሚታየው። ያጣችውን ማንነት ለማስመለስ፣ የተመኘችውን ሰው የመሆን ህልም የሚያጨልሙት ግብዞቹ ወንዶች እንደሆኑ ትገብቷን ትገልፃለች። " ... የእኛ የኢትዮጵያውያን ወንዶች በተፈጥሮኣችው ኩሩና ተግደርዳሪዎች ስለሆኑ፣ ከአቅማቸው ወይም ከገቢያቸው በላይ ወጪ ለማድረግ እምብዛም ቅር አይሰኙም። መከበርና ትሕትናን ይወዳሉ (ገፅ፣ 51)።" መባሉ የተሰራንበትን ማህበረሰብ ክንቱነት ያሳያል። በእርግጥ እናነ የበቀለችበትን፣ የምትኖርበትንና የተዋረደችበትን ማህበረሰብ የምትታዘበው በመራራ ምፀታዊ አገላለፅ ነው። አኗኗሩን፣ ሥርዓቱንና የወንድን ክንቱ ዓለም ከፍ ብሎም የገዘቅጠት መንፈሱን የታዘበችበት ነው።

ለዚህ ሁሉ መንስኤው የቤተሰባችን ሥርዓት፣ ባህሉ፣ ወጉ የፈጠረው ጣጣ፣ የፖለቲካው፣ የሃይማኖት እና የትምህርት ሥርዓቱ ችግር መሆኑን በካዛንችስ መንልየ መንልይ እና በሌቱም አይነጋልኝ ተደጋግሞ ተገልጿል። የወንድ "ተሸራሚጩ" ባህሉን ጋሻ አድርጐ የሴትነትን ሰብአዊነት ሲደፈጥጥ ገዝፎ ይታያል። "በአዲሱ የፍትሐብሔር ህግ መሠረት አባቱ ያልተቀበለው የሴተኛ አዳሪ ልጅ ውድቅ (አጽንኦት የኔ) ነው" (ገፅ፣ 60) የሚለውን ከሴተኛ አዳሪ ላይ መዘን ብናጤነው ሴተኛ አዳሪዎችን ከሰው በታች አድርጐ ሰብአዊነታቸውን የሚደፈጥጠው ባህሉ ብቻ ሳይሆን ፖለቲካው (መንግሥት) ጭምር እንደሆነ የሚያስገነዝበን ነው። ሴተኛ አዳሪዋ ብቻ ሳትሆን የወለደችውም ልጅ "ውድቅ" ነው። የህጉ አንቀጽ ሴተኛ አዳሪንና እናትነትን ብቻ ሳይሆን ሴትነትን ለይቶ የሚቀጣ በወንድ ዓለም የተቀረፀ ጉድፋችን ነው። አባትነት የውዴታ እንጂ የግዴታ ሆኖ ባልተቀረፀበት ማህበረሰብ ልጅ አባት የማግኘት እና ልጅ የመሆን መብቱ የተገደበ ነው። ግን አባትነት የእምነት ካልሆነ በባልና ሚስት መካከል የሚገኙ ፍሬዎችስ በእርግጥ ያባታቸው ናቸው? የሚል ጥያቄም ያጭራሉ። ተራኪዋ ልጅ አርግዛ የመውለዷን እንስታዊ ፀጋዋን ተፈጥሮአዊ በረከቷን የጠላችበትና የፈራችበት ምክንያት በልማዳዊ ህጉና በመንግሥታዊ ህጉ ሊደርስባት የሚችለውን "ቅጣት" በመፍራት ነው። ቅጣቱ በባህሉ መናቅን፣ መዋረድን እንደሚያስከትልባት የሚያውቀው አስወላጂው ወንድ ከውርደቱ ለመሸሽ መጠጊያው መከታው ባህሉ ሲሆን ይህንኑ የበለጠ በህጉ "አባቱ ያልተቀበለው የሴተኛ አዳሪ ልጅ ውድቅ ነው" የሚለውን መንግሥታዊ ህግ ታላቅ ማስፈራሪያ ይዞ ብቅ በማለት ለጥፋቱ ዕድቅን፣ ለውርደቱ ትንሳኤን ያገኝበታል። በአንዳሩ ሴቷ ግን ውርደትን ከስቃይና ከእንግልት ጋር ተሸክማ ተፈጥሮዋ ከሰውነት ተራ ወጥቶ፣ ቅስሟ ደቅቆ፣ የስነልቡና ስብራት በውስጧ ታቅፋ ትቀራለች። የሕይወት ጉዞዋ ቁልቁል ተዳፋቱን ለመውረድ እንጂ ሽቅብ ለመውጣት ፈታኝ ነው። አወራረዱ ፈጣን፣ አወጣጡ ግን የቆመ መሆኑን የምንረዳው ተራኪዋ ከውቤ በረሃ ወደ ገዳም ሰፈር ወርዳ በዚያ የሚገኙትን "የሥራ ባልደረቦቿን" ሴተኛአዳሪዎች ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ስትነግረን ነው። ከሽርመጥኖም ደረጃ፣ ከነ-ሮ በታችም ነ-ሮ መኖሩ በትልቁ ተስሏል። ጉዳዩ "በመንልየ መንልይ ዘካዛንችስ" ውስጥ በአምስት ደረጃዎች ተቀምጧል። በተለይም በአምስተኛ ረድፍ የተሳሉት ከገጠር የመጡ ወጣት ሴቶች የድህነታችን ፎቶግራፎች ናቸው። እዚህ የሴተኛአዳሪዎች ቦታ፣ ሰውነት የለም፤ ክብር፣ ፍቅር፣ ደስታ ... የለም። ሰው ከእንስሳት በታች የወረደበት ማህበረሰብ፣ ድህነትና ጉስቁልና ከሰው በላይ የገነነበት። ስብሃትም በሌቱም አይነጋልኝ

AAU LIBRARY ADDIS

አርግዘው ከወንድ ጋር ስለሚተኙ ሽርሙጥች የሚነግረን የጤና እክል የዚሁ አካል ነው። በወንዶቹ ገናንነት የተያዘው የማህበረሰባችን ባህል ሴቶቹ ለነሱ የተፈጠሩ ስለሚመስላቸው ስቃያቸውን ያበዛዋል። ሴትነት ራስን እንኳ ማክበር ማስከበር የሌለበት ነው። የመንግሥቱ ህግ በባህሉ ስለተተበተበ መብታቸውን አያስከብርላቸውም፤ ህግ አስከባሪውም ፖሊስም የስቃያቸው አንድ አካል ነው። ቅጡ ቢለያይም ይህ እውነታ በ መንልየ መንልይ ዘካዛንችስም ተንጸባርቋል። የ ሴተኛ አዳሪ አበይት ነጥቦች የሚሸከረከሩት ከገጽ 71-80 ድረስ በሚነሱት የክርክር ሀሳቦች ላይ ነው። ውይይቱ ወይም ክርክሩ የሚካሄደው በገዳም ሠፈሯ ሴተኛ አዳሪና ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ላይ በመጡ ጠጪዎች መካከል ነው። ነገርግን የውይይቱ ጭብጥ (theme) የሚያተኩረው በሰበካው ከምናነበው በሴተኛ አዳሪዋና በሁለቱ ጠጪዎች የሚካሄደው ክርክር ነው ካልን አያጠቃልልም። ክርክሩ በሁለት የማህበረሰቡ ክፍሎች የሚካሄድ ትእምርታዊ ውክልና ያለው ነው። የመጀመሪያው ተራኪዋ የወከለቻቸው ሴተኛ አዳሪዎች (ሽርሙጥች) ሁለተኛው ጠጪዎቹ የወከሉት የወንዶች ማህበራዊ ክፍል ነው። ክርክሩም ሁለቱ ክፍሎች አንድ ቋንቋ እየተናገሩ የማይደማመጡበት ከየራሳቸው አንባር በመከራከር የማይግባቡት ነው። በመጀመሪያዎቹ የሚነሳው የሕይወት ጥያቄ በሁለተኛው ክፍል አይመለስም። ከጅምሩ ተለያይተዋልና። በተለይ ሴቶቹ ላይ የወንዱ አመለካከት የወረደ እና የደከመ ነው። ሴቷ ለክርክሯ የምታነሳው ሀሳብ ቀጥ ያለ ሀቅ ነው። ሰዎቹ የመጡበትን የማህበረሰብ ክፍል የሚሸነቁጥ ነው።

> ባል አግቡ ላሉት ይኼ ሁሉ ጎረምሳ እኛው ዘንድ እያመሸና እያደረ ሲሄድ እንኳንስ ሊያገባን ይቅርና ቀን ሲያየን ፊቱን ያዞራል። ማታ እንደተለመደው በአፉ ሲደልለን ያመሻል። ይኼ ኑሮ ሰለቸኝ እንጋባና የድሀም ትዳር ቢሆን ችግራችንን በሆዳችን ይዘን አብረን እንቀመጥ ያልኩት እንደሆነ እንዲህ ሲል ይመልሳል። አስቀድሞ ነገር መላው አዲስ አበባ ያውቅሻል። በእድሜም ሆነ በአእምሮ ካልበሰለች ሴት ጋር ተጋብቶ ከመዳረቅ ካንች ጋር መኖር ይሻል ይሆናል የሚል እምነት ቢኖረኝም ይኼን ያህል ዘመን በሽርሙጥና ያረከሸውን የጋብቻ ፀጋ እንደና ለማደስ ያዳግታል።
>
> (ገፅ፣ 73-74) (አጽንኦቱ የኔ)

ትዝብቷ የዚያን ክፍል የወንድ ሽርሙጥና ግን ድብቅነት እና ግብዝነት የሚነካ ነው። ተራኪዋ ከተናገረችው ውስጥ "ቀን ሲያየን ፊቱን ያዞራል" ማታ እንደተለመደው በአፉ

"ሲደልለን ያመሻል" የሚሉት ሀረጐች የማህበረሰቡን ማንነት ቁልጭ አድርገው ያሳዩ ናቸው። የቀኑ ማንነታችን ድብቅ እና አስመሳይነቱ ማታ ይፋ የሚወጣበት ነው። ውስጣዊ ማንነታችን ማታ በመጠጥ ኃይል ይሉኝታና ባህል ፈሪ እና አክባሪነታችንን አሽቀንጥሮ ጥሎ ግብዝነታችንን ይፋ ያወጣዋል። በአስተያየት መልክ ጣል ያደረገቻቸው አልባሌ የሚመስሉት የተራኪዋ ቃላትና ሀረጋት የማህበረሰቡን ማንነት በምፀት አርቃኑን ያስቀረችበት ነው።

ማህበረሰቡ ጨክኖ የሚቀጣበት መንገድ በሌተኛ አዳሪዎችና በእሱ መካከል የብረት አጥር በመስራት ነው። የሚሸራሞጡት ከእነሱ ጋር ቢሆንም ሰርክ አብሯዋቸው ቢሆንም፣ የሌቶቹን እንጂ የነሱን አያስተውሉትም፤ ቢያዩትም አይታያቸውም። ምክንያቱም ባህሉ መደበቂያቸው መንግሥታዊ ህጉ ጋሻቸው ነውና። በመጨረሻም "እስቲ የማሰብ ክርክር ወደ ሌለበት ወደ ጨኸቱ መንደር እንሂድ (ገፅ፣ 80)።" የሚለው የሰዎቹ ንግግር ትልቅ ቁምነገርን ይዟል። "የማሰብ ክርክር" እና "ጨኸቱ መንደር" እነዚህን በውድቅት ሌሊት የተነገሩ በመጠጥ ስሜት የወጡ ሀረጋት በአንድምታ ስንፈክራቸው እውነት የማያስጨንቀው ራሱን መርሳት የሚፈልግ መፍትሔ የማያመጣና ማሰብን የሚሸሽ ትውልድ ሌላውን ግን የሚያወግዝ ማህበረሰብ ውስጥ መኖራችንን የሚያመላክቱ ናቸው። ሌቱን አንደአዳኝ አውሬ በየመጠጥ ቤቱ እየዞረ የሚጠጣና "የሚሸራሞጥ" ወንድ ግን ከሱ በተቃራኒ የቆመችውን በባህልም በህግም ድጋፍ ያጣችውን "በአፍ እየሸነገለ" በልቡ እየረገመ የሚቀብጥባትንና የሚረካባትን ሴተኛ አዳሪ፣ ሸርሙጣ ወዘተ. በሚል የውግዘት ቃል እየሸነቆጠ፣ ራሱን "ንጹህ" ሌላውን "ኃጢያተኛ" ያደርጋል። የተነሳውም ክርክር በወንዶቹ በኩል ከእውነት የቀረበ አይደለም። የማታለያ ለስሙ ያህል የቀረበ ክልብ ያልመነጨ ነው። ይህንንም ተራኪዋ ከረዥም ልምዷ ተረድታዋለች። ሀሳቡ የግብዞችና ያታላዮች መሆኑን አላጣችውም። ክርክር ማንሳቷ ውይይት መክፈቷ ታዝቤያችኋለሁ፤ አመለካከታችሁን አውቄዋለሁ ለማለት የተሰነዘረ እንጂ ከእነሱ እውነትን ትክክለኛ አስተያየትን እንደማታገኝ እንደማትሻም "ማታ በአፉ ሲደልለን ቀን ሲያዩን ፊቱን ያዞራል" በማለት ቀድማ ገልፃለች።ለዚህ አባባሏ ማጠናከሪያ የሚከተለውን ግጥም እንመልከት

ያው መቸም እኔም እንደሰው
አንዳንዴ አንዳንዴ ብቻ ሕሊናዬን እውነት ሲያምረው
.....

"ቀድሞስ ቢሆን ለእኔ ብጤ ለኔ ብጤ ለሔዋን ዘር
አዳሜ በኔ ለይ በቀር ለኔ መስክሮ አይናገር"

.....

ከቶ የናንተን ዳኝነት አልጠይቅምና ስመ-ኝ
ፋይል ክፈች እንዳትሉኝ። ...
ያው ብቻ በዘልማድ ሕግ በእንቶ ፈንቶአችሀ ልረታ ....
እውነቱ ከእውነት ተፋጭቶ ሐቅ ሆኗልና ሸውታ

(ፀጋዬ ገብረመድህን፣ 1966፣ 64)

ይህ ስንኝ እርስ በርሱ የሚጣቀስ ለተራኪዋ አባባል የሚስማማና የማህበረሰቡን ማንነት ሴተኛ አዳሪዋ ቀድማ ያወቀችው መሆኑን የሚያጠናክር ነው። ማታ በጨለማ እሱነቱ ይፋ እየወጣ፣ ቀን ግን ማንነቱን ደብቆ "ጻድቅ" መስሎ ሲመላደቅ ምን ያህል ማህበረሰባዊ የአስተሳሰብ ብክነት፣ የአመለካከት ድቀት ውስጥ ውስጡን እየገዘገዘን እንደሆነ በተራኪዋ አቀራረብ ለማስተዋል ይቻላል።

መኖር ማለት መብላት፣ መጠጣት የሆነ ይመስል የህሊና እውነት ከዕለት ጉርስ አንሶ የነገን እስትንፋስ በዛሬ ገቢ ለመሰነቅ የሚደረገው ግብግብ ሰው ከሰው በታች ለመውረዱ ምስክር ነው። እናትነት ኃጢያት ሴት በሴትነት ያገኘችው ፀጋ ረዳት ሆኖ መገለጹ እኛው በኛው ለእኛው እንድንቆዝም ያደርገናል። በተለይ ሴተኛ አዳሪዎች የአብራክ ክፋያቸውን ለእለት ጉርስ ሲለውጡት የሚያሳየን የተራኪዋ አገላለፅ በእጅጉ ያሳዝናል። "ልጅሽን ለምን ሲያለቅስ ዝምትይዋለሽ ወስደሽ አታጠቢውም? (ገጽ፣ 85)" በማለት የራሳቸውን ልጅ የሞግዚት ለማስመሰል የሚጥሩት እናት ሴተኛ አዳሪዎች ክህደታቸው ለነገ ሕይወታቸው ዋስትና በመሆኑ ነው። የወለደች (አራስ) የሆነችን ሴተኛአዳሪ ዘወር ብሎ የሚመለከት ወንድ የለም። ስለዚህ የወለደችውን ልጅ ሳትወድ በግድ ለእለት ጉርስ በመለወጥ ትክደዋለች። ተጠያቂው ያስኮበለላት ባህል፣ ለዚህ የዳረጋት ወንድ ነው። እናትነት ለነእዚህ አይነት ሴቶች ተፈጥሮአዊ ፀጋ ሳይሆን እዳ ሆኖ የቀረበበት ነው።

የታሪኩ ጉዞ ማህበረሰቡን በመውቀስ በመዘለፍና በመታዘብ አይቆምም። እግዜርስ "የለህም እንዳልል ይመሻል ይነጋል፣ አለህም እንዳልል እንዲህ ይደረጋል" የሚለው ቃላዊ ግጥም ከታሪኩ ጋር ጉልህ ተዛምዶ አለው።

ሴተኛ አዳሪዎችን ዝቅ አድርጐ መመልከቱና ማንቋሸሹ በባህል ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን በሃይማኖት ተቋምም በኩል መኖሩን ተራኪዋ ልጇ በሞተ ጊዜ የተከሰተውን ሁኔታ በትዝብትና በምፀት ገልጻለች። "ክርስትና ያልተነሳ ልጅ ከቅጥር ግቢ ይቀበራል?" ... "ያውም የሸርመጣ ልጅ (ገፅ፣ 102)" የሚሉት ሁለት ሀሳቦች የሴተኛ አዳሪዋን ሕይወት እና ሰብእና በባህል ብቻ ረግጦ የሚያበቃ ሳይሆን ባህላዊ አመለካከቱ ሃይማኖታዊ መሠረትም እንዲይዝ በማድረግ ሰብአዊ ተፈጥሮዋን በባህላዊ አመለካከት፣ በሃይማኖት ቀኖና በመርገጥ ስነልቡናዋን በመሰባበር ሁለንተናዊ "የሰብእና ንጥፊት" ያደርሱባታል። ከዚህ የከፋና የመረረ ኢ-ሰብአዊነት ከየት ይመጣል? አኽኮ አኽኮ ከጨረሰ በኃላ ወደ ትቢያ የሚያወርድና ትቢያ የሚያለብስ። በተለይም የተነገሩት ቃሎች በእምነቱ ሥፍራ መሆኑ ኢ-ሰብአዊነቱን ያብሰዋል። ለምን ቢሉ ማታ ጨለማን ለብሶ ከሴተኛ አዳሪዋ ጉያ የማይወጣው የማህበረሰቡ አባል "የሸርመጣ ልጅ" ማለት ይገባው ነበር? የሚል ሌላ የአንድምታ ጥያቄ ያስነሳል።

ሞት የማይቀር ተፈጥሮአዊ ክስተት ቢሆንም፣ ሞቶ ለመቀበር ደረጃ መለየቱ ደግሞ በደሉ ብርቱ፣ ሀዘኑ መሪሪ ነው። በዚህ ሁኔታ "የደካሞች ሁሉ ምርኩዝ ክርስቶስ መሆኑን እያመንኩ (ገፅ፣ 103)" ትልና ልጇ ለጽድቅ ባይበቃ እምነት ከንቱ እንደሆነ ትፈርዳለች። አምላክ እንዴት በምድርም በሰማይም ይበድላል የሚል አንድምታ አለው። ቤተክርስቲያንን ራሷ የማነች? የደሀ? የሐብታም? መነሳት ያለበት ጥያቄ ነው። የቤተክርስቲያን አስተዳዳሪዎች አንዲት ሴት ልጇን ክርስትና አንሱልኝ ብትላቸው የሚጠይቋት ነገር አለ። ጥያቄው የገንዘብና የቁሳቁስ ብቻ አይደለም። ይህ ብቻ ቢሆን ቀላል ነው። የልጁ አባት መቅረብ አልያም መታወቅ የግድ ነው። ይህን ከባድ ጥያቄ ደግሞ ሴተኛ አዳሪዋ ልትፈጽመው የምትችል አይደለችም። "አባት እኔ ነኝ" ብሎም የባህል ተጽእኖን፣ የሃይማኖት ውግዘትን ሰብሮና ደፍሮ የሚቀርብላትም ወላጅ ታማኝ አባት አታገኝም። በዚህ ምክንያት ለማሟላት ባለመቻሏ የልጁዋ ክርስትና የመነሳት ጉዳይ ህልም ሆኖ ይቀራል። ጥምቀት የእምነት ሳይሆን የክብር እና የሀብት ነው ወደሚል አንድምታ ያመራናል። "ክርስትና ሳይነሳ እንዴት ከዚህ ይቀበራል?" የሚል የእምነት ሳይሆን የድህነት ወይም የሀብታምነት ጥያቄ ያነሳል። ይህ ካልሆነ አብሮ ሲሸራሞጥ የነበረ ማህበረሰብ "ያውም የሸርመጣ ልጅ" ሊል ይገባው ነበር? ይህንን ይዘን ተራኪዋ ድህነትን "ቅዱስ መጽሐፉን"፣ ቤተክርስቲያንና ክፍ ብላም ክርስቶስን የምትሞግተው፣ የምትወቅሰው፣ የምትታዘበው እንደሆነ እንረዳለን። ልጅም ሆነ ዘመድ ሞቶ እንኳ ለመቅበር በዙሪያው ያሉ ነገሮች

የሚታዩ መሆናቸው በተለይም ይህ ልዩነት በቤተክርስቲያንና በመንግሥት መፈጠሩ ምን ያህል ባህላዊ ተፅእኖው ስር ሰዶ ቅርንጫፉ ብዙ እንደሆነ የሚያመለክት ነው። ይህ ሁኔታ በመጎልየ መጎልይ ዘካዛንችስም ይስተዋላል።

" ... የኡራኤል-የገብርኤል-የባዕታ-የኪዳነምህረት ..." አብያተክርስቲያናት የከበብዋት ካዛንችስ የእግዚአብሔርን ቃል ቀድማ ትሰማለች። " .. ተሸራሚጨ እየሸረሞጠ ይሰማል ..." የሚለውን አባባል "ከመጎልየ መጎልይ ዘካዛንችስ" ወስደን ስንመለከት ክርስቲያንና ክርስትና ያላቸው ግንኙነት ማህበራዊ ከበሬታን ለማግኘት እንጂ ከውስጥ አለመሆኑን ያሳያል። ማታ የሚያፈነግጥበትን የስነምግባር መርሆ ሲነጋ በየአብያተክርስቲያኑና በየመስጊዱ በመኮልኮል፣ በመስበክና በመሰበክ ለማካካስ የሚሞክረው የካዛንችስ ቡና ቤቶቹ ምርኮኛ መንፈሳዊ ሕይወቱ ከአለማዊ ሕይወቱ የተምታታበት ነው። ይህም መምረጥና መወሰን ያልቻለን ትውልድ ገጽታ ያሳያል። ለዚህ ደግሞ ደረጃ፣ ዕታ፣ እድሜ፣ ሙያ ... አይገድበውም፤ በካዛንችስ ሁሉም ቋንቋው አንድ ነው። ሲነጋ ግን አንዱ ሌላውን ለመታዘብ ይሽቀዳደማል። በሌቱም አይነጋልኝ በገጽ 23 ላይ ሴቶች ራሳቸውን እንኳ ለመከላከል የማይችሉ አቅመ ቢስ መሆናቸውን እንመለከታለን። በዚህ ጽሑፍ መጀመሪያ ላይ እንደተመለከተው "ራስን ለመሸጥም" ሆነ ለ "ማከራየት" ሴቷ መብት የላትም። የወንድ የበላይነት፣ የሴቶችን ሰብአዊነት ሲረግጥ ይታያል። አስገራሚውና የሰብአዊነቷ መንጠፍ ጐልቶ የሚታየው ሴተኛ አዳሪ (ሽርሙጣ) ለምን ተደበደብኩ ወይም ተመታሁ ብላ መክሰስ እንኳ አለመቻሏ ነው። በተመሳሳይ በመጎልየ መጎልይ ዘካዛንችስ ላይም የካዛንችስ ሽርሙጦች (ሴተኛ አዳሪዎች) ራሳቸውን ለፖሊስ "ጉቦ" እንደሚሰጡ ተመልክቷል። የህግ አድሏዊነት ወይም ለያዩነት ብቻ ሳይሆን እዚህ ላይ የሚታየው በህግ ጋሻነት የሚፈጸመው በደል ነው። ሴተኛ አዳሪዎች ከገንዘብ እስከ "ገላቸው" ጉቦ በመስጠት የሚደርስባቸው አካላዊና መንፈሳዊ ስቃይ መጠንና ልክ የለውም።

ሴተኛ አዳሪዎች ወደዚህ የስቃይ ሕይወት ለምን እንደገቡ ሁሉም የየራሳቸው መነሻ እንዳላቸው ይታወቃል። በሴተኛ አዳሪ ውስጥ የምትገኘው ተራኪ በማህበረሰቡ ዘንድ "በተነቀፈ" በባህሉ ባልተደገፈ በሃይማኖቱ በተወገዘ "ሙያ" እንዴት እንደገባች በትክክል ባታውቀውም ምናልባትም "የልጅነት ህልምና የመሻሻል ምኞት" ሳይሆን አይቀርም በማለት ታብራራለች።

ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

> ... በሽርሙጥና ያሳለፍኩትን ዘመን ስመለከተው በአንድ ፊት ከወንዶች ጭካኔ እንዲሁም ከብዙ ልማድና ሴትን ከሚጨቁን አንዳንድ አድራጐት ነፃ የወጣሁ ይመስለኛል። በአንድ ፊት ደግሞ ሥጋዬ፣ መንፈሴም ሆነ ሕሊናዬ የረከሰ ሆኖ አገኘዋለሁ። የሴተኛአዳሪነትን ሙያ እንደገመትኩት ሆኖ አላገኘሁትም። ባህልን በድፍረት በመጋፋት፣ የሚያማኝንና የሚነቅፈኝን ሰው በመናቅ ብዙ የኑሮ ትግል ካደረግሁ በኋላ ሥጋ ሸጦ የመኖር ተግባር ሰውን እንድጠላ ወይም እንድሸሸውና ተስፋ እንድቆርጥ ከማድረጉም በላይ ሕይወቴን በሞላ ከማህበራዊ ኑሮ ውጭ አድርጌ እንድገምተው አድርጐኛል፣ ወይም የማሰብ ችሎታየን ቀንሶብኛል (ገጽ፣ 128)።

ከተራኪዋ አባባል ሁለት አበይት ሀሳቦችን በመምዘዝ እንመልከት። "ከብዙ ልማድና ሴትን ከሚጨቁን ... አድራጐት ነፃ የወጣሁ ይመስለኛል" "በአንድ በኩል ደግሞ ሥጋዬ፣ መንፈሴም ሆነ ሕሊናዬ የረከሰ ሆኖ አገኘዋለሁ" የሚሉት አባባሎች ተራኪዋ ባህሉ በሴቶች ላይ የሚያደርሰውን ተጽእኖ በመቃወም ራሷን "ነፃ ለማውጣት" ያደረገችው ድርጊት በ.ያስደስታትም በሌላ ገጽታው ደግሞ የሥጋ ርኩሰት፣ የመንፈስ ጭንቀት፣ የሕሊና እረፍት ያላገኘች መሆኑን ትገልፃለች። የገፋት ባህልና ልምድ፣ የሸሸችው ሥርዓት በየዜደችበት እየተከተለ ሥጋዋን አርክሶ፣ የመንፈስና የሕሊና እረፍት እንዳይኖራት በማድረግ ለስነልቡና ችግር ይዳርጋታል። ይህንንም "ባህልን በድፍረት በመጋፋት የሚያማኝንና የሚነቅፈኝን ሰው በመናቅ ... ሥጋ ሸጦ የመኖር ተግባር ሰውን እንድጠላ ወይም እንድሸሸውና ተስፋ እንድቆርጥ ከማድረጉም በላይ ሕይወቴን በሞላ ከማህበራዊ ኑሮ ውጭ አድርጌ እንድገምተው አድርጐኛል" በማለት የስነልቡና ችግሩ ወደ ህሊና ግጭት ማምራቱን "የማሰብ ችሎታዬን ቀንሶብኛል" በማለት ትገልፃለች። ከጅምሩ የነበራት የማደግ ህልሟ ሰው የመሆን ምኞቷ በአጉል ልማዳዊ ተፅዕኖዎች የተቀጨባት ተራኪዋ ሴተኛአዳሪ ማህበረሰቡ የናቃትን የጠላትንና ያገለላትን ያህል እሷም የናቀችው የተጠየፈችው መሆኑን እንገነዘባለን። "ከማህበራዊ ኑሮ ውጭ አድርጌ ራሴን እንድገምተው አድርጐኛል" የሚለው አመለካከት አመለካች ነው። ስለዚህ ለራሱ ጥሩ ግምትና ስሜት የሌለው ሰው ከሌሎቹ ጋር ጤነኛ ግንኙነት ሊኖረው አይችልም። በዚህም ምክንያት የተወሳሰበ ስነልቡናዊ ችግር ሊታይበት ይችላል። የተራኪዋ ስነልቡናዊ ችግር የተከሰተው ከውስጥ በተነሳ የፍላጐት አለመጣጣም ብቻ ሳይሆን ከውጭ (ከማህበራዊ ልማዳዊ /ባህላዊ/) በመጣ ግፊት ነው። "ከልማድ ነፃ

ለመውጣት" ባህሉን በመጋፋት የገባችበት የሴተኛ አዳሪነት ሕይወት ወደ ሌላ "የመንፈስና የህሊና" ፀፀት ወደሚያስከትል ጣጣ ውስጥ ከተታት። ይህ የመንፈስና የህሊና ንጹህ ያለመሆን ጣጣ ደግሞ ወደ ጥላቻና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ዘፈቃት። ራሷን ገዝቅ አድርጋ እንድትመለከት በማድረጉ ሰው የተባለን ሁሉ ወደ መጥላት ወሰዳት። በመሆኑም ሰው የፈጠረው ባህላዊ ክስተት ሥርዓቱ ከርሮ ማስመሰሉ ገንኖ ሴተኛ አዳሪዋን አበሳዋን እንድትቆጥር አደረጋት ማንነቷን አደቀቃት። ሰብአዊነቷን አዋረዳት። ትንሽ እንኳ የሰውነት ባህርይ እንዳይቀራት ተደርጐ ተንጠፈጠፈ።

3.2 ሌቱም አይነጋልኝ

> Literature is the heart of the world; all the joys and sorrows, dreams and hopes, despairs and wraths of it, all the emotions of man as he faces the beauties of nature all his terror as he faces nature's secrets, lend to it wings (Gorky, Literature and Life, p. 90)

ይህንን የሩስያ የስነጽሑፍ ሰው አመለካከት በነፃ ትርጉም ወደ አማርኛ ብንመልሰው የሚከተለውን ይመስላል። "ስነጽሑፍ የምንኖርበት ዓለም የልብ ትርታ ነው። የሰውልጅ የተፈጥሮን ውበት ሲያደንቅ የሚሰማውን ስሜት፣ የተፈጥሮን ምስጢር ሲያይ የሚያድርበትን ፍርሀት፣ ደስታውንና ሀዘኑን፣ ህልሙንና ምኞቱን፣ የተስፋ መቁረጥ ስሜቱንና ቁጣውን ሁሉ ሕይወት ዘርቶ ያሳያል።" ይህን የጎርኪን አመለካከት በቁምነገር በማጤን በጽሑፌ መነሻ ላይ ያመጣሁት ሌቱም አይነጋልኝ በተሰኘው ልብወለድ ድርሰት ውስጥ ከማነሳቸው ሀሳቦች ጋር ተስማሚ የሆኑ የነገር ሰብ ጣጣ ድርጊቶችንና የአመለካከት ሁነቶችን በጭብጥነት የሚመዘዙ አስተሳሰቦችን (thoughts) ይዟል ብየ በማመን ነው። ደራሲ የሚኖርበት ማህበረሰብ አባል እንደመሆኑ መጠን በማህበራዊ ክንዋኔዎች ይሳተፋል፤ ያያል፤ የድርጊቶቹንም ክንዋኔዎች፣ የሁነቶቹንም ክስተቶች በበጐና በእኩይ ክንዋኒያዊ ሂደታቸውን በንቁ ሁኔታ ይከታተላቸዋል። በውስጡ የታመቀውን ምኞት ለህብረተሰቡ የሚያስበውን ርእይ እሱ በተመኘው መልካም ስነምግባር እንዲተካ ያለመውን በድርሰቱ ሕይወት ዘርቶ ያወጣል። መሆን አይገባውም የሚለውንም በድርሰቱ ይዟሳል።

ደራሲ ስብሀት ገብረ እግዚአብሔር ሌቱም አይነጋልኝ በተሰኘው ድርሰቱ የሴተኛ አዳሪዎችን አስከፊ የሕይወት ገፅታ፣ የስነልቡና ስብራት፣ ከማህበረሰቡ ልማዳዊ አመለካከት ጋር አቆራኝቶ፣ የማህበረሰቡን የአመለካከት ግብዝነት ቁልጭ አድርጐ ትዝብቱን አሳይቷል። ደራሲው ማህበረሰቡ ስለሴተኛ አዳሪዎች ያለውን አመለካከትና ድርጊታዊ ተሳትፎውን በዘመኑ ምን ይመስል እንደነበር ገልጿል።

ስነጽሑፍ ማህበራዊ ተቋም በመሆኑ የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ ማህበራዊ ገፅታዎች ያቀርባል። ስለሆነም ማህበረሰባዊ ሕይወት በስነጽሑፍ ይገለፃል። ስነጽሑፍ ራሱ ከማህበረሰቡ የሕይወት እንቅስቃሴ ውጭ ሕይወት የለውምና። ከዚህ መሠረተ ሀሳብ በመነሳት ሌቱም አይነጋልኝ በተሰኘው ድርሰት አንዱ የማህበረሰብ አካል በሆነው የሴተኛ አዳሪዎች የሕይወት ዙሪያ የሚያቀነቅነውን የሴተኛ አዳሪዎችን የስነልቡና ጭንቀት፣ የሰብአዊነት ንጥፈት፣ የማህበረሰቡን የአመለካከት "ንቀት" እና ውርደት ሲያስቃኘን በአንባራዊነት ደግሞ በዚህ የአመለካከት ታጋጊነት ማዕቀፍ ዙሪያ የማህበረሰቡን ምንነት የዘመኑን ትውልድ የርእይ መዛነቅ በአንድምታ ምን ይመስል እንደሆነ የሚያመለክት ነው። ለተገለጹት ሁነቶች እውነታዊነት ማስረጃችን በድርሰቱ ውስጥ የተገለጹት ሀሳቦች፣ አመለካከቶች እና አባባሎች ናቸው። ሀሳቦቹ፣ አመለካከቶቹና አባባሎቹ የፊለቁት ድርሰቱ በተረቀቀበት (በተፀነሰበት) ዘመን ይኖሩ በነበሩ ሀሳባዊ ሰዎች አማካይነት የተነገሩ በመሆናቸው ሌላ የሩቅ ነቃሽ የሚያስፈልግ አይመስለኝም።

ሴተኛ አዳሪዎች በሴተኛ አዳሪነት "ሙያ" ተሰማርተው ሲተዳደሩ በማህበረሰቡ የሚደርስባቸው ማህበራዊ ልማዳዊ ውርደት ከፍተኛ ነው። ነገር ግን ሁነቱን ጠለቅ ብለን ካጤንነው በሴተኛ አዳሪዎች ላይ ይህንን የውርደትና የንቀት አመለካከት የሚያሳድረው ማህበረሰብ የራሱ ምንነትና ማንነት መጠየቅ ያለበት ነው። እነሱን ዝቅ አድርጎ የሚመለከታቸው ቢመስልም ራሱ ህብረተሰቡ ከነሱ ጉያ አለመውጣቱን በዚህ ሌቱም አይነጋልኝ በተሰኘው ድርሰት ውስጥ እናገኛለን። በዚህም የማህበረሰቡ ማንነት ምን አይነት ገፅታ እንዳለውም ይጠቁማል። የማህበረሰቡን ማንነትና አመለካከት ምን ይመስል እንደሆነ ሰሬት ፀጋዬ ገብረመድህን ማነው ... "ምንትስ"? በሚለው ግጥማቸው

ኧረ ስንቱ ሞልቶ ስንቱ ብኩን የመንፈስ ምንትስ
ለሥጋውም አብሮን ወድቆ ዳግም በአእምሮው ሲረክስ
በልቦናውም ሲሴስን በሕሊናው ሕግ ሲድስ

AAU LIBRARY

"ፍሪ-ደሜ" ነው እያለ የኔኑ ደም ሲያልከሰክስ
በቃሉና በመንፈሱ ወድቆ ደቅቆ ሲበሰብስ
ቴህ ወዲያ ማነው ምንትስ!
ከሥጋው አልፎ በአእምሮ
ዘሙቶ ወድቆ ተሰብሮ
ከኔ እኩል ለገንዘብ ሰክሮ
በቃልና ባንደበቱ ከኔ ይበልጥ አመንዝሮ

(እሳት ወይ አበባ፣ 1966፣ 70)

በማለት ሴተኛ አዳሪዋ የታዘበችውን የማህበረሰቡን ምንነት በምሬትና በምፀት ገልፀዋል። ከዚህም አንባር በ <u>ሌቱም አይነጋልኝ</u> ውስጥ የሴተኛ አዳሪዎች ሕይወት በማህበረሰቡ አመለካከት ሲዳጥ ይታያል። ሴተኛ አዳሪዎች "በዝሙት ሙያ" የተሰማሩ በመሆናቸው ወንዶቹ የሚያዩያቸው የወሲብ ማርኪያ ብቻ አድርገው እንጂ እንደሌላው ሰው የሚያፈቅሩ መፈቀርንም የሚፈልጉ መስለው አይታዩአቸውም። በዚህም ምክንያት ሴተኛ አዳሪዎች ሲበሳጩና ሲጨነቁ ይስተዋላል። ሰው መሆናቸውንም ይጠራጠራሉ። የተገለሉ፣ የተናቁና የተዋረዱ መሆናቸውን አምነው ሳይወዱ ይቀበላሉ። ይህም የስነልቡና ችግር ያስከትልባቸዋል። ራሳቸውን ዝቅ አድርገው በመቁጠር ማህበረሰቡ በአፉ የሚለውን "ልማዳዊ" ባህላዊ ተፅእኖ ተቀብለው ለበለጠ የስነልቡና ስልበት ይዳረጋሉ። በአስተሳሰብም ሆነ በሰብዕናቸው የደከሙ የኮሰመኑ ይሆናሉ። በአስተሳሰብ የበለሉ በሰብዕናቸው የጠነከሩ ሆነው ከመገኘትና ከመታየት ይልቅ ውስጥ ውስጡን በመብሰልሰል ተስፋ ቢሶች እንደሆኑ አድርገው ራሳቸውን ይቆጥራሉ። ተናግረው ተከራክረው ከማሳመን ይልቅ እንባ ይቀድማቸዋል። ቀርቦ ለሚያናግራቸው ሰው የሚገልጹት ብሶታቸውን የውስጥ ቁጭታቸውን አፍቅረው አለመፈቀራቸውን በሰው መሀል ብቸኛ መሆናቸውን ከእንባ ጋር አቀላቅለው ይገልፃሉ። ተስፋቸው የተሟጠጠ መሆኑን አምርረው ይናገራሉ።

ሴተኛ አዳሪዎቹ በማህበረሰቡ "ምንትስ" (ፀጋዬ እንዳለው) እየተባሉ ቢጠሩም የማህበረሰቡ አንዱ አካል የሆኑት ወንዶች እነሱ ጋ "ሲልከሰክሱ" በመንፈስም "በሥጋም" ሲረክሱ "ምንትስ" ግን አይባሉም። ከዚህም አልፎ በሩካቤ ሥጋ ተደስተው ስሜታቸውን አርክተው ይሄዳሉ። ነገር ግን በሩካቤ ያረኩዋቸውን ሴቶች የሚመለከታቸው በንቀት እንጂ በፍቅር እንዳልሆነ <u>በሌቱም አይነጋልኝ</u> ውስጥ እናገኛለን። የድርጊቱ ሰለባዎች ሴቶችም

ይህን ያውቁታል። "በሥጋቸው ለመርካት" የሚመጡ እንጂ ንጹህ የፍትወት ሥጋ ፍላጐት ኑሩዋቸው ለፍቅር ብለው ሰዋዊ ፍቅር አስበው የሚመጡ አይደሉም። ይህንንም በመጽሐፉ አንድ ገፅ ውስጥ አንዷ ገፀባህርይ እንደሚከተለው ትገልፃለች።

> "አህያ መሰልኩት እንዴ ባየኝ ቁጥር ልተኛሽ የሚለኝ? እናቱን አህያ ይተኛትና! ሆ ... "ሰለቸኝ ብርሃንዬ ሰለቸኝ። መሸርሞጥ ሰለቸኝ። እጅ እጅ አለኝ! "ለምን አንዳንዴ እንኳን ዝም ብለው አቅፈውኝ አይተኙም? ሁልጊዜ መልፋት?"
>
> ... "ብርሃንዬ ለምን አንዳንዴ እንኳ በፍቅር አይስመኝም? ምን አረግኳቸው? ሽርሙጥና ከጀመርኩ ጀምሮ በፍቅር ተስሜ አላውቅም" (ስብሃት፣ 1993፣ 202)።

ሮዛ፣ የዘመኑ የውቤ በረሃ ሴተኛ አዳሪ ናት። ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ሀሳብ ብርሃኑ ለተባለው የውቤ በርሀ ደንበኛ ብሶቷን ስትገልፅ የሚያሳይ ነው። ሮዛ የውስጧን ጭንቀት ሰው ሆኗ ተፈጥራ እንደሰው አለመታየቷን በምሬት በእንባ አጅባ ታቀርባለች። ውስጧ ፍቅር ሽቷል። አፍቅራ የሚያፈቅራትን ትፈልጋለች። ነገር ግን ሴተኛ አዳሪ ናትና የሚያያት ሁሉ "ልተኛሽ" የሚሏት እንጂ በፍቅር አቅፎ የሚስማት ባለማግኘቷ ብሶቷን ትግልፃለች። ከአገኘችው ወንድ ጋር ወሲብ መፈጸሟ ሰልችቷታል። የውስጥ ነፍሷ የኔ የምትለው ሰው አስፈልጓታል። ያያት ሁሉ "ሥጋዋን" አይቶ ለመርካት ይጐመጓል፤ የጐመገፐውን ገላ በገንዘቡ "ገዝቶ" ግላዊ ደስታን የፍትወታዊ እርካታን ለማግኘት ይጥራል እንጂ ለሮዛ የመንፈስ ደስታን የነፍስ ሀሴትን የሚያስገኝላት ባለመሆኑ "አህያ መሰልኩት እንዴ ባየኝ ቁጥር ልተኛሽ የሚለኝ?" በማለት የተሰማትን ውስጣዊ ባዶነት በምሬት የምትናገረው። በማህበረሰቡ ዘንድ የተገለለች የተናቀች መሆኗን አምና ተቀብላለችና ለባህላዊ ልማዶች ሥርዓትና ደንቦች ግድ ሳይኖራት ብሶቷን ለመግለፅ የተጠቀመችበት አገላለፅ እንኳ ጥንቃቄ ያልታከለበት "ያልታረመ" አነጋገር ነው። "እናቱን አህያ ይተኛትና" የሚለው አገላለፅ ማህበረሰቡ እሷን እንደናቃትና እንዳዋረዳት ሁሉ እሷም የባህሉን ደንቦች በመጣስ ንቀቷን ያሳየችበት ነው። ከዚህ ልንረዳው የምንችለው ሮዛ አንዲት የውቤ በርሀ ሴተኛ አዳሪ ብትሆንም የሷ ብሶት የሁሉም ሴተኛ አዳሪዎች የጋራ ሕይወት መሆኑን ነው።

ሴተኛ አዳሪዎች ሕይወታቸውን በሙሉ ካልፈለጉት ወንድ ጋር በመተኛት የፍቅር ወሲባዊ ተራክቦ ሳይሆን የሚፈፅሙት ሕይወታቸውን ለማቆየት "መልፋት" ብቻ ነው።

ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

ይህም የሰለቻቸው "እጅ እጅ" ያላቸው በመሆኑ ውስጣቸው የተከፋ ተስፋቸው የተሟጠጠ ፍቅር ተመኝተው አፍቃሪ ያጡ በመሆናቸው በከፍተኛ ደረጃ ለስነልቡናዊ ችግር ይዳረጋሉ። ማህበረሰቡ እነሱን እንደሚያገላቸው ሁሉ እነሱም ማህበረሰቡን አግልለው በሰው መሀል ብቸኛ የሆኑ ባይታወር ይሆናሉ። በዚህም የራሳቸውን "የግል አለም" በመፍጠር በሚኖሩበት ማህበረሰብ ባህልና ሥርዓት ግድ ሳይኖራቸው ይኖራሉ። በውስጣቸው ተስፋ በአኗኗራቸው ደስታ ስለሌለ በመንፈስ የተሰበሩ በሰብዕናቸው የኮሰመኑ ሆነው አንገታቸውን እንደደፉ ሕይወታቸውን ይገፉታል። ፍቅር አልባ የሆነው የወሲብ ልፋታቸው ለስነልቡና ችግር ያጋልጣቸዋል። በዚህም የቀረቡትን ይጠራጠራሉ፤ የልባቸውን አውጥተው ውስጣዊ ስሜታቸውን ምኞት ፍላጐታቸውን ለመናገር አይደፍሩም። ታማኝነትን ከህብረተሰቡ ፍቅርን ከወንዱ አጥተዋልና ግልፅ ሳይሆኑ ድብቅ ሆነው ኑረው ማንነታቸው ሳይታወቅ ይሞታሉ። በአካላቸው ተደስቶ፣ ሥጋዊ ፍላጐቱን አብርዶ ንቀቱን አሳይቶ የተስማሙበትን ገንዘብ ወርውረውላት ይሄዳሉ እንጂ ፍቅርን አጎይተው መልካም ምኞትና ተስፋ ሰጥተው አይሄዱም። ለዚህ ነው "መሸርሞጥ ስለቸኝ እጅ እጅ አለኝ! ... ለምን አንዳንድ ጊዜ በፍቅር አይስመኝም (ገፅ፣ 203)?" እያለች የውቤ በረሀዋ ሴተኛ አዳሪ ሮዛ የምታማርረው። ፍቅርን እየፈለገ ፍቅርን ከማጣት የበለጠ ሰብኣዊ ስቃይ ከወዴት ይመጣል?

ሴተኛ አዳሪነት በማህበረሰባችን ውስጥ "እጅግ የተወገዘ" ድርጊት ነው። በሃይማኖት ረገድም ዝሙት ከሃጢያት የሚቆጠር ነው። እንደ ወንጀል ባይቆጠርም እንኳ እንደኃጢያ ት መታየቱ ግልፅ ነው። ይህም ህብረተሰቡ ለሴተኛ አዳሪዎች ያለውን አመለካከት የተዛባ አድርጐታል። ፍቅሯን ተቀብሎ የባህሉን ይሉኝታ ጥሶ የሚያፈቅር ወንድም ከተገኘ አሰዳቢ የጨዋ ልጅ ጠፍታ ነው ሸርመጣ የሚያፈቅረውና የሚልከሰከሰው እየተባለ ይታማል፤ ጣት ይቀሰርበታል በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በነገር ይሸነቁጡታል። ይህ የማህበረሰቡ አመለካከት በባህሉ የተደገፈ ስለሆነ ሴተኛ አዳሪዎችም አምነው ተቀብለውት ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ይቆጥሩታል። ቢያፈቅሩም ላለመግለፅ በውስጣቸው አፍነው ይይዙታል እንጂ "ወደድኩህ" "አፈቀርኩህ" ብለው ለመግለፅ ይፈራሉ።

<u>በሌቱም አይነጋልኝ</u> የተገለፀችው ትርሲት ሴተኛ አዳሪ ብርሃኑ የተሰኘውን አፍቅራዋለች። ፍቅሯም ልክ የለውም። ከሱ ጋ "ስትወጣ" እንኳ ገንዘብ አትቀበልም። ብርሃኑ ገንዘብ የሰጣት ዕለት ሴተኛ አዳሪ መሆኗን ታስታውስና ቅር ትሰኛለች። ከብርሃኑ ጋ ስትሆን ሴተኛአዳሪ መሆኗን ትረሳለች፤ ደስታም ይሰማታል። ብርሃኑም ትርሲትን ይወዳታል። ሆኖም ብርሃኑ ወደ ጀኔቫ ለሥራ ተልኮ የሚሄድ መሆኑን በመስማት

ተጨንቃለች። ስቃይዋ ውስጡ ውስጡን ያቃጠላታል ። የስቃዩ ምክንያት የብርሃኑ ፍቅር መሆኑን አውጥታ ለመግለፅ ባለመቻሏ የዘወትር መግለጫዋ የታመቀ ለቅሶ ብቻ ነው። የብርሃኑ ጓደኛ የሆነው ምናሴ ያፅናናታል። ይመክራታል። ግን ውስጧ በፍርሀት ስሜት በታመቀ ፍቅር ስለተገዳ መውጫ የለሽ እንባዋን ማውረድ ብቻ ነው። በመጨረሻ ምናሴ ሲቆጣት የግዷን "ምን ላርግ ምናስዬ? እወ-ወደዋለሁ እኮ" "እሱም ይወድሻል" "ታዲያ ለምን ትቶኝ ይሄዳል?" (ገፅ፣ 4-5) ትላለች። የትርሲት ፍርሀት ሁለት ስለት ያለው ነው። የመጀመሪያው ሴተኛአዳሪ ማፍቀር የማታውቅ ለገንዘብ ብቻ ገላዋን ለወንዶች የምታቀርብ ተደርጋ ስለተወሰደች ባህሉ ተፈጥሮዋን አበሻቅጦ ወደታች አውርዶባት እያለ ስተት ብላ ፍቅር ውስጥ ገባች። ይህንን ፍቅርዋን ለመግለፅ እንኳ በባህል የተገደበች ስትሆን ሁለተኛው ደግሞ ለወደደችው ሰው የፍቅሯን ልክና መጠን በቃላት ለመግለፅ ገልፃም በመጠኑ ለመገላገል አልቻለችም። ምክንያቱም የወደደችው ብርሃኑ ያምነኝ ይሆን የሚል የውስጣዊ የማሳመንና የመተማመን ጭንቀት ውስጧን ቀስፎ ይዟታል። ለጓደኛው በለቅሶ መሐል የገለፀችው "እወ-ወደዋለሁ እኮ" በሚለው ቃል የመጨረሻዋ የተሰመረባት "ኮ" እንዲሁ የገባች አይደለችም። ጭንቀቷን ለመግለፅ የገባች ናት። ማህበረሰቡ ባለው አመለካከት በሴተኛ አዳሪ ላይ የጫነው እይታ "ድንቄም አፍቃሪ!" ይሏታልና እንደማታፈቅር በግድ አሳምነዋታልና መውደድዋን ለምናሴ ስትገልፅ ምናሴም አያምነኝ ይሆን የሚል ጥርጣሬ ስላላት የውስጧን ጥርጣሬ ለማሳየት የተጠቀመችበት እንጂ የፍቅሯን ልክና መጠን አገልታ ልታሳይ የተጠቀመችበት አጋኖ አይደለም። ይህም ምናሴ "እሱም ይወድሻል" ሲላት የመለሰችለት "ታዲያ ለምን ትቶኝ ይሄዳል?" የሚል ነው። የትርሲት ፍርሀት ጭንቀትና ብሶት የሚጎላው እዚህ ላይ ነው። "ለምን ትቶኝ ይሄዳል?" የሚለው አባባል የሚያስተላልፈው አንድምታ ትርጉም ያዘለ እንጂ ተራ የሆነ አገላለፅ አይደለም። ይህንንም አባባሏን ምናሴ በሚገባ የተረዳው ይመስላል። "የምታለቅሰው ለአራት ወር ከብርሃኑ መለየት ስላቃታት ብቻ አይደለም። ቀናው ምክንያት "ሲመለስ ቢተወኝስ?" ብላ ስለምትሰጋ ነው (ገፅ፣ 5)።" የትርሲት የውስጥ ስቃይ ይህ ነው። አፍቅረው ካፈቀሩት ጋር አብሮ ያለመኖር። ከላይ ያየነው በተናጠል የአንዲት የትርሲት ስቃይ ብቻ አይደለም። የሁሉም የሴተኛአዳሪዎች ብሶት ነው። ሴተኛ አዳሪዎች ሁሉንም ጫና ችለው በፍቅር ቢያዙም እንኳ የባህልም ሆነ የባህሉ ተገዥ የሆነው ማህበረሰብ የሚያደርስባቸው ንቀትና ውርደት ራሳቸውን እንዲጠሉ ያደርጋቸዋል። የወደዱት ወንድ እንኳ የሚወዳቸው ቢሆንም የወደዳቸው መስሎ አይታያቸውም። አያምኑም። አምነው እንኳ ለጊዜው ቢቀበሉም

ILS LIBRARY ADDIS

በመጨረሻ ጥሎን ይሄዳል የሚል ጥርጣሬ ስላላቸው የዘወትር ጥርጣሬያቸው ከነሱ አይላቀቅም። ነገ ጥሎን ይሄዳል የሚል ፍርሀታቸው የየዕለት ሰቀቀናቸው ነው። ነገር ግን እነሱ የሚያፈቅሩትን ያህል የባህል ተዕእኖውን የቤተሰብና የጓደኛ አሽሙሩን ወደ ጐን ብለው ሴተኛ አዳሪዎችን የሚያፈቅሩ "ጀግኖችም" አልፎ አልፎ ይገኛሉ። ጀግኖች ያልኩበት ምክንያት ወግ አጥባቂውን የባህል አመለካከት ጥሰው "ነውር" የተባለውን ከምንም ሳይቆጥሩ ቤተሰቦቻቸውን ሳይፈሩ ጓደኞቻቸውን ሳያፍሩ ያፈቀረቻቸውን ሴተኛ አዳሪ አፍቅረው ፍቅር ሰጥተው ፍቅር ለመቀበል ችለዋልና ነው። ለዚህ አባባሌ ድጋፍ ከድርሰቱ ውስጥ የሚከተለውን አባባል በነቃሽነት ላቁም። "እዚህ ቤት ከሚመጡት ወንዶች ሁሉ ከእያንዳንዳቸው ጋር ቢመዘን፣ የብርሃኑ ወንድነት (አዕንኦቱ የኔ) እጥፍ ወይም አስር እጅ ነው" (ስብሃት፣ ገዕ፣ 27)።

ጥላሁንና ምናሴ በምዕራፍ ሁለት "ገድለ ጥላሁን" በሚለው ስር ስለወንድነት የሚያደርጉት ክርክር የሁለቱን የምናብ ሰዎች የአመለካከት ልዩነት አጉልቶ የሚያሳይ ነው። ጥላሁን "ወንድነት" የሚለው መደባደብ ሌላውን በጡንቻ አሸንፎ የበላይ መሆንን የሚያንፀባርቅ ነው። ይህም ከሌሎች ሁሉ ወንዶች በጉልበት በልጦና ልቆ መገኘት ነው። አለመሸነፍ ድል አለመሆንን ነው ወንድነት የሚለው። በአንፃሩ ግን ምናሴ ይህን አካላዊ ጥንካሬና ተደባድቦ ያለመሸነፍንና የጠብ አጫሪነት የሰዋዊ ወንድነት ከወንድነት ወይም ከጀግንነት አይቆጥረውም። ለምናሴ "ወንድነት" (ጀግንነት) ማለት አጉል የሆነውን በባህል ስር ሰዶ ያለውን አመለካከት ጥሶ መውጣትና በራስ አመለካከት መኩራትንና መፅናትን ነው እንደወንድነት የሚቆጥረው። ለዚህም ነው ብርሃኑን ወንድነት አለው ከማንም ይበልጣል ብሎ በአዕንኦት የሚከራከረው። ብርሃኑንን ጀግና ነው የሚለው እንደነውር እና ኃጢያት የሚቆጥረውን ሴተኛ አዳሪን ማፍቀር እሱ ስለፈፀመው ከባህሉ በማፈንገጡ ያደንቀዋል።

... "ከብርሃኑ ሌላ ማን ወንድ ነው ደፍሮ
ሸርሙጣ ይዞ ፒያሳ መሀል የሚንሸራሸር?
ማነው በየቡና ቤቱ ይሂት የሚገቦ? ሌሎቻችን
እንዲያው እዚህ ሲሆን እናሸሞነሙናቸዋለን፣
ውጪ ስናገኛቸው እንደማናውቃቸው እናልፋቸዋለን ...
(ገዕ፣ 27)።

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

ብርሃኑ በምናሴ የተደነቀው ወንድነት ያለው ጀግና የተባለው በባህል ያልተደገፈውን የባህሉ አራማጆች የናቁትን የሴተኛ አዳሪነትን ሕይወት ደግፎ ሴተኛ አዳሪዎችን ሳይንቅ ትርሲትን በማፍቀሩና ለሷም ክፍ ያለ ግምት በመስጠቱ ነው። ማንም የማያደርገውን በማድረጉ ነው። ምናሴ ብርሃኑን እንደ ጀግና ቆጥሮ የሚያደንቀው በድፍረቱ ብቻ አይደለም። ሴተኛ አዳሪዋን ይዞ በማንሸራሸሩ በየቡና ቤቱ ይዞም በመዞሩም ብቻ አይደለም። ይህንን ሲያደርግ ሌሎች ወንዶች በድብቅ የሚፈፅሙትን እሱ በይፋ ሲፈፅመው እነዚያንም ማጋለጡ ለምናሴ ግልፅ ስለሆነለትም ነው። ከሴተኛ አዳሪዎች ጋር ማታ ማታ ነፍሱን በፍትወት ሲያረካ የሚያመሸው ሴሰኛ ወንድ ሁሉ የተዝናናባትን ሴት ጧት ሲያገኛት እንደማያውቃት አንገቱን ጠምዞ ያልፋታል። ለምን የማህበረሰቡን ትችት ይፈራል። በጨለማ እንጂ በቀን ብርሃን ጉዱ እንዲወጣ አይሻም። ይህን የማህበረሰቡን ዝንቅ ድርጊት ብርሃኑ በተዘዋዋሪ ያጋልጣል። ለምን ሽርሙጣዋን አፍቅሮ እንደእድፍ የሚቆጠረውን ሽርሙጥና ካፈቀራት ሽርሙጣ ፍቆ ለማውጣት የቻለ ብቸኛ ወንድ እሱ ብቻ ነው። ሌሎች ይህን አላደረጉም፤ ድፍረቱን አጥተዋል። ተደብቀው ግን አዛውንቱ ጉልማሳውና ወጣቱ ሁሉ ሳይቀር ከነሱ ጉያ ተወሽቆ የስሜት ፍላቱን የሴሰኝነት አመሉን ሲከላ መታየቱን ምናሴ ትዝብቱን ይገልፃል።

በማህበረሰቡ የተዛባ አመለካከት ሳቢያ እያፈቀሩ የተጉዱ ብዙዎች ናቸው። በ <u>ሌቱም አይነጋልኝ</u> የቀረበችው ማሚት፣ በእሷ ቤት ውስጥ የምታስተናግደው ጠንፍየለሽ ለአብነት ተጠቃሽ ናቸው። ሁለቱ ሴተኛአዳሪዎች በቡና ቤቱ ያላቸው የሥራ እርከን ማሚት የቡና ቤቱ ባለቤት፤ ጠንፍየለሽ ደግሞ በማሚት ቡና ቤት ተቀጥራ መጠጥ አቅራቢ ናት። የሁለቱም የጋራ የሆነው የ "ሙያ" ግንኙነት ደግሞ ለዝሙት የመጣውን ወንድ ገንዘብ በመቀበል "ገላቸውን ማከራየት" ነው። በዚህ "ሙያ" በሚተዳደሩበት ጊዜ ሁለቱም አፍቅረው የተጉዱ የማህበረሰቡ የተዛባ የአመለካከት ሰለባዎች ናቸው። ማህበረሰቡ ማንነታቸውን ሸርሽሮ ውልቃቸውን ያስቀረ የባህል መጋኛ የመታቸው ምስኪኖች ናቸው።

ማሚት መልካም አሳቢና ፍቅርን አጥብቃ የምትሻ ናት። ነገር ግን ፍርሀትና ጭንቀት ሰቅዞ ይዟታል። ምክንያቱም በሷ ፍቅር ናላው የዞረው ክንፉ እንደማያገባት ስታውቅ ባያገባትም እንዳይተዋት ትፈራለች፤ እንዲተዋትም አትፈልግም። እንደው ዝም ብሎ አፍቅሯት እንዲቆይ ትመኛለች። እንደማይጋቡ ራሷ ቀድማ ታውቃለች፤ "ሽርሙጣ" የሚያገባ የሚደርስበትን ማህበራዊ ውግዘት ታውቃለች። ይህን እያወቀች ፍቅሩ አስገድዷት እንዳይተዋት እየተሳቀቀች አፍቅራዋለች። ምንም እንኳ ክንፉ ማፍቀሩን ቢገልፅላትም እሷ

ግን አንድ ቀን ሊተዋት እንደሚችል ታውቃለች። ማሚት ክንፈን ያፈቀረችው ለመጀመሪያ ጊዜ ስታየው ነበር። ክንፈ ግን ማሚትን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያያት በቁንጅናዋ ተማርኮ ሌሎች ሴቶችን ሲያደርግ እንደነበረው ሊቀብጥባትና የሴሰኛ አመሉን በፍትወት ሊወጣባት እንጂ ለእውነተኛ ፍቅር አልነበረም። የማሚትና የክንፈ የፍቅር ግንኙነት የተረቀቀው በምን መልክ እንደነበር በምዕራፍ ስድስት "ማሚት" በሚለው ርዕስ በሰፊው ተጠቅሷል። የክንፈና የማሚት የፍቅር ልክና መጠን ለየቅል ነው። ማሚት ክንፈን ያፈቀረችውን ያህል ክንፈ ማሚትን አላፈቀራትም ነበር። ማሚት ለገንዘብ ብላ ከተለያዩ ወንዶች ጋ "ስትወጣ" ክንፈ አያውቅም ነበር። ቀስ በቀስ ከሌሎች ወንዶች ጋር የምትወጣ መሆኑን ሲደርስበት "ሽርሙጣ" እያለ ሲሰድባት ይከፋት ነበር። "ሽርሙጣ" መሆኔን ቀድመህ ታውቅ አልነበረም? እያለችም ምሬት የተቀላቀለበት ንግግርም ታሰማው ነበር። መናደድዋንና ለብእናዋ የተነካ መሆኑን ይገነዘብና ፈጥኖ ይቅርታ በመጠየቅ ንደታን ለማስረሳት ይሞክራል። ክንፈ ቀስ በቀስ ፍቅሩ በቅናት መልክ ይወጣል። አጀማመሩ ገና ጀማሪ "ባለድንግል" ወጣት መስሎ በማታለል የገባበት የማሚት "ገላ" ሳያስበው ወደማይወጣበት በቅናት ወደታጀበ ፍቅር ውስጥ ይከተዋል። ከማሚት አልጋም ሳይወጣ ሁለት ድፍን ወር ከትምህርቱ ተስተጓጉሎ የሷም የጓደኛም የዘመድም ምክርና ተግሳጽ ሊመልሰው የቻለው ከብዙ ልመና በኋላ ነው። ማሚትም ፈተናውን ተፈትኖ በማለፉ በጣም ተደሰተች። ክንፈም የኮሌጅ ትምህርቱን ቀጠለ። ፍቅራቸውም አልተቋረጠም።

በህብረተሰቡ የተዛባ አመለካከት ምክንያት የሚናቁት ሴተኛ አዳሪዎች እንደማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ማፍቀር የሚችሉ፤ ላፈቀሩትም ሰው በጐ የሚያስቡና የተሻለ ደረጃ ደርሰው ማየት የሚፈልጉ ናቸው። ነገር ግን ምንም በጐ ቢያስቡ ምንም የሚያፈቅሩ ቢሆኑ ማህበረሰቡ በቀና የማይመለከታቸው በበጐ ዓይን የማያያቸው ናቸው።

> ... ማሚት ክንፈን ወደ ገሀነም የምትመራ የሰይጣን አገልጋይ በመሆኗ እሸቱ እንደ ጠላት ይቆጥራታል። እሷም በበኩሏ እሸቱ የክንፈን ፍቅር ሊያስቀርባት መሞከሩን ስለምታውቅ ትጠላዋለች። ... አንቱ "እርስዎ" እየተባባሉ እየተከባበሩ ሲነጋገሩ ክንፈ ውስጥ ውስጡን ይስቅባቸዋል (ገፅ፤ 154)።

ከመጽሐፉ የተጠቀሰውን "ማሚት ... ወደ ገሃነም የምትመራ" የሚለውን ሐረግና "የሰይጣን አገልጋይ" የሚለውን ሐረግ ወስደን የሚያስተላልፉትን መልእክት ብንመረምር

ሴተኛአዳሪዎች የሚደርስባቸውን የስነልቦና ስብራት ለመገመት አያዳግትም። ማሚት፣ ክንፈን ምንም ያህል ብታፈቅረው ለሱም የምታስብና የምትጨነቅ ቢሆንም ማንም ከቁምነገር የቆጠረላት የለም። "ወደገሀነም የምትመራ" የሰይጣን ፈረስ ተደርጋ ነው የተወሰደችው። ሰው በራሱ ልዩ ልዩ ሰብኣዊ ድክመት ምክንያት ማህበረሰቡ በማይቀበለው ቦታና ስፍራ ከተገኘ፣ "የተከለከሉ" ማህበረሰቡ ያገዳቸውን ድርጊቶች፣ አሊያም እምነቶችና አስተሳሰቦች ከፈፀመና ከጣሰ በማህበረሰቡ ዘንድ የተወገዘ መሆኑ ግልፅ ነው። እነዚህን እምነቶች፣ ወጐችና ደንቦች የጣሰበት ምክንያት አንድም "ሰይጣን" አስቶት አሊያም አጉራ ዘለል ባህልና ደንብ ረጋጭ አፈንጋጭ ስለሆነ የሚመስለው በሰይጣን ነው። ነገር ግን ነገሩን ከልብ ካጤንነው ማሚት ይህን "ሰይጣናዊ" ሥራ የምትፈጽመው ከማን ጋር ነው? እሷን ሰይጣን ናት ብለን ከተቀበልን ወደሷ በመምጣት ጨለማን ጋሻና ከለላ አድርገው "የሚያሳጥኗት" ሌሎች የማበህበረሰቡ አካሎች ምን ተብለው ሊጠሩ ነው? ማሚት ጋ ሄዱባት እንጂ ማሚት በየቤታቸው በየጐጇቸውና በየመጠለያቸው በመሄድ አላሳላተቻቸውም። ስለዚህ "የሰይጣን አገልጋይ"፣ "የገሀነም መሪ" ልትባል ይገባል? "ሙያውን" በገሀድ እንደማንኛውም የሥራ መስክ ቆጥራ የምታስተናግደውን ሴተኛአዳሪ በይፋ ሲቃወም ሴተኛአዳሪዋ ጋ አብሮ የሚያመሸውን፣ እስከ ሌሊት በመጠጥ ኃይል የሚሌስነውን ብሎም ባህሉን በመጠጥ ጀግንነት የሚጥሰውንና አብሮ አድሮ ጧት ሲነጋ አዩኝ አላዩኝ ብሎ ሹልክ ብሎ የሚወጣውን ማንም ደፍሮ የሚያወግዘው የለም።

የሴተኛ አዳሪዎች የኢ-ሰብኣዊነት ሁነት ባለብዙ ዘርፍ ነው። ሴተኛአዳሪዎች ቢወዱ የማይታመኑ ቅን ቢያስቡ የማይመሰገኑ ናቸው። ለነሱ ይህ ነው የሚባል ስም ያለው በገ አመለካከት ህብረተሰቡ ሲያሳያቸው አይታይም። ለነዚህ ሴቶች ሕይወት ከብዙ አቅጣጫ በችግር የተከበበ ባለብዙ ዘርፍ ስቃይ ነው። የኑሮ መግፊያ ብለው የገቡበት የዝሙት ተግባር ስመ ሰባራ፣ አድርጓዋቸው በማህበረሰቡ የተናቁና የተዋረዱ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። እንደማንኛውም ሰው ደግነት የማያንሳቸው፣ የሚያፈቅሩና የሚያዝኑ ቢሆኑ አመኔታን የሚለግሳቸው የለም። ደግነታቸውን በደግነት፣ ፍቅራቸውን በፍቅር የሚመልስላቸው ሰው አያገኙም።

ሴተኛ አዳሪዎች ቃል ሰጥተው ቃልን ያምናሉ። እነሱ ይታመናሉ። ሌላው ግን ለነሱ ታማኝ ሳይሆን ይቀራል። የሰጡዋቸውን ቃል የገቡላቸውን መሀላ ጥሰው ይበድሏቸዋል። በዚህም የተነሳ ሰውን ይጠላሉ። የሚኖሩበትን ማህበረሰብ ይንቃሉ። እነሱም በማህበረሰቡ ይናቃሉ። እምነታቸውንም ይለቃሉ። ሲያምኑት የሚታመን አጥተዋልና። ውስጣቸው ባዶ

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

የሆነ ይመስላቸዋል። ሁሉም ነገር ባዶ ይሆንባቸውና ውስጣቸው ይመንናል። በማህበረሰቡ ውስጥ ቢገኙም ከሰው መሀል ያሉ ሳይሆን የሚመስላቸው በሰው መሀል ብቸኛ የሆኑ ገለልተኞች/ባይታወር/ ሆነው ይሰማቸዋል። ሰብኣዊ ፍጡር መሆናቸውን እስከመጠራጠር ይደርሳሉ። ምክንያቱም በተግባርና በፍላጐት መካከል ያለመጣጣም ችግር በሚፈጠርበት ጊዜ አንድ ሰው የተረጋጋ ሰብዕና አይኖረውም። ሰክን ብሎም ማሰብ ያዳግተዋል። በመሆንና በመምሰል መካከል ይንገላታል። ይጨነቃል፤ መምሰል መሆንን ሊሆን ባለመቻሉ። የሴተኛ አዳሪዎችም ሕይወት በእንደዚህ ዓይነቱ የስነልቡና ምስቅልቅል ውስጥ ይገባል። የፈለጉትን ለማግኘት ያልሆኑትን ሆነው ለመታየት የሌላቸውን ሰብዕና ሊላበሱ ይታያሉ። ስነልቡናዊ ግጭት የሚባለውም አንድ ሰው ሊሆን በሚፈልገውና በእውነተኛው ገፅታው ተግባር ላይ በሚውለው መካከል የሚታየው የጐላ ልዩነት ነው ማለት ይቻላል። ለዚህ ነው በሰው መሀል እየኖረች/ሩ ሰው መሆናቸውን የረሱ ከማህበራዊ ግዴታዎች ያፈነገጡ ባይታወር ፍጡር (alienation) ሆነው የሚንቀሳቀሱት። ለማንም ለምንም ደንታ የሌላቸው በመሆን ራሳቸውን በማህበረሰቡ ውስጥ እያኖሩ "እንግዳ" ሆነው ለመታየት ለየት ያለ የማስመሰል ሰብዕና በመጐናጸፍ በውስጣቸው ሀዘን፤ በውጫቸው ድሎት ያላቸው መስለው የሚታዩት።

ሴተኛ አዳሪዎች ከተለያየ ወንድ ጋር ገንዘብ ለማግኘት ተሰድበውም ሆነ ተደብድበው "የሚወጡት" ለራሳቸው ሕይወት ብቻ ሳይሆነ በስራቸው ያሉትን የሌሎች ሕይወት ለመታደግም ጭምር ነው። የነሱ አካል "ተሸጦ" በተገኘው ገንዘብ እነሱን መልሶ ለሚበጭቃቸውና በተሰማሩበት "የሥራ መስክ" ለሚያፍሩበት የሥጋ ክፋያቸውና በደምና በአጥንት ለተሳሰሩት ዘመዶቻቸው የሕይወት ቤዛ ይውላል። ይህ ነው የበለጠ ሰብኣዊ ማንነታቸውን ረግጦ ርካሽ ሸቀጥ መሆናቸውን የሚያሳየን። ሰው ሆነው ተፈጥረው "ሰው" ናቸው ብሎ የሚቆጥራቸው በመጥፋቱ ነፍሳቸውን ለሞት ይዳርጉታል። "ቃልማ ቃል እንጂ ሁሉን መጠቅለሉ፤/እኛም ሰው ስንባል እነዚያም በሙሉ" (ገፅ፤46) የሚለው የዮሐንስ ስንኝ ሴተኛ አዳሪዎች "ሰው" በሚለው ቃል ይጠቃለሉ እንጂ የሰውነት ባህርይ እንዳላቸው እንደማይቆጠሩ ያሳያል። ይህ ሁኔታ ሕይወታቸውን ሲኦል ያደረገባቸው መሆኑን አመላካች ነው።

የማህበረሰቡ አንድ አካል የሆነው ወንድ በነሱ "ሥጋ" ለመደሰት ማታ ማታ ወደ ሴተኛአዳሪዎች ሲከንፍ ባገኘው ደስታ ምስጋናን ሳይሆን ውርደትን፤ መውደድን ሳይሆን ጥላቻን መልሶ ለነሱ ግን ሥቃይን ፀፀትን አስርፆ ይመለሳል። ለወንዱ መደበቂያው ያው ሀብረተሰቡ ነው። በባህል ሽፋን፤ በሀይማኖት ሰበብ። ሴተኛ አዳሪዎችም ይህን መንታ ስለት

ያለውን ስቃይ ውበታቸው እስካለ ውስጣቸውን በውጫዊ የማስመሰል ደስታ ሸብበው ኑሮን በስቃይ ይገፉታል። ይህ "ልማዳዊ" የባህል ጠላት እያረሩ መሳቅን እየተጠሉ መውደድን ተላብሰው እየሞቱ ይኖራሉ። "ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል" የሚለው ህዝባዊ አባባል ለነሱ ተስማሚ ብሂል ነው። ሰብአዊ ተፈጥሮአቸው ከሰው በታች ተቆጥሮ ተዋርደው፣ ተረግጠው ከሰው በታች ቁልቁል ተሽቀንጥረው የሚኖሩት ኑሮ "መች የሚያስቆጥር ነው እነሱን ከሰው" ዮሐንስ እንዳለው ዓይነት ነው። "ሰው" የሚለው የወል ቃል እነሱን እንኳ የማይጠቀልል እንደሆነ ያስገነዝባል። የሴተኛ አዳሪዎች "ሙያ" "የመኖር ግዴታ" ከሰው እኩል ሊያስመድባቸው የማይችል እንደሆነ ዮሐንስ በስንኙ ያስረግጣል።

ዋና ወረታቸው ያላቸው ውበት፣
ያገኙት በውልደት የተፈጥሮ ሀብት፣
እስኪከስም ድረስ እስኪጠወልግ፣
በርጅና በሕመም በክሳት በማጣት ደርሶ እስኪባልግ።
ኑሮው ባይሳካ ሆድ የባሳቸው፣
መኖር ሥጋ ሽጦ የመራራቸው
አውጥተው አውርደው ሲያጡ ሌላ መላ
ሲጨፈልቃቸው የችግር አበላ
ያሥር ሳንቲም ገመድ ውላ በጉሮሮ
ትለያቸዋለች ከተጨነቁበት ከችግር እሮሮ (1990፣ 46)።

የሴተኛ አዳሪዎች መጨረሻ መራራ ሕይወት ኑረው መራራ ሞትን መጮንጨት መሆኑን ያጠይቃል። ኑሮ ለነሱ በምድርም በሰማይም ሲያል ነው። በዓለማዊ የምድሩ ኑሮ በባህል ሲገለሉ፣ ሲናቁና ሲሰቃዩ እንደኖሩ የአሟሟታቸው ነገር ደግሞ በሃይማኖት በተወገዘው ራስን በማጥፋት ሲሆን አካላዊ ሥጋቸው ብቻ ሳይሆን ነፍሳቸው መውደቂያዋ "እሳቱ ከማይጠፋ ትሉ ከማያቀላፋ" ከሚሉት ይሆናል። ስለዚህ የሴተኛአዳሪዎች የሰብአዊ መንጠፍ ጉዳይ (Dehumanization) በምድራዊ ሰው በሚታየው ብቻ ሳይሆን በወዲያኛውም ዓለም (life after death) ያለው ሳይቀር "ትንሳኤ ሙታን" የሌለው ሞት ነው። ሞታቸውም ከሌሎች ሰዎች ጋር እኩል እንደማይሆን ከወዲሁ አውቀውት በአካላቸውም በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም ሳይቀር እየሞቱ ኑረው ወደ ሞት ይጓዛሉ። "በቁመና ሲያል አካላቸው ገብቶ/ለግዴታ መኖር በከንቱ ተገዝቶ (ዮሐንስ፣ 1990፣ 46)" በቁማቸው ሲኦል

ገብተው በመጨረሻም ሲያል መውረዳቸውን ያሳያል። ማታ ማታ በግርግሩ፣ በጨኸት በሀሳታው ከመጠጡ ብዥታ ጋር በሳቅ የተጀመረው ጧት ለስቃይና ለእንጉርጉሮ ይዳርጋቸዋል። አዕምሮኣቸውን ሰላም ያሳጣቸዋል። ገላቸውን በሌሊት ለገበያ ያቀርቡታል። የቁም ገላዊ "ኪ.ወስካቸውን" በተለያየ የአለባበስ ስልት ሞሽረው ለውድድር ያቀርቡታል። የወንዱ ተሸራሚጭም ቀን ባህታዊ መስሎ በምክር ሰጭነት ሲመፃደቅ ማንነቱን በሌሊት የቀበሮ ባህታዊነቱን ያሳያል። የሴትን ባትና ጭን፣ ዳሌና ተረከዝ ወዘተ. እያወዳደረ በስንት ሊገዛት እንደሚችል የራሱን ግምት ይዞ ለዋጋ ክርክር ይቀርባታል። ይህ ነው እንግዲህ ሴቷን "ሽርመጣ"፣ "ዘማዊ"፣ "ሴተኛ አዳሪ"፣ ወዘተ. በማለት ራሱን በባህል አክባሪ መሳይነት ደብቆ ማታ የእንስሳት የባህርይ ተጋሪነቱን በይፋ የሚያሳየው። ሲሻው በገንዘቡ አልያም በጡንቻው ተጠቅሞ የፊለጋትን ሴት ገ•ትቶ ይወስዳል።

> አንድ ማታ ... ከአንድ ፈረንጅ ጋር ዝናሽ ቤት ይመጣል። ይኼ ፈረንጅ ፀሐይን ሁለት ብርጭቆ ውስኪ ጋበዛትና እንሂድ አላት። ሰው አለኝ አለችው። <u>ሃይለሚካኤል</u> ... ብድግ አለና "የኔን እንግዳ? አንቺ ምናምንቴ!" እያለ በጥፊ፣ በርግጫ፣ በክርን፣ በጡንቻ ሲያጣድፋት ጊዜ አፍንጫዋ ደማ፣ አይኗ አበጠ አምስት ቀን ተኛች። ስትተነፍስ ጐኗን እያመማት ብዙ ተሰቃየች። እስከዛሬ በደንብ አልዳነችም (ገፅ፣ 23)። (አፅንኦት የኔ)።

ሴተኛ አዳሪዎች በራሳቸው ሰውነት እንኳ መብት የሌላቸው መሆኑን ከላይ ከተጠቀሰው ጽሑፍ ለመረዳት እንችላለን። ከላይ ከተጠቀሰው ጽሑፍ በርካታ ሁነቶችን ለመገንዘብ እንችላለን። እነዚህንም ሁነቶች ፈልፍለን ምናወጣቸው በአንድምታ እንጂ ላይ ላዩን እንደተገለፀው ዓይነት ስናነበውና ስንተረጉመው አይደለም። ሃይለሚካኤል የፈረንጅ እንግዳ ይዞ ሊያስተናግደው የወሰደው ቡና ቤት ነው። ቡና ቤት የሚያስተናግዱት ደግሞ ሴተኛአዳሪዎች ናቸው። ፈረንጁ ፀሐይ የምትባለውን ሴተኛ አዳሪ ከጀላት። ስሜቱንም ሊያበርድባት አቅበዘበዘው። ስለዚህ ጠየቃት። ፀሐይ ግን ሌላ ሰው እንዳላት ገለፀችለት። ይህን ጊዜ ነው "የኛ ወንድ" ሃይለሚካኤል እንስሳዊ ባህርይውን ያሳየው። "የኔን እንግዳ? አንቺ ምናምንቴ!" የሚሉትን ቃላት ካሰማ በኋላ ፀሐይን ደበደባት። ለምን? እንግዳውን ማስተናገድ ነበረባት። እሷ በፈለገችው መልኩ ሳይሆን "እቃ" ናትና ወንዱ በፈለገው ጊዜና ሁኔታ መሆን አለበት። ሃይለሚካኤል እንደ ስሙ ሁሉን ነገር በጉልበቱ መፈፀምና ማስፈፀም የሚፈልግ ዓይነት ሰው ነው። ሴተኛ አዳሪዎችንም የሚመለከተው ዝቅ አድርጐ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ነው። ለዚህ ነው "የኔን እንግዳ?" ሲል በጉልበቱ የሚመካ መሆኑን ሲያመለክት፣ "አንቺ ምናምንቴ!" የሚለው ሐረግ ደግሞ ለሴተኛ አዳሪዎች ያለውን ንቀት አጉልቶ ያሳያል። ከሐረጉ በስተመድረሻ የገባው ትእምርተ አንክሮ የሚያመለክተው የንቀቱን መጠንና ልክ ከፍ አድርጐ አመላካች ነው። ሁኔታውን ጠለቅ ብለን ስናጤነው "አንቺ ምናምንቴ!" የሚለው ሐረግ ዝንቅ ትርጉም ያለው ነው። አንድምታው ባለሁለት ፈረጅ ነው። "ምናምንቴ" የተባለችው ሴተኛ አዳሪ የማትረባ ውዳቂ መሆኗን ባህሉን ተገን አድርጐ ሲያባሽቅጥ ምን ያህል የንቀቱ ብዛት ላቅ ያለ መሆኑን ሲያመለክት በሌላ መልኩ ደግሞ አንቺን ብሎ ሰው መራጭ ምን መብት አለሽና የሚል ስሜት ያዘለ ነው። ሁለተኛው ሁነት ደግሞ ዓይነቱም ሆነ ሁኔታው የተለየ ነው። "ምናምንቴ" የተባለችው ሴተኛ አዳሪ ጋ የሄደው ሃይለሚካኤል የውጭ ሰው ሌላ ዜጋ ይዞ ነው። ስለዚህ ለእንግዳው እንደ ስጦታ ያቀረበለት "የሰው እቃ" ነው። እንግዳውም አይቶና ተመልክቶ ቀልቡ ውስጥ የገባችለትን ፀሐይን መረጠ። ሁለት ብርጭቆ ውስኪ አጠጥቶ ሊቀብጥባት ፈለገ። የፈለገው ያለመሳካቱን የሰማው ሃይለሚካኤል እንግዳው የተዋረደበት ስለመሰለው የእንግዳውንም ሆነ የሱን ክብር ነክታለች ብሎ ያሰባትን "ምናምንቴ ሽርመጣ" የክብርና ሞገሱን ለማስከበር አጋር የሌላትን ሴተኛ አዳሪ በመምታት ማንነቱን ለፈረንጁ አሳየ። በአንፃሩ ግን ምናምንቴ ያላትን ያገሩን ልጅ መደባደቡ "አባቱን አያውቅ አያቱን ናፈቅ" አስመስሎታል። ሌላው የማንነት ብክነት የተገለፀበት የማንነት ውድቀትና ግሽበት የታየበት ሌላው ገፅታ ነው ለማለት ይቻላል። ሴተኛ አዳሪ በመሆኗ ንቀቱን ቢያሳይም እንግዳ እንድታስተናግድለት የሚያስገድዳትና የሚደበድባት ግን የተናቀችው "ምናምንቴ" የተባለችው መሆኗ ደግሞ ምን ያህል በማህበረሰቡ ውስጥ የማንነት መምታታት፣ የባህል ጨለምተኝነት እንደተፈጠረ የሚያመላክት ነው።

ሴተኛ አዳሪ ለመረገጥ እንደተፈጠረች በመቁጠር አቤቱታዋን ለመስማት እንኳ የሚችል አካል የለም። ብቸኛው አማራጯቸው የማይከለክሉትን እንምባ ማፍሰስ ነው። ይህንን ጉዳይ በድርሰቱ ውስጥ ተራኪው "ተኝታ ሳለ ልጠይቃት ገብቼ ስናወራ ለምን አትከሽውም?" አልኳት። "አንተ ደግሞ! ከመቼ ወዲህ ሽርመጣ ተረገጥኩ ብሎ የሚከሰው?" አለችና ማልቀስ ጀመረች። "ደሞ ብከሰውም እኔ ነኝ ምታሰረው ወንድመ ፖሊስ ሻለቃ ነው (ገፅ፣ 23)።" ለሴተኛ አዳሪዎች ሕይወት ከብዙ አቅጣጫ መራራ ነው። ባህላዊ ህጉ ብቻ ሳይሆን መንግሥታዊ ህጉም ለነሱ የቆመ አይደለም።

ሴተኛ አዳሪነት በማህበረሰቡ እጅግ የተወገዘ ድርጊት እና በሃይማኖትም ረገድ ከኃጢያት ስለሚቆጠር በህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት አናሳ ነው። ይህ መራራ

የሕይወት ገዙዋቸው ማንነታቸውን ከሰው በታች ያዋለው በመሆኑ ከዚህ ሕይወታቸው ያፍሮ የሚያወጣቸው "አጋር" አለመኖሩ ደግሞ ሌላው ስቃያቸው ነው። ወንዱም ቢሆን በማህበረሰቡ የሚመጣበትን የባህል ተፅእኖ በሃይማኖትም የሚከተልበትን ውግዘት ይፈራል። ስለዚህ እነዚህ ሴተኛአዳሪዎች ያላቸው አማራጭ ይህን ዓለም እስኪሰናበቱ ተገልለው እየኖሩ "መልፋትን" በፀጋ ተቀብለው መኖር ነው። እድሜያቸው እየገፋ ሲሄድ ግን ዘወር ብሎ የሚያያቸው አይኖርም። "አሁን የሷ ኑሮ ኑሮ ይባላል? በሀያ ዓመት ውስጥ ስንቱ ተኝታታል። ስንቱ ተደስቶባታል፣ ስንቱ አልፍታታል፣ ... ምስኪን ጠንፍ የለሽ (ስብሃት፣ 1993፣ 127-128)። እርጅናን ይፈሩታል እንጂ አያስቡትም። ባላሰቡት ሁኔታ ወዛቸው እየረገፈ ደምግባታቸው እየጠፋ እንደሚሄድ አይረዱትም። ለምን ቢሉ ማሰቢያ አካላቸው በሌላ ተወጥሯልና፤ ሕይወታቸው በሙሉ በማስመሰል የተመላና ጊዜአዊ ነው። ለምንም አይጨነቁም። ትተውታል። ከወንድ ጋር "ተላፍታ" ለምታገኘው ገንዘብ እንኳ የተዋርድኩበት የለፋሁበት፣ የተረገጥኩበት ነው በማለት ቁምነገር ላለው ጉዳይ አታውለውም። ማሰብ፣ ማስተዋልና ለነገ ማለት ምኗም አይደለም። "ምን መጣ ብዬ ነው እንዲህ ምጨነቀው? ልብስ ገዛሁስ አልገዛሁስ እቁብ ገባሁስ አልገባሁስ ለኔ ምን ልዩነት ያመጣል (ገፅ፣ 200)።" የሚለው አገላለፅ ሴተኛአዳሪዎች ተስፋ የቆረጡ በሰው የተጠሉና የተገለሉ በመሆናቸው በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታዩት ማህበራዊ እንቅስቃሴና እንደሰው ጥሮ ማደግን የማያስፈልጋቸው መሆኑን ይጠቁማል፡ "ለኔ ምን ልዩነት ያመጣል?" የሚለው አባባል ትልቅ መልዕክት አለው። "እኔ" የሚለው ተውላጠስም ሴተኛአዳሪዋን በቀጥታ የሚጠቁም ሲሆን ሴተኛአዳሪዎች ለራሳቸው መጨነቅን ማሰቡን እርግፍ አድርገው የተውት መሆኑን ያሳያል። "ምን ልዩነት ያመጣል" ስትል በሁሉም ረገድ ተስፋ መቁረጧን ያሳያል። ገንዘብ አግኝቶ ለብሶና አጊጦ መታየቱ ለነሱ የሚያመጣላቸው ሰዋዊ የሆነ ክብር አለመኖሩን ያመለክታል። አምረው ቢታዩ ማታ ለሰከረው "ማብረጃ" ከመሆን ውጭ በማህበራዊ ኑሮ እንቅስቃሴ ውስጥ ከመናቅ በባህል ከመገለል፣ በሃይማኖት ከመወገዝና ከመኮነን የሚያስጥላት አለመሆኑን በመረዳት ተስፋ እንድትቆርጥ አድርጐታል።

ለነሮዋቸው የሚያስቡና የሚጨነቁ ቢኖሩም እንኳ በህብረተሰቡ ዘንድ ያለው አተያይ ማሰብና መጨነቅ እንደማይችሉ ተደርጐ ነው።የሚከተለውን ለአብነት ያክል እንመልከት።

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

ማሰቢያ አንገሳቸውን መጠጥ-ገንዘብ-መጠጥ-ወሲብ-ጌጣጌጥ አበስብሶ እንደ ትንሽ ልጅ አድርጓቸዋል። የአንድን ነገር ጥቅምና ጉዳቱን አመዛዝነው አይተው ይኼ ይጠቅመኛል ብለው ለማሰብ የሚችሉ <u>ሽርመጦች</u> በጣም ጥቂት ናቸው አብዛኛዎቹ <u>ደንብን</u> <u>መከተል</u> ማለት የሚደረገውን እያዩ ማድረግ ብቻ ነው (ስብሃት፣ 1993፣ 203 አፅንኦት የኔ)።

ሴተኛ አዳሪዎች በአስተሳሰብ ያልበሰሉ፣ በአመለካከት ያልበለፀጉ ልክ እንደህፃን በሂደት የሚማሩ እንጂ የማይጨምሩ ተደርገው በህብረተሰቡ ይታያሉ። ይህም አመለካከት በራሳቸው በሴተኛ አዳሪዎች ውስጥ ሰርፆ በአስተሳሰባቸው ጭምር ውድቅ ተደርገው እንዲታዩና እነሱም እንዲቀበሉት ተደርጓል። ምንም ጥሩ ነገር ቢሰሩ እንኳ ሴተኛ አዳሪ በመሆናቸው ብቻ በመልካም አይታዩም። ምንም ጥሩ ቢሆኑ በጥሩነት የሚፈርጃቸው የለም። ክንፈ በማሚት ፍቅር ተለክፎ የኮሌጅ ፈተናውን አልፈተንም በማለቱ ያጐቱ ልጅ እሸቱ ስለማሚት ከሚገልፀው የተወሰኑ ሀሳቦችን መዘን ብንመለከት ሴተኛ አዳሪ ምንም መልካም ቢሆኑ ምስጋናቸው እንኳ ስድብን ያዘለ ውስጡ በአሽሙር የታጀበ ነው። "እቺ ማሚት እኮ ምንም አትል ይለዋል ሽርመጣማ ባትሆን በጣም ጥሩ ሴትዮ ነበረች። ከልቧ ትወድሀለች" (ስብሃት፣ 1993፣ 155 አፅንኦቱ የኔ)።

ይህ የሚያሳየው በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የተዛባ አመለካከት ነው። እሸቱ እዚህ ላይ አንዱ የማህበረሰቡ አባል ነው። ምንም ያህል የማሚትን ጥሩነት ቢረዳ ሴተኛአዳሪ ስለሆነች ብቻ ጥሩ አይደለችም ነው እያለው ያለው። ይህ አስተሳሰብ የእሸቱ ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡ እምነት ነው። ይህ እምነት በእሸቱ ላይ ሰርፆ ጐልቶ እንዲወጣ ነው ተራኪው ያደረገው። ይህም ሴተኛ አዳሪዎች መልካምም ሰሩ ክፉ በህብረተሰቡ ዘንድ በበጐ የማይታዩ መሆናቸውን የሚያስጨን ነው።

ሴተኛ አዳሪዎች በችጋር ምክንያት የገቡበት "ሙያ" ከባህላቸውና ከማህበረሰባቸው እንዲገለሉ አድርጓቸዋል። እነሱን የሚረዳቸው ሰው ወይም ተቋም ስላጡ፣ የችጋር ሰለባዎች፣ የሰብአዊነት መጎጠፍ፣ የስነልቡና ድቀት ተጠቂዎች ሁነዋል። ህብረተሰቡም "ሴተኛአዳሪ" ናቸው እያለ ከባህልና ወግ ያገላቸዋል። የህብረተሰቡ ክፍል የሚያከናውነው ማንኛውንም ሰብኣዊ ማህበራዊ ሕይወት ተካፋይ እንዳይሆኑ በስም ብቻ ይቀጣቸዋል። እነሱም ምን ደግ ቢያደርጉ ምን መልካም ቢፈፅሙ "እስየው!" የሚላቸው ስለሌለ የተሰማሩበት ሥራ "ስላስገለላቸው" እነሱም ህብረተሰቡን ጠልተው፣ ተገልለው ይኖራሉ።

የሚኖሩበትን አካባቢ ችላ ብለው፣ በውስጡ ታቅፈው የሚኖሩበትን ህብረተሰብ ንቀው ይኖራሉ። በገቢርም ሆነ በነቢብ ስነምግባር ተብሎ ነገር ለነሱ ምናቸውም አይደለም። ህብረተሰቡ ገዝቅ አድርገው እንደሚያቸው ሁሉ እነሱም ህብረተሰቡን ንቀው፣ ባህላዊ ህጐቹንም ረግጠው ፍጹም "አይባሌ" እና "አይደፈሬ" የሚባሉትን የህብረተሰቡን ባህላዊ ህጐች ጥሰው ራሳቸው በፈጠሩት ዓለም ይኖራሉ። በድርጊት ለሚፈፅሙትም ሆነ በአንደበት ለሚናገሩት ነገር ሁሉ "ጥንቃቄ" ይሉ ነገር የላቸውም። የውስጥ ብሶታቸውን የሚያወጡት ህብረተሰቡ "ሀራም" ወይም "ፀያፍ" ናቸው ብሎ የማይናገራቸውን ቃላት ሳይቀር በመናገር ምፀታቸውን ለህብረተሰቡ ይገልፃሉ። ምንም እንኳ ይህ ጉዳይ በሌሎች የህብረተሰቡ ክፍሎች "ትክክል አይደለም" ቢባልም ለነዚህ ሴቶች ግን "ትክክል" ወይም "ትክክል ያልሆነ" የሚለው የባህል ገደብ ምናቸውም አይደለም። ህብረተሰቡ እነሱን እንዳገለለ ሁሉ ሴተኛ አዳሪዎችም ህብረተሰቡን አግለው ለባህሉ የማይገዙ ራሳቸውን ያገለሉ ሁነው ይኖራሉ። ይህንን በቁም የመረሳት ሁነት ፀጋየ በቅኔው እንደሚከተለው ፈክሮታል።

ልቤ ልቤን ሲያማክረው
"በቁም መረሳት መጥፎ ነው!"
እንኳ ቢለው
ዳኝነት የእግዜር ነውና እኔም ፍረደኝ የምለው
"እውነትስ ምንትስ ማነው?"
እያልኩ ነው (ፀጋዬ፣ 1965፣ 74)።

ይህ ደግሞ ሴተኛአዳሪዎች በቁም የተረሱ የመሆናቸው ነገር ውስጣቸውን እያቃጠላቸው "ዳኝነቱን" ለሰው ሳይሆን ለእግዜር መስጠቱን ይመርጣሉ። እነሱን "ምንትስ" የሚላቸው የህብረተሰብ ክፍል ራሱ ማንነቱ ጥያቄ ውስጥ የገባ ማንነቱ የተምታታበት መሆኑን የሚያጠይቅ ነው።

3.3 መጎልየ መጎልይ ዘካዛንችስ

> Literature has ... a social function, or use, which can not be purely individual. Thus a large majority of the questions raised by literary study are, at least ultimately or by implication, social questions: Questions of tradition and convention, norms and geners, symbols and myths. (Rene wellek and Austin warren. Theory of Literature 94)

3.3.1 መግቢያ

ይህንን የስነጽሑፍ ሰዎች አባባል ያመጣሁበት አቢይ ምክንያት ይገርው የተነሳሁትን አስተሳሰብ ይደግፍልኛል በሚል እምነት ነው። አንድ ስነጽሑፍ የሚፃፈው ያለበትን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግና ልማድ ከኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ገጽታዎች ጋር አቆራኝቶ የማህበረሰቡን ባህርይ፣ ድርጊት፣ ምናብና ስነልቦናዊ አመለካከቱን ለማሳየት ነው። ታሪኩን የሚተርክልን ደራሲ በምናብ በፈጠራቸው ገጸባህርያት አንደበት የዘመኑን ሁኔታ፣ የሰዎችን ድርጊታዊ እንቅስቃሴ ደግሞ ከሀሳቶችና ከሁኔታዎች ጋር አቀናጅቶ ያቀርባል። ስነጽሑፍ በዘመኑ የሚኖሩትን ሰዎች አመለካከት፣ አስተሳሰብና ድርጊት የሚያሳይ ሆኖ የሚከተብ ነው። የዘመኑን ሰዎች አጠቃላይ ባህርይ፣ ድርጊትና ምናብ እንዲሁም ስነልቡና የሚያሳይ አሻራ የያዘ ይሆናል። ከዘመኑ ውጭ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም። ለዚህ ትልቁ ምክንያት ደግሞ ደራሲው የማህበረሰቡ አንድ አባል በመሆኑ፣ የሚጽፍበትን ጥሬ ሀብት የሚያገኘው ከሚኖርበት ማህበረሰብ ሲሆን የሚቀበለውም ያው ማህበረሰብ ስለሆነ የሚደርሰው ስነጽሑፍ የዚያን ዘመን ሕይወት የሚያሳይ እና ድርጊቶቹም የዘመኑን አሻራ የያዙ ሆነው መቅረባቸው የግድ ነው። የሚፃፍበትም ቋንቋ የሚገለጽበት የአነጋገር ዘዬ ሁሉ የማህበረሰቡን ባህርይ፣ ድርጊት፣ ወዘተ. ማንነት የሚገልጹ ናቸው። የሚገለጸውም ሕይወት ነው። ሕይወት ደግሞ ማህበራዊ ክስተት ነው። ይህንን ሕይወት የሚተርከው ደራሲ ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ ቦታ አለው። የሚጽፍበትን ገጠመኝ የሚያኘው ከዚያው ከማህበረሰቡ ነው። መጎልየ መጎልይ ዘካዛንችስን ስናነብ በአዲስ አበባ ካዛንችስ ውስጥ ስለአለ አንድ የሕይወት መልክ እናገኛለን። ይህም የሕይወት መልክ ምን ገጽታ እንዳለው በስነጽሑፉ ውስጥ ደራሲው ምንም ባልተቀባባ ሁኔታ፣ በተፈጥሮ ቋንቋ፣ በተፈጥሮ ህግ፣ በግልጽነት

ይነግረናል። ደራሲው ሳይፈራና ሳያፍር የካዛንችስን ትዕይንት ምን ይመስል እንደሆነ አሳይቶናል። የጠቅላላ የካዛንችስ ድባብ ፀሐይ ስሌላው ስትጠልቅ ሰሷ የምትፈነጥቅ ሌላው የአዲስ አበባ ሕይወት ሲያንቀላፋ እሷ የምትነቃበት መሆኑን ያሳያል። በመጽሐፍ የመጀመሪያ ገጽ ላይ "ጀምበር ስታዘቀዝቅ" በሚል ርዕስ ስር "የአዲስ አበባ ሰማይ ሊመሽ ቀልቷል። የካዛንችስ ሰማይ ሊነጋ ጠቁሯል። ካዛንችስ ሥራ ልትጀምር ነው። (ገጽ፣ 1)" በተገለጸው ዐረፍተነገር ውስጥ የተሰመረባቸውን ሁለት ቃላት ልብ ብለን ብናጤን "ቀልቷል" እና "ጠቁሯል" የተሰኙት ተቃራኒ ፍች ያላቸው ናቸው። ቀሪው የአዲስ አበባ ሕይወት የቀኑ የብርሃን ክፍለ ጊዜ እያለቀ የማታውን ለመቀበል እና እረፍት ለማድረግ በሚስናዳበት ጊዜ ካዛንችስ ግን ለሥራ የምትሰናዳበትና የምትጣደፍበት ሰዓት እየመጣላት ነው። ሰማዩ ሊመሽ "ሲቀላ" ሰማዩ ሊነጋ "ጠቁሯል" ፍጹም የማይቀራረቡ ተቃራኒ አገላለጾች ናቸው። እነዚህ አገላለጾች ስነጽሑፍን እንደምን እንደምናነበው እንዴትስ እንደምንገነዘበው እና የትንታኔ አንድምታችን ምን ሊመስል እንደሚችል የሚያመላክቱ ጠቋሚዎች ይመስሉኛል።

ድርሰቱ በግርድፉ እንደሚነግረን የሰካራሞችን እና የተሸራሚጮችን ገድል ለማሳየት የተፃፈ አይደለም። በተራኪውም ይሁን በገጸባህርያቱ አማካይነት የሚተላለፈው ንግግርና ድርጊታዊ ክንውን ውስጥ፣ ውጭ እና ጀርባ እምቅ እና ምፀት አዘል የሆኑ የነገረ-ሰብ ሐሳቦች ወይም ትዝብቶች ይገኛሉ። የነዚህ እምቅ ሐሳቦችና ትዝብቶች መካተቻና መከሰቻዎች በይፋ የሚባሉት ተፈጥሮአዊ ቃላትና ተፈጥሮአዊ ሰዋዊ ግዴታዎች ወይም ህጐች ሳይሆኑ በምፀት መሰል አባባሎች በተቃራኒ ቃላት አማካይነት እንደዋዛ ጣል የተደረጉት አይመስሌ ቃላት፣ ሐረጐች ወይም አረፍተነገሮች ናቸው። እነዚህ ናቸው መጽሐፉ እንደስመ "መጎልየ መጎልይ ዘካዛንችስ" ሳይሆን ከአማላይ ስመ በስተጀርባ እንደወረደ ከተገለጸው ገድለ ሽርመጥና እና ስካር ሌላ ቆም ብላችሁ የምታዘክሩት አቢይ ጣጣ አለ ብለው የሚነግሩን። ይህንን ነው አገልተን በማውጣት ለማሳየት የሚጣረው። ይህ ምኑ ይነበባል፣ ብልግና እና ፀያፍ አባባል የታጨቀበት ድርሳን ነው፣ የሚሉትም ራሳቸውን ከበቀሉበት ማህበረሰብ ውስጥ የሚታየውን "ስክረን እና ስክረን ስንሸረሙጥ ምን እንመስላለን? የሚለውን እጅግ በጥቂቱ እንዲያጤኑ ልብ ያሰጣል። ይህም ካልሆነ አተረጓጐም ለየቅል ነውና አይደለም ለሚሉትም የግድ ይሁን አልልም።

ከዚህ በታች የማቀርባቸው ሐሳቦችና አስተያየቶች ከፍ ሲል በእናኑ አገኖናፍር ሴተኛ አዳሪ እና በስብሃት ገብረእግዚአብሔር ሌቱም አይነጋልኝ ድርሰቶች ከሰጠኋቸው ሐሳቦችና አስተያየቶች ብዙም የተለየ አይደለም። ሴተኛ አዳሪ እና ሌቱም አይነጋልኝ ድርሰቶች

የዘመን አንድነት ያላቸው ናቸው። ሁለቱም ከተደረሱበት ዘመን አንፃር ስንመለከታቸው አንድ ያደርጋቸዋል። የሴተኛ አዳሪን ሕይወት ምን ይመስል እንደሚችል ያቀረቡበት ስልት እና ቃና ይለያይ እንጂ የሴተኛ አዳሪነትን "ሙያ"፣ የሴተኛ አዳሪን ማህበራዊ ውርደት፣ ንቀትና ያለባቸውን ኢ-ሰብኣዊ የሆነ ሁነት ለማሳየት የተጠቀሙበት መቼት ተመሳሳይ ነው። ይኼውም "ቡና ቤት"። ልዩነታቸው ደግሞ በሴተኛ አዳሪ ድርሰት ታሪክ የሚነገረን በአንዲት ሁሉ አወቅ በሆነች ገጸባህርይ አቀንቃኝነት ሲሆን በሌቱም አይነጋልኝ ግን በረከት ያሉ ገጸባህርያት በሀሳብና በድርጊት ሲሳተፉ ይታያል። መጎልየ መጎልይ ዘካዛንችስ የተፃፈው ሁለቱ ድርሰቶች ከታተሙ ከአራት አስርት ዓመታት በኋላ ነው። ሆኖም በሁለቱ ድርሰቶች የተነሳው ሀሳብ በዚህኛው የበለጠ የማህበራዊ ህመም ሽርሙጥናው ተስፋፍቶና ጠንክሮ የቀነ ብርሃን የማንነታችን መደበቂያ፣ የባህላችን ማንነት ማድፈጫ ሆኖ "ትክክለኛው" ባህርያችንና ሰብእናችን መከሰቻ ደግሞ ምሽቱና ሌሊቱ መሆኑ ኧረ እኛ ማንን ብለን ራሳችንን እንድንመረምር የሚያደርገን ሆኗል። ስለሆነም በሁለቱ ላይ የተነሳውን ጨምሬ ይኼኛውንም አክየ ሶስቱ ድርሰቶች የሚያነሷቸውን የሴተኛአዳሪን ኢ-ሰባኣዊ የድርጊት ክስተት፣ የመገለልና የመናቅ በሰው መሀከል የባይታወርነት ስሜት በማጉላት ወደ አንድ መሠረት ሀሳብ እንዲያመሩ ከፍ ሲል የጠቀስኳቸውን ጠቋሚ ቃላት፣ ሐረጋት እና አባባሎች ማሄጃ እና ማጉልመሻ እንዲሆኑ ለማሳየት እሞክራለሁ።

3.3.2 ትንታኔ

መጎልየ መጎልይ ዘካዛንችስ ሲነበብ ብዙም ያልተወሳሰበ እና አንብቦ ለመረዳት (በውስጡ እንደወረደ የተገለጹትን ቃላት፣ አባባሎች ወዘተ. በግልጽነት ለተቀበለ) የሚያስቸግር ድርሰት አይደለም። ድርሰቱም የሚያወራው ስለምንድን ነው? የሚል ጥያቄም የሚያስነሳ አይመስልም። ለምን ቢሉ መልሱን "ደፋር" አንባቢ ሳይጨነቅ የሚያገኘው ነው። ይኼውም በሴቶች እና ወንዶች "ተሸራሚጮች" አንደበት የሚነገረው ገድለ ሽርሙጥና እና ስካር ነው። ከድርሳነ ሽርሙጥናው ልቆና ገኖ የሚታየው የሴት "ሽሌዎች" አስከፊ ሕይወት ነው፤ ለሚለውም አስተያየት ሰጪ ተቃውሞ የለኝም ትክክል ነው። መጽሐፉን ያነበቡት አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ድርሰቱ ድርሳነ ወሲብ በበልግና ቃላት የተሞላ ነው። ከዚህ የዘለለ ምንም ፍሬ የለውም ከሚሉት ጋር ግን በፍጹም አልስማማም። ከአንድ ማህበረሰብ የወጣ ስነጽሑፍ የዚያኑ ማህበረሰብ ባህል፣ ወግና ልማድ ... ማህበራዊ ገጽታዎች ...

ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

ከዚያው የወጣውን ሰው ባህርይ፣ ድርጊት፣ ምናብ እንዲሁም ስነልቡናና አመለካከት (Rene wellek and Austin warren 94) ያሳያል ባማለት ይገልፃሉ። በመሆኑም የካዛንችስን ሕይወታዊ እንቅስቃሴ አሁን ድርሰቱ ከተፃፈበት ውጭ ለመግለጽ ሌላ የተሻለ የለዘበ አባባል ሊኖር ቢችልም፣ እውነታውን ግን ደብቆ እስከመቼ የሚል አቋም አለኝ። በሌላ ጐኑ ደግሞ የተገለጸበት ያፃፃፍ ስልት፣ የቃላት አመራረጥ፣ ካዛንችስ በመቼትነት ተመርጣ የሚታየውን የሕይወት ክስተት እንደሚከወነው፣ እንደሚደረገውና እንደሚነገረው ካልተገለጸ የማህበረሰቡን ሕይወታዊ እንቅስቃሴ አላንፀባረቁም ማለት ይሆናል። ደራሲው የማህበረሰቡ አባል እስከሆነ ድረስ በማህበረሰቡ ውስጥ የታዘበውንና የተመለከተውን እንደተመለከተውና እንደተከወነው አከዋወን አድርጐ ማቅረቡ አግባብነት ያለው ነው የሚል አቋም አለኝ። የሚገልጸውም የሕይወት እንቅስቃሴ የማህበረሰቡን ሕይወት መመሰል ካልቻለ ተአማኒነቱ ጥርጣሬ ውስጥ ይወድቃል። ስለዚህ ዝናዋን የምናውቃት ካዛንችስ፣ ውስጧን፣ ጓዳዋን የምናውቃት ካዛንችስ በለዘበና በተቀባባ ቋንቋ ቢገለጽልን ደራሲውን አናምነውም፣ አንቀበለውምም። በዚህ ምክንያት የካዛንችስን ሕይወት እንደተገለጸው መልኩ መገለጹ አግባብ ያለው ነው ባይ ነኝ።

አንባቢን ላለማልፋት የምመታቸው መላምቶች ወደምን እንደሚያመሩ ለመጠቆም ስል ከመጽሐፉ ከተራኪው ዲስኩር ውስጥ የተወሰኑ መረ አረፍተነገሮችን ልምዘዝ፡-

ሀ. የአዲስ አበባ ሰማይ ሊመሽ ቀልቷል። የካዛንችስ ሰማይ ሊነጋ ጠቁሯል።
ካዛንችስ ሥራ ልትጀምር ነው። (ገፅ፣ 1)

ለ. አዲስ አበባ ወደቤቷ ልትገባ ትተራመሳለች። ካዛንችስ ከጓዳዋ
ልትወጣ ታዘግማለች። (ገፅ፣ 31)

ሐ. ጎበዛዝት ሆይ! ለካዛንችስ ዘምሩ
አንቺ መሸሸጊያዬ ሆይ! ወደአንቺ አመራሁ
ጉንጮችሽ የሸቶ መደብ ናቸው። (ገፅ፣ 57)

እነዚህን ሶስት ሐሳቦች መነሻ አድርገን ነገሩን ስንመለከተው እውነት መጎልየ መጎልይ ዘካዛንችስ የሚገልጸው ወይም የሚያስተላልፈው መልእክት የተሸራሚጮችንና የሰካራሞችን ገድል ብቻ ለማሳየት የተፃፈ ነው? እንደወረዱ ምንም ሳይቀባቡ የተቀመጡትስ ቃላት "እውነት" "ብልግና"ን ለማሳየት ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን እንድናነሳና ከድርሳነ

ሽርሙጥናው እና ከገድለ ስካሩ በስተጀርባ ምን የነገር ሰብ ጣጣ፤ ምን ዓይነት የማህበረሰብ ማንነት ይንጸባረቃል የሚሉትን አንስተን እንድንመረምር ያስገድዱናል።

ከድርሳነ ሽርሙጥናው ይልቅ አሰቃቂና አስከፊ ሕይወት ስለሚኖሩት ሴተኛአዳሪዎች ("ሸሌዎች" እንደደራሲው አባባል) ሕይወት ይበልጥ እንድንመረምር ሰክረን እና ሰክረን ስንሸረሙጥ ምን እንደምንመስል?፤ የወንዶች ተሸራሚጮች በሴተኛ አዳሪዎች ላይ የሚያሳዩትን "ንቀት" ከባህሉ ጋር አገናኝተን እንድንመረምር የሚያደርጉ ጠቋሚዎች ስለሆኑ በነዚህ ሐረግ መነሻነት ከድርሰቱ ርዕስ አንፃር የማህበረሰቡን ምንነትና ማንነት አጉልተን ለማሳየት የሚያስችሉን ናቸው። ድርሰቱ ድርሳነ ሽርሙጥና ነው፤ ከፍ ሲልም በዚህ ታጋጊነት (frame work) በሚንሸራሸሩ ሀሳቦች አማካይነት የሴተኛ አዳሪዎችን አስከፊ ሕይወት የምንረዳበት ድርሰት ነው ብለን የምናቆምበት የሀሳብ አንድምታ ላይ ብቻ የምንደርስ አይመስለኝም። የማህበረሰቡን ማንነት የምናጠይቅበትም ነው የሚል አስተያየት አለኝ። የተደበቀውን ውስጣዊ ማንነታችንን ፍንትው አድርጎ አሳይቷል የሚልም አመለካከትም አለኝ። እነዚህም የማንነት ጥያቄዎች የሚወጡት በይፋ በተገለጹት አባባሎች ላይሆን ውስጥ ውስጡን በሚርመሰመሱት አልባሌ ቃሎችና ከላይ በጠቀስኳቸው አባባሎችና አገላለፆች መልክ ነው። ይህንን ነው አጉልቶ ለማውጣት የሚሞክረው። በድርሰቱ የተነገረው ይፋ አይባሌ ቃሎች፤ ሐረጎችና አባባሎች ለነዚህ "አልባሌ" ግን ዋጋ ላላቸው አባባሎች መጓጓዣ ወይም ማዔጃ መንገዶች ናቸው።

ነገሩን ከኔ አንፃር ስመለከተው የ "<u>መጎልየ መጎልይ ዘካዛንችስ</u>"፤ ካዛንችስ የምትወስደው እንደ መነሻ ነጥብ (focus of attention)፤ እንደማህበራዊ አውድም (social context) ሆና የሴተኛአዳሪን የሰብኣዊነት መጠፍ (Dehumanization)፤ የማህበረሰቡን የማንነት ንቅዛት፤ የባህሉንና የቋንቋውን ግልፅ ያልሆነ መግባቢያነትን፤ ሁነት ከተለያየ አቅጣጫ የምንመረምርባት ሰፊ ተምሳሌታዊ ደሴት ናት። ካዛንችስ በተለይ የተወሰደችበት ከ "ተራ ሰው" እስከ የ "ተከበረ" የሚባለው "ሰው" አንስቶ ካዛንችስን ይጎበኛል። ልዩነቱ ሌላ ቦታ ከ "ክብሩ" ጋር በሚሄድ መልኩ የሚፈጽመውን ዘማዊነት እዚህ በመጠንም በዓይነትም ልቆና ገዝፎ መፈጸሙ ላይ ነው። ከካዛንችስ ውጪ በረቀቀ በለዘበ መልኩ ሲካሄድ ካዛንችስ ሲመጣ ግን ድብቅነቱን አሸቀንጥሮ ጥሎ፤ ባገጠጠና ባፈጠጠ ድርጊታዊ ተሳትፎ መከወኑ ላይ ነው። ለዚህ ነው ሁሉም ወደ "ደሴቷ" ካዛንችስ የሚመጡት። <u>መጎልየ መጎልይ ዘካዛንችስ</u> የተባለው የካዛንችስን የሴተኛ አዳሪዎችን ድርሳነ ሽርሙጥና ለመደስኮርና

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

የሰካራም ወንዶችን ገድለ ሽርመጥና ለመስበክ አይደለም። የድርሰቱን ቁምነገር በዚህ ፈር (ጠገግ) ስንመለከተው መነሻውም ሆነ መድረሻው ይህ አይደለም የሚል አቋም አለኝ።

የሽርመጥናም አልነው የስካር ታሪክ በሁለቱም አንባር የሚነግረን ነገር ለሌሎች "አንድምታዊ" ሀሳቦች መረማመጃ ድልድዮች ሆኖ የሚያገለግል የታሪክ አወቃቀር ሂደት ያለው ነው። የጭብጡ ፈርጅ ይህ አይደለም። የተሰጠን የተከተበልን የታሪክ ፍሰት ግን ካዛንችስን መነሻ አድርጐ የቀረበ ስለሆነ የአንድምታችን ማጠንጠኛ ነው። የትኩረት አቅጣጫችን (focus of attention) የሚያርፈው ካዛንችስ ግለሰባዊ-ማህበራዊው ቅራኔ የሚያደላ ነው። አንባሩ ወደ ማህበራዊው የማንነት ጥያቄ የሚያመላክት ነው። መደባዊ ሚናው ደግሞ ግለሰባዊ ነፃነት ከማህበራዊ ተጫኝነት ጋር ቅራኔ ገብቶ ውስጣዊ ግጭቶች በቀን ብርሃን ታምቀውና ተብላልተው ውስጥ ውስጡን በ "ልበል-ልተው" (approach-approach-conflict) ተወጥረው በምሽት ብልጭታ አሳይተው በሌሊት እንደእሳተ ገሞራ ፈንድተው ማንነትን ፍጹም አቻ በማይገኝለት ሁኔታ ያሳዩበት ነው።

የድርሰቱ መነሻ "ኢ-ሰብአዊነት" ነው (አንብበን ለምንተረጉመው የአንድምታ ጥያቄና ጣጣ ሁሉ መነሻ የሚሆነው ሴተኛአዳሪነት) መጠቅለያው "የሰብአዊነት መንጠፍ"፣ የማህበረሰባዊ የ "ማንነት ንቅዘት" ነው። (በድርሰቱ አውድና ድባብ ውስጥ "ርህራሄ" የሌለው የማይኖረው የሰብአዊነት መንጠፍ እና የማንነትን ንቅዘት ነው።) የድርሰቱ ጠቅላላ ድባብ ኢ-ስነምግባራዊ እና ኢ-ባህላዊ ነው። ከሴቷም ሆነ ከወንዱ ተሸራሚጩች አንደበት ሀራም (taboo) ቃላት በድርጊቶቻቸው ደግሞ "ቅስም የሚሰብሩ" (non-moral) ሁኔታዎች የተሞሉባቸው ናቸው። ይህንን ሁኔታ የሚያጐለልን ሁኔታዎችና ቃለምልልሶች እና ድርጊታዊ ክንውኖች ምንድናቸው ብዬ ጠይቄ በምላሌዎች አስደግፌ ለማሳየት እሞክራለሁ። ትላልቅ የሚባሉ ሁነቶች (ለምሳሌ ጀምበር ስታዘቀዝቅ /ገፅ፣ 1/ ከሚለው ከመጀመሪያው ክፍል ጀምሮ እስከ "ከምሽቱ ሰባት ሰዓት በኋላ" /ገፅ፣ 177/) በውስጣቸው ከሚገኙት አንዳንድ መጠቆሚያዎች በስተቀር የድርሰቱ መነሻና መቋጫ ነገር አይደሉም። እነዚህ ሊተላለፍ የተፈለገውን የድርሰቱን ጨመቅ (ዮሐንስ እንዳለው) አጅበው በሰበካው የቀረቡ አንገብጋቢ እንጂ ጭምቅ ፍሬ ጉዳዩን አያሳዩም። "እነዚህና እነሱን የመሳሰሉት ትዕይንቶችና ትርኢቶች ማጎደር እንጂ ጎዳሪ አይደሉም፣ መከሰቻ (manifestation) እንጂ የድርሰቱ ጨመቅ (essence) ወይም ጭብጥ (theme) አይደሉም። (ዮናስ፣ 1992፣ ገፅ፣ 83)።

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

3.3.3 ፍካሬ[5]

3.3.3.1 አሀድ አንድ[6] (ምዕራፍ አንድ "ጀምበር ስታዘቀዝቅ")

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከታሪኩ ሂደት አንፃር ተራኪው የካዛንችስ ቡና ቤቶች ሰራተኞች በአስር እና በአሥራ አንድ ሰዓት ወደ ስራቸው ተጠቃለው መግባታቸውን በመንገር ይጀምራል። ተራኪው የካዛንችስን እለታዊ እንቅስቃሴ እና ምን ዓይነት ሁኔታ እንደምታሳይ በመጀመሪያው ምዕራፍ የመጀመሪያ አንቀጽ "የአዲስ አበባ ሰማይ ሊመሽ ቀልቷል። የካዛንችስ ሰማይ ሊነጋ ጠቁሯል። ካዛንችስ ስራ ልትጀምር ነው። (ገፅ፣ 1) ብሎ ከነገረን በኋላ ነው። የየቡና ቤቶቹ ሰራተኞች ከካዛንችስ ሰማይ ጋር ሊነጋገላቸው አብረው ጠቁረዋል። ከየአሰሪዎቻቸው የእለት ምድብ ሥራቸውን አውቀው ታዳሚዎቻቸውንና ደንበኞቻቸውን ሲጠባበቁ በየወንበሩ ተሰባስበው ስለትላንት ማታው "ገድል" ያወራሉ። ለመነሻነት ከመጽሐፉ የሚከተለውን ሀሳብ ልምዘዝ (ገፅ፣ 3)።

> ሴቶቹ በየወንበሩ ላይ ተሰብስበው ስለትላንት ማታው ገድል ያወራሉ። በዝነስ (ቢዙ) ያገኙቱ ... ስለአዳራቸው፣ ያጡቱ ስለዶርማቸው ይቀዳሉ። ሶስት አራት ሆነው ስለትላንት ማታው ... አሰካክራቸው አበላለጋቸው አስተዳደራቸው አፈነጋገላቸው ገገቢያቸው የአልጋ ገድላቸው የለሊቱ ውጣ ውረዳቸው ጎዘናቸው ክፍ ዝቃቸው አነጋገራቸው አመሻሻቸው መሸታው ... ያወራሉ። ይቀዳሉ።

እነዚህ ሴቶች ዛሬ ላይ ሆነው ጀምበር ስታዘቀዝቅ የሚያወሩት ያላለፉትን የማታውን ገድል ሸርመጣን ነው። ሴቶቹ ለዛሬው መጭውን እየጠበቁ ያላለፉትን ያለፈባቸውን የሰካራም

---

[5] ይህን የአፃፃፍ ብሂልና የፍካሬ ስልት የቀሰምኩት ዶክተር ዮናስ አድማሱ "አስረኛንኩዋ" ሀዲስ አለማዩሁና የማህበራዊ ሂስ ሥልታቸው" በሚል ርዕስ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ መጽሔት (1992) ውስጥ የቀረቡትን የአሠራር ስልት በመከተል ነው። በዚህ መጣጥፍ ውስጥ የሀዲስ አለማዩሁን ድርሰት ዘለግ ያሉ የንባብ አሀዶች (reading units of considerable length) ተብለው በሚፈቱ አሀዶች ከፍለው ያስተነትናሉ። ይህን ሥልት መከተሉ ለማንኛውም ድርሰት ፍካሬ ይበጃል የሚል እምነት የለኝም (1992፣ 84) በማለት ቢገልጹም እኔ ግን በምሠራባቸው ድርሰቶች ሴተኛአዳሪ፣ ሌቱም አይናጋልኝ እና መነልየ መነልይ ዘካዛንችስን በሳቸው ያፈካከር ስልት ለፊክሩ ያመቻሉ የሚል ግምት ስላለኝ የአሠራር ስልታቸውን ተከትያለሁ።

[6] ይህንን ቃል የወሰድኩትም ከእሳቸው ከተጠቀሰው ጽሁፍ ነው። ቃሉን ሳልቀንስና ሳላሻሽል ተስማሚ ሆኖ ስላገኘሁት ተጠቅሜበታለሁ።

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

ወንድ ተሸራሚጭ ትፋት፣ ቅርናት፣ ግማት፣ እንደዋዛ የሚናገሩ ይመስላሉ። አንዷ ለሌላዋ ሌላዋ ለሶስተኛዋ ይተርካሉ። እንደዋዛ። የወንዱን ተሸራሚጭ ዱላ፣ ኢ-ሰብአዊ የሆነ አወሳሰብ፣ ወዘተ. ሁሉ ይተርካሉ። ነገር ግን ከዚህ ትረካ በስተጀርባ የምንረዳው የምንገነዘበው ቁምነገር ያለ ይመስለኛል። አቀራረቡ ቀለል ያለ በተራ ቃላት የተዋቀረ የንግግር በሚመስል ቋንቋ የተዋቀረው የዓረፍተነገር ሀሳብ ጥልቅ የሆነ መልእክትን የሚያስተላልፍ ቁምነገር አለበት። በመነሻዬ እንደገለፅኩት ተራ በሚባሉ ቃሎች "ሀራም" ናቸው ተብለው በማህበረሰቡ በተገደቡ ቃላት የተገለጹት ሀሳቦችና ሁነቶች የሚያስተላልፉት ቁምነገር "ተራ" የሚባሉ አይደሉም። ከላይ ከተጠቀሰው ዓረፍተነገር ውስጥ ተራ የተባሉትንና "ሀራም" ናቸው የተባሉትን ቃላት ደርድረን እንመልከታቸው፤ አሰካከራቸው፣ አበላለጋቸው፣ አስተዳደራቸው፣ አፈነጋገላቸው፣ ገገርያቸው፣ የአልጋ ገድላቸው፣ ውጣ ውረዳቸው፣ ከፍ ዝቃቸው፣ ወዘተ. የሚሉት ቃላት የሚባሉትና የሚነገሩት በተራ ሰው ነው ልንል እንችላለን፤ ነገር ግን እነዚህ ቃሎች የሴተኛ አዳሪዎችን መናቅ፣ መዋረድ እና ዝቅ ተደርገው መታየት የሚጠቁሙ አመላካቾች ናቸው። ሴቶቹ በማህበረሰቡ ዘንድ የተናቁ፣ የተገለሉ መሆናቸውን ራሳቸው ሳይቀሩ አምነው ተቀብለውት ያሉ ለመሆናቸው የሚገለገሉበት የቃላት አጠቃቀም ጠቋሚ ነው።

ቁምነገሩ በሴቶቹ የሚነገረው የባህል ገደብን የለቀቀ "መረን" የሚባለው አነጋገር ወይም አባባል አይደለም። ተራኪው እንደሚለው ሴቶቹ በተፈጥሮና በህግ መብት የተሰጣቸው "ሴት" የሚለው መጠሪያቸው ሌላ ማንጠልጠያ ተቀጥሎለት ማህበረሰቡ፣ አብሯቸው የሚሸራሞጠው ወንድ ሳይቀር የቡና ቤት ሴት፣ ሸሌ፣ ሸርሙጣ፣ ሴተኛአዳሪ፣ ዘመናዊ ነኝ ባዩ ደግሞ "ባር ሌዲ" የሚሉዋቸው መሆኑ እና ስመ ብዙ መሆናቸው የሚያስከትልባቸው የስነልቡና ችግር፣ ወደ የማንነት ጥያቄ ውስጥ ከቶ ለከፋ የሰብአዊነት ንጥፈት የሚከታቸው መሆኑ ላይ ነው። ማህበረሰቡ ለነሱ የሚሰጠው ግምት የተዛባ መሆን ተስፋቢሶችና አቅመቢሶች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። የስማቸው መሰበር፣ የአቅማቸው መዳከም ከስነልቡናዊው ድቀት ጋር ተዳምሮ ሕይወታቸው ተስፋን የማትሻ ስለምትሆን የዛሬን እንጂ የነገን የማያልሙ ያደርጋቸዋል። ይህ ነው ተስፋቸው የጨለመ አቅማቸው የደከመ ስለሆነ የሚስማቸውን ስሜት፣ የሚፈጽሙትን ድርጊት፣ የማህበረሰቡን ባህልና ደንብ ሳያከብሩ እንደወረደ የሚያወርዱት። ለነሱ ባህል፣ ወግ፣ ሥርዓት፣ ወዘተ. ብሎ ጣጣ ምናቸውም አይደለም። ማህበረሰቡ አግልሏቸዋል፤ እነሱም አግልለውታል። ስለዚህ የሱን ወግና ልማድ እነሱን እንደደፈጠጣቸው ሁሉ፣ እነሱም የሚደፈጥጡት። "የአዲስ አበባ

ሰማይ ለመሸ ቀልጂል፣ የካዛንችስ ሰማይ ሊነጋ ጠቁሯል። ካዛንችስ ሥራ ልትጀምር ነው (ገፅ፣ 1)።

ከመጀመሪያው ምዕራፍ መጀመሪያው አንቀጽ ላይ የምናገኘው የታሪኩ አጀማመር ራሱ የሀሳብ አወራረዱን ያዋቀረው በተቃራኒ አስተሳሰቦች ነው። ካዛንችስ የአዲስ አበባ አንድ አካል የሆነችና በአዲስ አበባ ውስጥ የምትገኝ ስትሆን የሁለቱ ሰማይ ግን በአንድ የቀን ስሌት ውስጥ ፍጹም የተለያዩ ሆነው ቀርበዋል። የአንድ ቦታ ሰማይ "ገሚሱ ለመሸ ሲቀላ" ገሚሱ ደግሞ "ሊነጋ ሲጠቁር" ማየት ያልተለመደ የተፈጥሮ ክስተት እንደሆነ እንገነዘባለን። ይህንን ስናነብ ግን ምን ማለት ነው ብለን ይህንን አያመአዊ (paradoxical) የሆነ ሀሳብ ለጥያቄ ማቅረባችን አይቀሬ ነው። ይሁን እንጂ ቀስ ብለን የሀሳብ ፍሰቱን የአወቃቀር ስልቱን የአቀራረብ ብሂሉን ስናጤን እውነታውን እንረዳለን። አደናግር መስሎ የታየን ሀሳብ እውነት መሆኑን ስንረዳ ደግሞ ቆም ብለን ማህበረሰባችንን የበቀልንበትን ባህላችንን እና ፍጹም ግልፅነት የጐደለውን መግባቢያችንን እንድንመረምር አቀራረቡ ግድ ይለናል። በትልቁ ሰማይ አዲስ አበባ ለመሸ ጀምበር ስታዘቀዝቅ በሱ ጣራ ስር ያለችው ካዛንችስ ሊነጋላት ሰማዩ መጥቆሩ የሚያጠይቀው የተፈጥሮ ክስተት መሣባቱን ሳይሆን በተምሳሌት የቀረበው የማህበረሰባችን አመለካከት ልክ ያለመሆን ሚዛን ነው። አዲስ አበባ ወክሎ የቀረበው ሰፊውን የሀገራችንን ባህላዊ እሴት ሲሆን ካዛንችስ ደግሞ የባህሉን ተጋፊዎች ወይም ተቃዋሚዎች የሆኑትን የማህበረሰብ ክፍል ነው። ይህም በሰፊው የባህላችን ልዩ ልዩ እሴቶች ውስጥ የአመለካከት ችግር የአስተሳሰብ ጉድለት እና ግድፈት የመኖሩን ያህል ተቃውሚችን ደግሞ ይፋ ያልወጣ፣ ሲያሻን መጠቀሚያ ሳያሻን በድብቅ ፍላጐታችንን በጨለማ የምናሰማ አቋማችን ግልጽ ያልሆነ ስንሆን፣ ይህም የማንነታችን ምንነት ይፋ የወጣበት ለመሆኑ አመላካች ነው።ይህንን የማንነት መገደር ዮሃንስ እንደሚከተለው ዘርፎታል።

> ሁኗል መንፈሳችን ከውስጥ በስብሶ፣
> ቁሟል ቀጥ ብሎ አምሮ እንደምሰሶ፣
> ከውስጡ ቦክቡኮ ቁንቁን ቆርጥሞት፣
> መንፈሳችን ቁም ይመስላል ያማረ የቆመ በውነት።
>
> (እስኪእንነጋገር፣ 1990፡ 96)

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

ዮሐንስ በቅኔው እንደፈከረው "በመንልየ መንላይ ዘካዛንችስ" የሚታየውና የሚፈጸመው ካዛንችላዊ ሕይወት ውስጡ በስብሶ ውስጡን ቁንቁን እንዳነከተው አቁዋመ መልካም ዛፍ ይመስላል። የማህበረሰቡ ማንነት ውስጡ "ቦክ ቡኮ" ላይ ላዩ ሲታይ ግን ያማረ የሚመስል በማስመሰል የተገደረ ነው። ማህበረሰቡ ማንነቱ በመንፈስም ሆነ በህሊና ተሸርሽራል። አቋመ ገጹ ያማረ መስሎ ቢታይም የበሰበሰና የቦከቦከ መሆኑን ግን ጀምበር ስታዘቀዝቅ ከሰፊው ባህር-አዲስ አበባ ወጥቶ በካዛንችስ "ደሴት" ያሳያል። ደሴቷ-ካዛንችስ ለሁሉም እጇን ዘርግታ ወደ ጉያዋ ታስገባለች። በቀን ብርሃን ማንነቱን የደበቀው ማህበረሰባዊ ተጋፊ ግላዊ ሰው እሱን መሰል አቻውን ወደሚያገኝበት ካዛንችስ ያመራል። አንድና ሁለት አልኮል ሲቀምስ ውስጡ እየተፍታታ "የመገሙሮች ሁሉ መገሙርን" መንልየ መንልይን የካዛንችስን ቅኝት ያዜማል። በዜማ ተነቃቅቶ በመጠጥ ተነሳስቶ የቦከቦከውን ውስጣዊ ስሜቱን ያነቃል። የሚገደርበት ባህል፣ ወግ፣ ወዘተ. ርግፍ ብለው ከላዩ ይነሱና የተጣባው የሱነቱ ማንነት ቦታውን ይቆጣጠራል። በቀን የተቀማውን "ግላዊ ነፃነት" በካዛንችስ ከምሽት እስከ ለሌት በመጠጥ ኃይል በመዚቃ አነሳሽነት ይጐናፀፋል። የተጫኑት ማህበራዊ ልማዶች አሁን ቦታ የላቸውም። ካዛንችስ የነፃነት ፈላጊዎች "ነፃ መሬት ናት"። የአዲስ አበባ ሕይወት ሲያንቀላፉ የካዛንችስ ሕይወት የሚያንሰራራበት ነው። "ሰማዩ ሊነጋ ጠቀሯል"፣ "ካዛንችስ ሥራ ልትጀምር ነው" የሚሉት ሁለት ሀሳቦች የሚያስተላልፉት መልእክት እንዲሁ የሚታለፉ አይደሉም። "ሰማይ" የሚለውን ቃል "ካዛንችስ" በሚለው የቦታ ስማዊ ቃል ብንተካውና ሌሎቹን ብናስከትል "ካዛንችስ ሊነጋ ጠቀሯል" የሚል ይሆናል። የሀሳቡ መጠቅለያ ግስ ደግሞ "ጠቀሯል" የሚለው ነው። ይህን ግስ ተክትሎ መግባት የነበረበት "ሊነጋ" የሚለው መስተዋድዳዊ ቃል ሳይሆን "ሊመሽ" የሚለው መሆን ነበረበት። ነገርግን የሀሳብ አቀራረቡ ምፀታዊ ነው። የሀሳብ ፍሰቱም አያዊ (paradoxical) ስለሆነ የማህበረሰቡን ህጸጽ በምፀት ሲሸነቁጥ ነው። ጀምበር ስታዘቀዝቅ ካዛንችስ ስራዋን ልትጀምር ስትሰናዳ ወደ እሷ የሚመጡት ታዳሚዎች እንደመልካቸው ቀለም እንደስማቸው ብዛት ውስጣዊ ፀባያቸው ባለብዙ ፈርጅ ነው። የባህርያቸውን ዓይነትና መጠን በመጠጥ ኃይል በሌት አስተናጋጆች ላይ ያሳያሉ። ሴቶቹ (እንደ መጽሐፉ "ሽሌዎቹ") ወደ "ደሴቲቱ" ለሚመጡት ወንድ ሽሌዎች የሁለንተናዊ ባህርያቸው መከሰቻ ናቸው። ማህበራዊ ልማድ የነፈጋቸውን ፍላጐት የተጫናቸውን ስሜት አምቀው ያቀፉትን ውስጣዊ ብሶት የሚያወጡት ካዛንችስ በሚገኙ "ሽሌዎች" ነው። እያንዳንዱ የምሽት የካዛንችስ "ወንድ ተሸራሚ" በወሬ የሰማውን በፊልም ያየውን፣ ወይም በልምድ ያገኘውን የወሲብ ገድል

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

በሴታ "ሽሌ" ላይ ሊተገብር ይፈልጋል። ፈቃደኛ ከሆነች በሰላም፤ ካልሆነች ጡንቻውን ተጠቅሞ እንስሳዊ የባህርይ ተጋሪነቱን ያሳያል። በካዛንችስ ሰማይ ስር በምሽት "ቀን" ነው። ገድለ "ብልግናው" ምሽቱ በጨመረ ቁጥር ዓይነቱና መጠኑ ይጨምራል፤ ይለያያል። ካዛንችስ ሌላ ራሷን የቻለች አለም መሆኗን የምታሳይበትና የምትገልጥበት ወቅት ይሆናል። ከመፅሀፉ የሚከተለውን ሀሳብ እንመልከት።

> ... የቀኑ ውጣ ውረድ፤ ብርሃን፤ ይሉኝታ አዩኝ አላዩኝ፤ ስነምግባር፤ ፍርሀት፤ የማህበረሰብ ደንብ፤ ባህል፤ ወግ፤ ልማድ፤ ... ሁሉም በየቤታቸው ገብተዋል። ... ጠጪና ተሸራሚጩ ከዚህ ቤት እዚያ ቤት ይሄዳል። በእያንዳንዱ ቅያስና በየጥጋጥጉ ፓትሮልና ተዘዋዋሪ ሽሌዎች ተኩልኩለዋል። ... ጐዳናዎች ከካዛንችስ ጓዳዎች በሚወጣው የሙዚቃ ድምጽ ተሞልተዋል። ... አዲስ አበባ በእንቅልፍ ልብዋ ማሸለብ ጀምራለች መሸላት። ካዛንችስ ከእንቅልፏ ሙሉ ለሙሉ ነቅታ-ተፀዳድታ-ተጣጥባ-ለብሳ አምራ ስራዋን ጀምራለች-ነጋላት። (ገፅ፤ 56) (አጽንኦቱ የኔ)

ካዛንችስ ከምሽቱ ሶስት ሰዓት በኋላ ቀን በብርሃን ካንቀላፋችበት ሙሉ በሙሉ ነቅታ ታዳሚዎቿን የምታማልልበት ወቅት ነው። ታዳሚዎቿም በብርሃን "የሚፈሩትን"ና የሚያከብሩትን ማህበራዊ ወግና ልማድ እርግፍ አድረገው በመተው የካዛንችስን ሕይወት ማጣጣም የሚጀምሩበት ሰዓት ነው። ለምን? አዲስ አበባ አንቀላፍታለች። ግለሰባዊ ትዝብት፤ ባህላዊ እና ሐይማኖታዊ ውግዘት፤ ወዘተ. የሚሉት ጣጣ በዚህ ሰዓት የለም። ሁሉም የማህበራዊ ተጫኝነትን በመቀበልና ባለመቀበል መሀል ሆኖ ሊያቅማማ የነበረ ጐበዛዝት "ካዛንችስ መሸሸጊያ መደበቂያ እያለ በስካር ዜማ እያወደሰ ለሕይወቱ እርካታን እሻለሁ ስለዚህ ወደ አንቺ መጣሁ" የሚልበት ወቅት ነው።

ከመጀመሪያው ምዕራፍ እስከ ስድስተኛው ምዕራፍ ድረስ የተረከ መንደርደሪያ ሆነው ያገለገሉት አረፍተነገሮች አዲስአበባንና ካዛንችስን የፊተኛውን ቀን ሲመሽበት፤ ውድቅትና ደረቅ ለሌት ሲሆንበት፤ የኋላኛው ደግሞ ማታ ሊነጋለት ሊረፍድበትና ሊቀትርበት መሆኑን በምፀት በማወዳደር ነው። የተረኩ አቀራረብ ደግሞ የሀሳብ አያያዝት ያለበት ነው። የየምዕራፉ ትኩረት በአንድ በኩል በአዲስ አበባና በካዛንችስ መካከል ያለውን የአንድ ቀን (የ24 ሰዓቱን ግማሽ ሌሊቱን/ምሽቱን ማለቴ ነው) ተመሳሳይ ሰዓቶች ሁለት የተቃረኑ የቀን ክስተቶች ሆነው መቅረባቸውን ሲያጐላ፤ በሌላ በኩል በካዛንችስ ስለራሳቸው

እጣ ፈንታቸው ምን እንደሚመስል የሚቆዙምበት ስለሌላው ከ "ሥራ ባልደረቦቻቸው" ጋር የሚጫወቱበት፣ ለዚህ ያበቃቸውን ማህበረሰብ እና ባህሉን እንዳገለላቸው አግለውት እንደናቃቸው ንቀውት ማንንም ሳያፍሩና ሳያክብሩ የማህበረሰቡን ደንብ በጣሰ፣ የባህል ገደቡን በናደ ቋንቋ የየቀን የየምሽትና የየለሌት ገድለ ብልግናቸውን፣ ስካርና የስካር ውጤት ድርጊቶቻቸውን በምፀታዊ ቃላት የሚመዘነብት ነው።

በየምዕራፉ መጀመሪያ አንቀጽ ላይ ወይም አልፎ አልፎ (በአብዛኛው በመጀመሪያው አንቀጽ ስለሚገኝ ነው) በምዕራፉቹ መካከል የአዲስ አበባ "ሕይወት ማንቀላፋቱን"፣ የካዛንችስ በአንባሩ "እየነቃና እያንሰራራ" መምጣቱን የሚጠቁመ አመልካቾችን ወይም ጠቃሾችን እናገኛለን። እነዚህ ሁለት ተቃራኒ መጠቆሚያዎች በየምዕራፉ ውስጥ በመገኘታቸው እንደ አንድ ተነበው የማህበረሰቡን አቋመ ሕይወት፣ የባህሉን ተጫኝነትና የባህሉን አፈንጋጮች ገድለ ተቃውሞ ልክና መጠን ምን ያህል እንደሆነ ልንፈክርበት የሚያስችሉ ናቸው የሚል አቋሜን ያጠናክራሉ። መፈክር አለበት ብየ ከማምነው የካዛንችስ ደሴታዊ ዝማሬ ቤቶች አማሏቸው የሚመጡ "ወንድ ተሸራማጮች" እና በችጋርም ይባል በሌላ ምክንያት በየቡና ቤቱ የሚያስተናግዱ የ "ሴት ሸሌዎች"ን ዕጣ-ፈንታ እንተረጉምባቸዋለን። ይህ አንድ ገጽ ነው። ሁለተኛው ገጽ አሁንም ከባህል እሴቶች (values) ውጭ፣ ያልተለመዱና የማህበረሰቡን ወግና ልማድ የጣሱ ኢ-ግብረገባዊነትን የሚያንጸባርቁ ወሲባዊ ግንኙነቶች በካዛንችስ መከሰታቸው ማህበረሰቡ አጠቃላይ ሰብእናው ውስጥ ውስጡን እንደቁንቁን ያቦክቦክው ግንድ በመሆኑ ይህ ውስጣዊ የሰብእና ንቅዘት፣ የሚያስከትልበትን የህሊና እና የመንፈስ ጭንቀት የሚገላገለው "በካዛንችስ ነፃ መሬት" በሚገኙ "ነፃ" ሴቶች-ሸሌዎች ነው። ለዚህ ነው ቀኑን ማንነቱን ደብቆ ምሽቱን መምረጡ። "ከአንገት በላይ ታቦት ከወገብ በታች ጣዖት" ይሏል ይህ ነው። ሁለተኛው ቁምነገር የተካተተው ማህበረሰብ የተጫነው፣ ባህል የገደበውና ሐይማኖት ያወገዘው ግለሰብ ከዚህ "ባርነት" ነፃ የሚያወጣው የካዛንችስን ቡና ቤቶች በምሽት ተራምዶባቸው፣ በለሌት ሲሮጥባቸው ነው። በካዛንችስ ቡና ቤቶች ፍላጐቱን ወደሚሟላበት ጓዳ ገብቶ መመሰግ ብቻ አይበቃውም። "መነልየ መነልይ ዘካዛንችስ"ን ይዘምራል (ገፅ፣ 57-58)

ነበዛዝት ሆይ! ለካዛንችስ ዘምሩ
አንቺ መሸሸጊያዬ ወይ! ወደአንቺ አመራሁ
ቁንዳላሽ የተገረፈረፈ ነው።

ጉንጮችሽ የሽቱ መዳብ ናቸው።
ያሻኝን ከጓዳሽ አገኝ ዘንድ
አንቺ የገነት ምንጭ፣ የኤደን ተምላሌት
የሕይወት ውሃ ጉድጓድ
አቤቱ በፈቃዴ ለሕይወቴ ርካታን እሻ ዘንድ
ወዳንቺ ሰገድኩ።
ውዴ! እንደሲባኖስ የባህርዳር አበቦች
ቀለማትሽና መዓዛሽ የበዙ
የመዘቃሽ ቃና እንደኪሩቤል ዋሽንት
እንደገነት ማር የምትጣፍጭ
በኮረብቶች ላይ እንዳሉ ምንጮች ነሽ
ከአበቦችሽ ልቀስም
በወለላ ሀሴትን ላገኝ
ከምንጮችስ ተጎንጭቼ ልረካ
እነሆ መጣሁልሽ ...

ከላይ እንደተናገርኩት ካዛንችስን የፈቀደበት ለሕይወቱ ርካታን ለማግኘት ነው። የካዛንችሱ ታዳሚ የዝማሬው የውዳሴ ቃላት መረጣ ሁኔታ ለመሰሎቹ አስቂኝና ማራኪ ሊመስል ለሌሎች ደግሞ ድፍረትና ስድነት የተመላበት ሊመስል የሚችል ነው። ምክንያቱም የውዳሴው የአዘማመር ሂደት/ስልት የተኮረጀው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኘውና በብልህነቱና በጥበበኛነቱ ከሚታወቀው ከእስራኤላውዩ የሰለሞን ዝማሬዎች "መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን" ከሚለው መጽሐፍ ነው። ትርጓሜውም፡-

> "መኃልየ መኃልይ" የተባለው መጽሐፍ የፍቅር ቅኔዎች ቅንብር ነው፤ ከነዚህም ቅኔዎች አብዛኛዎቹ የተፃፉት በመዝሙር መልክ ሲሆን ወንዱ ለሴቲቱ ሴቲቱም ለወንድየው ያቀረቡአቸው ናቸው። መጽሐፉ በአንዳንድ ትርጉሞች "መኃልየ መኃልይ" ወይም "ከመዝሙሮች የሚበልጥ መዝሙር" በመባል ይታወቃል፤ በሌሎች ትርጉሞች ደግሞ "የሰሎሞን መዝሙር" በመባል ይታወቃል፤ ምክንያቱም በዕብራይስጡ ቅጂ የሰሎሞን መሆኑ ስለተገለጠ ነው። ይህ መዝሙር በክርስቶስና በቤተክርስቲያን መካከል

AU LIBRARY

ያለውን ግንኙነት የሚያመላክቱ ምሳሌዎችን የያዘ ነው፤ አይሁዳውያን ግን "በእግዚአብሔርና በእስራኤል ሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያመላክቱ ምሳሌዎችን የያዘ ነው" ይላሉ።

(መጽሐፍ ቅዱስ፤ 1980፤ ገፅ፤ 680)

ከዚህ የ "ማነልየ መነልይ" የትርጉም ምንነት በመነሳት በርካታ ሐሳቦችን ማርቀቅ ይቻላል። ሐሳቦቹም የሚያጠነጥኑት ደራሲው የድርሰቱን ርዕስ ይህን ስያሜ እንዲያገ ለምን ፈለገ? የሚለውን ጥያቄ በማንሳት መላምታዊ መልሳችንን በፍካሬ በማምጣት የምንሰነዝረው አስተያየት ላይ የሚያተኩር ይሆናል። ከላይ የተገለጸው ትርጉም ሁለት አቢይ ሐሳቦችን የያዘ ነው የሚል አመለካከት አለኝ። ይኼውም የ "የመነልየ መነልይ" ትርጉም ሥጋዊ እና መንፈሳዊ ሆኖ የቀረበ ነው። ይህን ለማለት ያስቻለኝ አንደኛ መነልየ መነልይ የፍቅር ቅኔዎች ቅንብር ነው። ቅኔዎቹም "... ወንዱ ለሴቲቱ ሴቲቱም ለወንድየው ያቀረቡዋቸው ናቸው" የሚለው አባባል ሥጋዊ ትርጓሜ የያዘ ነው። ቅኔው ሁለት በፍቅር ለወደቁ ወንድና ሴት የፍቅራቸውን ልክና መጠን በቅኔ አንቅተው በዜማ አጅበው መግለፃቸውን የሚያሳይ መሆኑን በማያሻማ መልኩ ያሳያል። ይህም ሥጋዊ ሕይወትን አለማዊ ኑሮን የሚገልፅ ነው።

ሁለተኛው መንፈሳዊ ሕይወትን የሚያሳይ የሚወክል ሆኖ የቀረበ ትርጉም ነው። "ይህ መዝሙር በክርስቶስና በቤተክርስቲያን መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያመለክቱ ምሳሌዎችን የያዘ ነው።" ይህንን ሀሳብ ይዘን ስንመረምረው "መነልየ መነልይ" መንፈሳዊ ሕይወትን የሚገልጽ ነፍስን ለጽድቅ ለማብቃት ለእግዚአብሔር የሚደረግ መንፈሳዊ መዝሙር ነው የሚል አቋም እንድንይዝ ያደርገናል። ለዚህ ነው ሁለት የተቃረኑ ነገር ግን የማይቃረኑ የሚመስሉ የትርጉም ሀሳቦችን የያዘ ነው የሚል አስተያየት ያለኝ። የተቃረኑ ያልሁበት ሥጋዊ ሕይወትና መንፈሳዊ ሕይወት ከሃይማኖታዊ አተያይ አኳያ ስናየው ፍጹም የማይገናኙ ናቸው። የሥጋሕይወት ምድራዊ ሲሆን መንፈሳዊ ሕይወት ግን ሰማያዊ ነው። ይህንን አመለካከት ይገፍ የትርጉሙን ሐሳብ ስመረምረው ደራሲው ለድርሰቱ የመረጠው ርዕስ በራሱ ጥያቄ የሚያስነሳ ብቻም ሳይሆን ከሁለት የተከፈለ አመለካከትም እንዲኖር የሚያደርግ ነው ባይ ነኝ። ይህን ለማለት የሚያስችለኝ ለመጽሐፉ የተሰጠው ርዕስ መንፈሳዊ ይዘት ያለው ሲሆን የጠቅላላው የድርሰቱ ድባብ ግን ኢ-ምግባራዊ ነው። ስለዚህ የካባንችሶቹ ምድራዊ ሕይወት ፈላጊዎች በገጠሬው ውበት፤ በይዘቱ ረቂቅነትና

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

በአቀራረብ ብሂሉ ሊደሰቱ ይችሉ ይሆናል። በአንፃሩ ግን የሃይማኖቱ ተከታዮችና አጥባቂዎች ደግሞ የ "መዝሙሮች ሁሉ መዝሙር" የተከበረውን ሰሎሞናዊ ቅኔ ለተወገዘ ድርጊት ውዳሴ በመጠቀሙ በድፍረቱ ሊያወግዙትም ሊነቅፉትም ይችላሉ። ነገርግን በውዳሴው የተደሰቱ ወይም የተበሳጩ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መኖር ወይም ያለመኖር ጉዳይ አይደለም ቁምነገሩ። አንድምታው የሚያመራውና የሚያነጣጥረው በግለሰቦች ወይም በቡድኖች ላይ ተወስኖ የሚቀር አለመሆኑ ነው። ዝማሬ መኃልየ መኃልይ ዘካዛንችስ የአንድ ትልቅ ማህበረሰባዊ ባህላዊ ተቋምን የሚወክል፣ በአመሳሰሉም ረገድ ስንመለከተው በመኃልየ መኃልይነቱ ዝማሬ ትእምርት ሆነው የሚቆሙ እንዳሉ ነው። በዚህ ረገድ ስናየው የነገሩን ክባድነት የሁኔታውን አሳዛኝነት እንረዳለን። በመሆኑም ማህበረሰቡ በልማዳዊ አመለካከቱ ብቸኛ ባይታወር ገለልተኛና "ጋጠወጥ" እንድትሆን ላደረጋት ሴተኛ አዳሪም ሆነ የማህበረሰብ ልማዳዊ አመለካከት ተጭኖት የውስጥ ፍላጐቱ የታመቀ፣ ስሜቱ የተደበቀ፣ አመለካከቱንና አስተያየቱን በድፍረት ይፋ ለማውጣት የተቀየደ የማህበረሰቡ አባል ተቃውሞውን የሚያሰማበት ድፍረቱን የሚገልጽበት እና ነፍሱን በሀሴት የሚያረካበት ሥፍራ ካዛንችስ ነው። የሁለቱም ተገፊዎች የካዛንችስ የምሽት ውሎና አዳር ደግሞ ብሶት እንዳገናኛቸው ዓይነት የተጠቂ ትብብር ሳይሆን የእልህ መወጣጫ በቀላዊ ግንኙነት ነው የሚታየው። ይህን ነው በአንድምታ በማጉላት ድርሰቱን እንዴት ማንበብ እንዳለብን ለማሳየት የሚጣረው።

በዝማሬ መኃልየ መኃልይ እንደተገለጸው "አቤቱ በፈቃዴ ለሕይወቱ ርካታን እሻ ዘንድ ወደአንቺ ሰገድኩ" የሚለውን አገላለጽ ወስደን ብንመረምር ዘማሪው ከዛንችስን የሚፈልግበት አበይ ቁምነገር ምን እንደሆነ እንረዳለን። የመጣው በፈቃዱ ነው። "በፈቃዴ" የሚለው ሌላ ተጨማሪ አንድምታ ትርጉም እንዳለው አመላካች ነው። ይኼውም "ፈቃጅ" ያለመሆኑን ያመላክታል። ስለዚህ ካዛንችስ ገብቶ የተመሰገው ሳያስፈቅድ ተደብቆ ነው። ፈቃድ ሰጪው ማነው? ለዚህ ጥያቄ መልሱ ግልጽ ነው። ካዛንችስ ቡና ቤቶች እንዳይሄድ የሚፈልገው የሚኖርበት ማህበረሰብ ነው። ለምን ቢሉ? ካዛንችስ ሲመሽ ሕይወት የምትዘራ የቀን መት የለሌት ሕይወት የሆነች በአዲስ አበባ ሕይወት ዙሪያ የታጠረች ደሴት ናት። በተቃራኒ የቆመች። (ከላይ ለመጥቀስ እንደተከሞረው የመኃልየ መኃልይ ትርጉምስ ተቃራኒ ሀሳቦችን የያዘ አይደል?) ለዚህ ነው "በፈቃዴ ለሕይወቱ ርካታን እሻ ዘንድ ወደ አንቺ ሰገድኩ።" በማለት የገለጸው። ነፍሱን ያረካ ዘንድ የሚሄድባት ካዛንችስ ውስጥ የሚያገኘው "የባህርዳር አበቦች"ን ነው። "የባህር ዳር አበቦች" ያላቸው ሴተኛ አዳሪዎቹን ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

በሴተኛአዳሪዎች ውበት ተደስቶ የነፍስ ሀሴት ለማግኘት ባህሉን ጥሶ በፈቃዱ ለካዛንችስ ሰገደ። ቁምነገሩ አበቦቹን መፈለጉ ስሜቱን ለማርካት ባህሉን መጣሱና ለካዛንችስ እንቡጥች መስገዱ አይደለም። ባህሉ የነፈገውን ግልጽነትና ተጫኝነት ተቃውሞ በሴት "ሽሌዎች" ላይ የሚፈጽመው ኢ-ስነምግባራዊ ሁነትና ሁኔታ ነው። ውዳሴውም ለግሉ "ነፍሴን ላረካ" አለ እንጂ ለነፍሴ የምትሆን አላለም። የፈለገው ግላዊ ርካታን እንጂ የሴቷን ስሜት አልጨመረም። ለምን ሴቷ ሽሌ የምትታየው እንደሸቀጥ ዕቃ ነው። ወንዱ በገንዘቡ ገዝቶ እንዳሻው የሚገለገልባት። በዚህ መልክ የሚጀመረው ውዳሴ ከንቱ መሆኑን ምሽቱ እየጨመረ ውድቅት ሲሆን የወንድ ተሸራሚጩ ውስጣዊ ማንነቱ እየተገለጠ ይመጣል። እሱ ራሱ እየተሸራሞጠ ሴቷን ሸርሙጣ በንቀትና በማንጓጠጥ እየተመለከተ ወሲባዊ ፍላጐቱን ሊያበርድባት ከባህሉ የወረሰውን የወንድ የበላይነቱን መጠቀም ይጀምራል።ይህንን የሚያጠናክርልን ማስረጃ እንምዘዝ

> በግ ልትገዛ ሄደህ ታውቃለህ? ሲገዙስ አይተሀል ...? ፍርንባ-ወገብ-አንገት-ጥርስ-ሽሆና ... አገላብጠህ እንደምታየው ... እዚህም አብዛኛው ተሸራሚጭ በየራሱ ስልት ይፈትሻል-ያያል። እንደብጤቱ ነፍሱ እንደፈለገችውም አይነት ይገዛል ... እንደበግ ሲደባብሳት የነበረችውን ካልፈለጋት ትሰናበታለች ወይ ሰበብ ይፈለግላታል። ወይም በስድብ ከከፋም በጥፊ ትባረራለች።
>
> (ገፅ፣ 113-114)

ካዛንችስ የመጣ ወንድ ማይም ከምሁር ልዩነት ላይኖረው "በሴት ሽሌዎች" ላይ ያለው አመለካከት አንድ ነው። ማክበር ተብሎ ነገር አይታሰብም። ወንዶቹ የካዛንችስ ሴት ሽሌዎች ለነሱ መቀለጃና መሳለቂያ ናቸው። የሁሉም ወንዶች ለሴት ሽሌዎች ያለውን የንቀት አመለካከት የምትረዳው በስካር ስዓት ነው። ሁሉም ወንዶች ሲሰክሩ የሚያስቡት በአምሮኣቸው ሳይሆን "በብልታቸው" መሆኑን ትገነዘባለህ። ወሲባዊ ፍትወቱን ሊያበርድባት የፈለጋትን "ሴት ሽሌ" ጠርቶ ወይም አስጠርቶ የምትሆነው ወይም የማትሆነው መሆኗን የሚወሰነው እንደበግ ገዥ ቂጧን ደባብሶ ወገቧን ጨምቆ ጡትዋን አሻሽቶ ነው። ለውሳኔው በእጁም በዐይኑም የነካካውንና የማተረውን ልቡ ከፈቀደለት ዋጋ ይደራደራል። ካልሆነ ግን ልዝቡ በሰበብ ሲሸኛት አብዛኛው በስድብ ወይም በጥፊ አልሶ ያባርራታል። ሁለቱም ተሸራሚጮች (ወንዱና ሴቷ) ሆነው ላለ "ወንዱ ሽሌ"፣ "ሴቷን ሽሌ" አዋርዶ ሰድቦና መቶ የማባረሩ ምስጢር የሚገልጸው የማን አለብኝ ባይነቱን ብቻ ሳይሆን ማህበረሰባዊ ልማዱ

ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

የነፈገውን ይፋዊ "የወንድ ሽሌነት" "ሴታ ሽለ" በብቸኝነት የወሰደችበት መስሎ ስለሚታየው የተፈጠረ ድብቅ ቅናት ነው ለማለት የሚያስችል ይመስላል።

"የሴታ ሽሌ" ጣጣ እንደ እቃ ወይም እንደ እንስሳ ተቆጥራ ለግዥ መቅረቧ ወይም "የቀንሽ" "ጨምር" ድርድሩ ብቻ ሳይሆን ሌላም ሰብአናዋን የሚጐዳ ሞራሏን የሚሰብር ሁኔታም ይገጥማታል።

> ... በቡድን ሆነው የሚጠጡቱ አንዷን ሴት መሀላቸው አስገብተው ... ሲያፈዙባት-ሲደበሩባት ሲሳለቁባት ታያለህ ... እሷም "ዙ" ውስጥ እንደገባች ጠጣ መውጫ አጥታ ስትሰቃይ ... አንዱን ብትናገር በጭካኔ እንደምትመታ ታውቃለች ... ቢበዛ ጓዳ ሄዳ ታለቅሳለች። (ገፅ፣ 115) (ሰረዝ የኔ)።

"ወንዱ ሽሌ" ካዛንችስ የሚመጣው የማህበረሰቡ ደንብ የቀየደውን የታመቀ ውስጣዊ ባህርይውን ቀስ እያለ በምሽት አነቃቅቶ የታመቀ ስሜቱን የሚያበርደው የተቀየደ አመሉን "ነፃ" የሚያወጣው መውጫ ባጣችው ሽሌ ላይ ይሆናል። "ዙ" ውስጥ የገባች ጠጣ ከሌሎች እንስሳት ጋር ስትቀላቀል ባይታወርነት ይሰማታል። በሌሎችም እንስሳት የመጠቃት እድሏም የበዛ ነው። የሴታም ሽሌ እጣ ፈንታ ይኼው ነው። ወንዱ ሽሌ በስካር ኃይል ይፋ ያገጠጠ ድብቅ አመሉን በመምዘዝ ሲፈልግ የስድብ ናዳ ሲያሻውም በጡንቻው የወገሸ አመሉን ይከላባታል። ለሱ ሴታ ሽሌ በገንዘብ የምትገዛ የሸቀጥ እቃ አልያም የእርድ ሽህር ናት። መዝናኛና መቀለጃ አሻንጉሊት አልያም የ "ዙ" እንስሳ ናት። ሰው መሆኗን ይረሳል። ከሴት የተገኘ መሆኑንም ይዘነጋል። ይህ አመለካከት ደግሞ ተማረ ወይም አልተማረ የሚሉ ልዩነት የለውም። ያልተማረው በልማዳዊ ምሳሌያዊ አነጋገር ተማርኩ ባዩ ደግሞ ልማዳዊ አባባሎቹን ከዘመናዊ ብሂል ጋር እያቀናጀ የሴተኛአዳሪዋን ቅስም መስበር ብቻ ነው። የሴትን ልጅ የሰብአዊነት ክብር የማያውቅ ለሴት ያለው ግምት ተራ ራስ ወዳድነትን የሚያንፀባርቅ ያለው ብቻ ነው የካዛንችሱ ወንድ ተሸራሚጭ። ተማርኩ ባዩ ካዛንችስ መጎልየ መጎልይ ሲዘምር ማሳረጊያው "ለውሃ ማጫወቻ ድንጋይ እንደተፈጠረ ለወንድ ማጫወቻ ሴት ተፈጠረች (ገፅ፣ 116)" የሚል ነው። ሴት በተለይም ሴተኛአዳሪ (ሽሌ) ግአዝ ነገር ናት። ምንም ምኑም አይደለችም። ለአልጋ ብቻ የተፈጠረች መሆኗን ይደሰኩራል። "ክሕገ ልቡና ጀምሮ ... እስከ 21ኛው ክፍለዘመን ያለውን በፊደላዊ አውቀቱ ይተርክልሃል ... ታየዋለህ ሽሌዋን ሲያራክስ (ገፅ፣ 116)"

ይህንን የወንድ ሸሌውን ሁኔታ ከማህበረሰባዊ ልማዳዊ እሴቶች ጋር አነፃፅረን ስንመለከተው ሴተኛ አዳሪዋ እየደረሰባት ያለው ኢ-ሰብኣዊነት ሁለት ስለት ያለው ነው። ማህበረሰቡ ስመ ብዙ አድርጐ የስም ቅጭት ሰጥቶ በሰዎች መሀል እያለች የተገለለች፣ የተነወረች፣ ባይታወር ሲያደርጋት ይህንን እንኳ ችላ የራሷን አለም ከመሰሎቿ ጋር መፍጠሯ ማህበረሰቡ እንደናቃት ንቃው እንዳነወራት አነውራው፣ የባህሉን እሴቶች አፋልሳ፣ ደንቡን ጥሳ ሀራም የተባለውን ተግብራና ተናግራ ብሶቷን ልትወጣ ብትሻ በአካሏ እየረካ ስሜቷን የሚሰብር፣ ሰብእናዋን የሚያጐድፍ ጠላት ተፈጠረባት። ሊገላገሉት የማይቻል፣ ሊርቁት የማይሞክር በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ "መ.ያዬ" ላለችው "ሥራ" "ሽሪክም" "ተጋሪም" የሆነ "የወንድ ሸሌ" በገላዋ ረክቶና ተደስቶ በመሄድ ፊንታ አበሻቅጦና ደብድቧት ይሄዳል። ስትሰደብ "ተው ባይ"፣ ስትደበደብ ገላጋይና ምን አደረገችህ ባይ የለም። ካለም አለቀሰት ይፈረካከሳል፣ ሁሉም ይፈርድብሃል ... ለሸሌ ብሎ ... ለሴት ብሎ" "በለው! በለው! ... በለው! በለው" የአያቶች ጦርነት ካዛንችስ ይደገማል። ሌላው ቀርቶ በቅድሚያ የሚንቅህ እና የሚያሸካክብህ ጓደኛህ ነው ... ሺህ ጊዜ አንተ ብታጠፋ ... የሚፈረድባት እሷ ናት" (ገፅ፣ 116)። ይህች ሴት የሚደርስባት የኢ-ሰብኣዊነት ሁኔታ እጥፍ ነው። ይህን ነው በ መነልየ መነልይ ዘካዛንችስ የምናነበው። ይህንን የሴተኛ አዳሪን የሰብኣዊነት ንጥፊት (Dehumanization) ከድርሰቱ ውስጥ በሚገኙ ጠቋሚ ሐረጋት አማካይነት መዘን መፈክሪያ የምናደርገው። በግልፅ የተቀመጠው ተራና ስድ የሚመስሉ ቃላት የሰብኣዊነቱን ንጥፊት ልክ እና መጠን አጉልተው የሚያሳዩ ናቸው እንጂ ድርሳነ ወሲቡን በስካርና በተሸራሚፎች አጅቦ "ስድ" የሚባሉ ያልታረሙና ያልለዘቡ ቃላትን፣ የአነጋገር ዘዬዎችን ለማሳየት አይደለም። ይልቁንስ የሴቷን ሸሌ መሆን "ሽርመጣ" እያለ ራሱን ካዛንችስ ውስጥ የመሰገውን ለካዛንችስ የሰገደውን "ወንዴ ሸሌነት" ጉዳይ እንድናጤን የአነባበብ ስልታችንን የፍካሬ ብሂላችንን እንድናስተካክል ያስገድደናል።

በትረካው መንደርደሪያ ዓረፍተነገር የሚያቀርባቸው "አዲስ አበባ" እና "ካዛንችስ" ተምሳሌታዊነታቸው እንዲሁ በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም። የሚወክሉት ትእምርት አለ። ትእምርትነታቸው ደግሞ ብዙ የሚያስፈክሩ ናቸው። ማህበረሰባዊ እሴቱን ከልዩ ልዩ ፈረጀ ብዙ ሕይወት አኳያ ብዙ ልናዘምርበት የሚያስችሉን በተራና ግልብ መሰል ቃላት፣ ሐረጋትና ዐረፍተነገር ውስጥና መሀል ተሰገው የምናገኛቸው የአገላለፅ ስልቶች የሁለቱን የቦታዎች ተምሳሌት ሰፋ አድርገን እንድንተረጉም ያመላክቱናል። የመጽሐፉ ርዕስ ራሱ በዘፈቀደ የተሰጠ አይደለም። ካዛንችስን በታወቀው የሰሎሞን መዋድስ ዝማሬ ስም

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

በተገላጭነት ማስያዙ የአፈካከራችን ስልትና ሂደት ከምን አንፃር ሊተኮርበት እንደሚችል ጠቋሚ ነው። አዲስ አበባ አንድን ከተማና ህዝብ ብቻ የሚወክል አይደለም። በውስጧ የሚኖሩት ህዝቦች ከተለያዩ የአገሪቱ አቅጣጫዎች ከነቋንቋቸው ከነባህላቸው ከነዋግ ሥርዓታቸው መጥተው የሠፈሩባት ናት። ስለዚህ የአዲስ አበባ ትእምህርታዊ ውክልና ሰፊ በባህር የሚመስል ሲሆን የአዲስ አበባ አንድ አካል የሆነችው ካዛንችስ ደግሞ የትልቁ ባህር "ደሴት" ሆና ትእምርታዊ ውክልና ሊሰጣት ይቻላል። የፍካሪያችንም መጠን የሚወሰነው የአቅጣጫው ወሰን የሚለካው በዚሁ ዙሪያ ይሆናል።

ተራኪው የአዲስ አበባን ሕይወት በእንቅልፍ የካዛንችስን ደግሞ በእንቅስቃሴ ያለ ህይወት አድርጎ ነው የሚያቀርበው። ሁለቱም ግን የጊዜ ቀመር ሂደታቸው ተመሳሳይ ሆኖ ሳለ ሕይወታዊ እንቅስቃሴው መለያየቱ እንደምን ነው? የሚለውን የባህሩን የሕይወት ኑሮ (አዲስ አበባ) ከደሴቷ ነዋሪዎች (ካዛንችስ) ጋር በማነፃፀር ስንፈክር የአንድ የቀን ክፍለጊዜ ክስተት ሰዋዊ እንቅስቃሴ ሲያቆም በዚያው የቀን ክስተት ሌላው ሕይወት ነፍስ የሚዘራበት ሁነት ከመጽሐፉ በተገኙ አስረጅ አመላካች ጠቋሚነት በምንሰጠው አፈካከር እውነታውን ከማህበረሰቡ የሕይወት እንቅስቃሴ ጋር የምናገናኝበት ይሆናል።

ድርሰቱ የሴተኛአዳሪዎችን ስቃይ፣ መከራና ችግር ከወሲብ ጋር አቆራኝቶ የሚያቀርብ ቢሆንም ጨመቁ ግን ይህ አለመሆኑን ጠቁሚያለሁ። ምክንያቱም ይህ ማንም አንብቦ የሚረዳው ጉዳይ ነው። ተራኪው ይህንን የታወቀ እውነት መልሶ በመንገር ሊያደነቁረን እንደማይችል ግልፅ ነው። በስድና በሀራም (taboo) ቃላትና አባባሎችም መግለጹ ደራሲው ተራ ያልታረመና ህገ-ወጥ፣ ባህል ደፍጣጭ ተብሎ እንዲወቀስ አስቦም አይደለም። ዋናው የድርሰቱ ቁምነገር ደጋግሜ እንደገለፅኩት ከነዚህ ግልብ ከባህል በወጡና ባፈነገጡ አባባሎችና ቃሎች አማካይነት በስተጀርባ የሚተላለፈውን አንድምታዊ ሃሳብና የአመለካከት ሁነቶች ከሁኔታውና ከዘመኑ ጋር አቆራኝቶ ከማሳየቱ ላይ ነው።

3.3.3.2 አሁድ ሁለት (ምዕራፍ አንድ፣ "...ድርሳነ ካዛንችስ) ...መልክዓ ወሲብ...!" ወይስ ያመንዝራ ጎራ?)

አሉ ወይ እንደዚህ ባስከሬን አገር፣
ሳይወዱ ተፈጥረው ሚኖሩ በጣር
ነው ወይ ለመሆን የመቃብር አገር ያመንዝራ ጎራ፣
ለሕዝቡ ነቀርሳ ለሴቱ መከራ፣

ፈጥኖ ይስፋፋል ወይ እንዲህ ያለው ሥራ፤
ወይንስ ህግ አለ ይሽን የሚከላ በረድፍ በተራ፤
ለወንዱም ለሴቱም በወግ የሚያስመካ፤
ይሽን ለማስቀረት ምንድር ነው ሚተካ።

(ዮሐንስ አድማሱ፤ እስኪተጠየቁ ገጽ፤ 46)

ሴቶቹ ማህበረሰቡ በውስጠ ወይራ "የቡና ቤት ሴት" የሚላቸው ካዛንችስና መሰሎቹ ግን "ሽሌ"፤ "ሴተኛ አዳሪ"፤ ሸርመጣ"፤ የሚላቸው ደንበኞቻቸው እስኪመጡ በየወንበሮቻቸው ተቀምጠው የየማታው አዳራቸውን "ገድለ ሽርመጥና" አንዷ ለሌላው ይተርካሉ። ትረካው እንደ ተራኪዋ "ሽሌ" ምግባር የትረካው አቀራረብ አስከፊም አስቂም ወይም አሳዛኝ ሊሆን ይችላል። የአጠቃላይ የትረካው ድባብ (mood) ግን መልክዓ ወሲብ ነው። "የወንዱን ሽሌ" ወሲባዊ ባህርይ "ሴት ሾሌዎቹ" ትዕይንታዊ ሁነት የምሬት ምፀት ባዘለ የአገላለጽ ስልት እርስ በርሳቸው ያወራሉ። ገለፃቸው ሀፍረት የሌለበት ቋንቋቸው የባህል ገደብ የጣሰ ነው። የወሲባዊ ቃላዊ መገለጫዎችን ምንም ሳይሸፋፍኑ የበለጠ ለማጉላትም ድርጊታዊ ክንዋኒውን በቃልም በተግባርም ይገልጹታል። "ወንዱ ሽሌ" ስክሮ የታመቀ አመሉን በነሱ ላይ እንዴት እንደገለጸባቸው በምሬት ሳያፍሩና ሳይደብቁ ይናገራሉ። "መጥኔ ላንቺ" "በትውክት አፍ ሳመሽ" አድማጯ ናት፤ "አ-ህ ተገመጠመጠ። ተፋ። (ገፅ፤ 4) ተራኪዋ። የሚሉት ዓይነት ጠቋሚ ሀሳቦች "የሽሌዎቹን" የስቃይ ሁኔታ የሚያሳዩ ናቸው። ስክሮ የሚታገላት "ወንድ ሽሌ" አ - ህ ተገመጠመጠ" ብላ የምትሰጠው መልስ የሴተኛ አዳሪዋ ስነልቡና ምን ያህል እንደተሰበረ የሚጠቁመው ሁነት አለ። "ለህዝቡ ነቀርሳ፤ ለሴጂ መክራ" እንዳለው ዮሐንስ አይነት ነው።

ድርሳነ ካዛንችስ ዓይነቱና ባህሪው ብዙ ነው። መልክዓ ወሲቡ ለአንባቢው ግራና እንግዳ ነው። ለሰሚው የሚከብድ ኢ-ባህላዊ። ግን እየሆነ ያለ አዲስ ያመንዝራ ጎራ። ይህ አዲስ ኢ-ባህላዊ የሆነ ገድለ ወሲብ የሚያመለክተን ሁነት ቢኖር የማህበረሰቡን ማንነት፥ ጥያቄ ውስጥ የጠላ ማህበረሰባዊ ህመም እየተስፋፋ መሆኑን ነው። ይህንን ማህበረሰባዊ ህመም "በሴት ሽሌዎች" አንደበት የየእለት የወንዱን ሽሌዎች "ድርሳን ወሲብ ይተረካል። "ወንዱ ሽሌ" በምድረ ካዛንችስ በምሽት ጀምሮ በሌሊት የሚያከናውነው ከምግባር የራቀ፥ ክባህል ያፈነገጠ ድርጊት ሴቶች ያወራሉ። የሚያወሩት ወንዱ፥ በነሱ ላይ የፈፀመውን እንስሳዊ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ብቻ ሳይሆን ሌላም ያልተለመደ የእርስ በርስ ተራክቦ መፈጸሙንም ጭምር ነው። ይህ ኢ-ስነምግባራዊ የወንዶች ማህበራዊ ተራክቦ (social

AAU LIBRARY

interaction) ይህ የባህልን ገደብ የጣሰ አስነዋሪ አሳፋሪና አሰቃቂ፥ የወንዶች ኢ-ስነምግባራዊ ክዛንችሳዊ ወሲባዊ ህመም ክምን የመጣ፥ የወገንና የሀገርን ስም የሚያጎድፍ ተግባር እንደሆነ የሚያጠይቅ ሁነት ነው። በድርሰቱ ውስጥ የምንገነዘበው ይህንን ሁኔታ ነው።

"ገድለ ወሲብ ... ገድለ ሽርሙጥና ... ድርሳነ ክዛንችስ... መልክዓ ወሲብ ... ተዓምረ ወሲብ ... ገድለ ፍትወት ... ድርሳነ ቅንዝር ... ታደምጣለህ። አንተም በአባልነት ከተመዘገብክ ታሪክህ "... ይኸውልሽ አንዱ ..." ተብሎ ይዘከርልሃል። (ገፅ፣ 24-25)" ይህ የዓረፍተ ነገር አሀድ የተወሰደው (ጀምበር ስታዘቀዝቅ የሚል ርዕስ ከተሰጠው ክምዕራፍ አንድ ከገጽ 24-25) ውስጥ የተወሰደ ነው። የዚህ አመለካከት ምንጨ በገጽ፣ 10 የተገለጸው አባባል ነው። "እያንዳንዳቸው ገጠመኛቸውን ያወራሉ። ካልቀረብካቸው ጥሩ ወሬ ደባቂዎች ናቸው። ከቀረብካቸው የክዛንችስ ገድል ትሰማለህ። አምሮ ተኳኩሎ ተቀንድቦ፣ ፍሪዝ ተሰርቶ ጀል ፐርም ተቀብቶ፣ ጆሮህ ይደርሳል" የሚለው ነው። ይህ ሁኔታ በሁለት ነገሮች የታጀበ ነው። አንደኛው በተራኪው አማካይነት የሚነገረን ከዚህ በላይ የጠቀስኩትን የሸሌዎቹን "ትዝብት" ተከትሎ የሚመጣው የወንድ ሸሌዎች ወይም ተሸራሚጭ ገድለ ወሲብ አፈጻፀም በሴት ሸሌዎች ላይ የሚተገበርበት ሁኔታ በሴቶቹ ቢወራም ቀስ በቀስ በውስጣቸው ቅሬታን፣ ያሳደረባቸው እና የህሊና ሰቀቀን የስነቀረባቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው። ዋናው ቁምነገር የታወቀውና እኔም ፍካሬዬን የምዘርፍበት "የሸሌዎቹ የድርሳንና የገድል ምንጨ ወንዱ ተሸራሚጭ ነው" የሚለው ነው። ሌላው ሁለተኛው አጀበ. የወንዱ ተሸራሚጭ ገድል አይፃፍም እንጂ በየቀኑ ቢያንስ አንድ "ፍቅር አስክ መቃብር" ይወጣዋል። የአልቤርጎ የትላንት ማታው ገድል በሸሌዎች መካከል ይወራል። ነገ ሌላ ቀን ነውና ይረሳል። "... የወሲብ ርካታው ሁሉ ይረሳል ... አንዳንዴ የአንዳንድ ተሸራሚጭ ገድል ከልምድህና ከአካባቢህ የወጣ ይሆናል። ... በተለያየ መንገድ ስለሚረካው ጀግኔ ትሰማለህ" (ገጽ፣ 10) የሚለው ሁኔታ ነው።

ጠቅላላ ድባቡን (mood) እና ድምፀቱን ስንመለከት ሴት ሸሌዎቹ በወንዱ ተሸራሚጭ ገድለ ወሲብ ወሬ ውስጥ ውስጡን አብላልተው የወንዱን ተፈጥሮ ከእንስሳ የማይሻል የቀን "ድመት" የሌሊት "አነር" ፀባዩን በነሱ (በሴት ሸሌዎች) ላይ የሚገልጽበትን ሁነት የታዘበበትን አገላለፅ ነው። ሴቷ ሸሌ "ነፃነት" የሌላት በነፃ ስም "ዘመናዊ ባሪያ" መሆኗን ለመገንዘብ አይገድም። ወንዱ ተሸራሚጭ ከባህልና ከልምድ የወጣ ወሲባዊ ፍላጐቱን በሌሊት የሚወጣው በሴቷ፣ ባህሉ የነፈገውን፣ ሀይማኖቱ ያቀበውን ውስጣዊ ስሜቱን ለማብረድ ክዛንችስ ሲመጣ የባህል በቀሉን፣ የሃይማኖት እልሁን የሚወጣው

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

በሴታ "ሽሌ" መሆኑ የሴቶቹን ስነልቡና ምን ያህል ያደቀቀ እንደሆነ እናጤናለን። በዚህም የሴተኛ አዳሪዎች ሰብአዊነት ከሰው ተራ "ወረዶ" ኢ-ሰብአዊነቱ የገዘፈ፣ ውርደት ንቀቱ የከፋ፣ እና መገለሉና ባይተዋርነቱ ወደር የሌለው መሆኑን በዚህ አሀድ ውስጥ ለማየት ይቻላል። የሴተኛ አዳሪዎቹ የሰብአዊነት መንጠፍ ልክና መጠን ምን ያህል እንደሆነ ለመገንዘብ የመጽሐፉን ጠቅላላ ይዘት በግርድፉ በተገለጹት ቃላት፣ ሀረጋትና ዓረፍተ ነገሮች በሰበካው ስናነባቸው እና ስንገነዘባቸው አይደለም። እያንዳንዷን ቃል፣ ሀረግና ዐረፍተነገር "በፈርሱ" ገልብጠን በአንደምታ ትርጉም በፍካሬ እየዘረፍን ሀሳቡን ከባህሉና ከዘመኑ ጋር አቆራኝተን ስንመለከተው ብቻ ነው። ይህ ሲሆን ምን ያህል ማህበረሰሳዊ "ህመም" በእያንዳንዳችን ውስጥ ገብቶ ውስጣችን "ቁንቁን" እንደበላው ዛፍ የነቀዘን መሆኑን የምንረዳው። ነሊናችን መንተቡን፣ ባህላችን ፈርመልቀቁን፣ እና አስተሳሰባችን መሰለቡን በዚህ አሀድ ከገጽ 10 እስከ 29 ድረስ በገሀድ ተቀምጧል። ይህንን ለመገንዘብ የአነባበብ ብሂላችንን ትርጓሚያዊ ይዘት ከሰጠነው ብቻ ነው ሊገባን የሚችለው፤ ይህ ካልሆነማ እንደ የዋሁዎቹ አንባቢዎች ይህ "ድርሳነ ብልግና" ነው ብለን ድርሰቱን ማጣጣላችን አይቀሬ ነው። ይህም የብዙ አንባቢዎች ግልብ አስተያየት ስለሆነ የመጽሐፉን መልዕክት የሚረዱት በሌጣው ነው።

ድርሰቱ ግን የሚያስተላልፈው መልዕክት ይህ እንዳልሆነ ቀደም ብየ ገልጫለሁ። የእነ Rene wellek ን አስተሳሰብንም አንስቼ አንድ ስነጽሑፍ የሚዛፈው ያለበትን ማህበረሰብ ማህበራዊ ገፅታዎች ከልዩ ልዩ ሁነቶችና ሁኔታዎች ጋር አቆራኝቶ የማህበረሰቡን ባህርይ፣ ድርጊት፣ ምናብና ስነልቡናዊ አመለካከቱን ምን እንደሚመስል ለማሳየት እንደሆነ ጠቁሚያለሁ። ስለሆነም በዚህ አሀድ የተገለጹት ድርሳነ ካዛንችስ ... መልክዓ ወሲብ ... በትክክል የማህበረሰቡ አካል የሆነው "አፈንጋጭም" ይባል "አማፂ" ማህበረሰቡ "ውጉዝ ከማርዮስ" ብሎ በባህልም ሆነ በሃይማኖት የተከለከለውን ወሲባዊ ድርጊት በካዛንችስ ይፈፀማል። ይህም ባህልን የጣሰ ሃይማኖታዊ ስነምግባርን ያረከሰ ድርጊት በወንዱ ተሸራሚጭ የሚፈፀም ሲሆን የሁኔታው መከሰቻ (የሚደረግባቸው) ደግሞ ሴት ሽሌዎች ናቸው። በሴቶቹ ሽሌዎች ላይ የሚፈፀመው ያልተለመደ ኢ-ባህላዊና ኢ-ምግባራዊ ሁኔታ በባህላችን ያልተለመደ ሲሆን በካዛንችስ ምድር መፈፀሙ የሚያመለክተን ቁምነገር ቢኖር በማህበረሰቡ የአኗኗር ዘይቤ ላይ ቀስበቀስ ማህበረሰባዊ ህመም እየተከሰተ መምጣቱን ነው። የማህበረሰቡን ህመም የምንረዳው ሴት እና ወንድ "ሽሌዎች" የየራሳቸው ገድለ ወሲብ ከሚተረኩበት የአገላለጽ ስልታቸው ከሚያወጡት ቃላትና ሀረጋት ነው።

የሁኔታው አቀራረብና አወቃቀር ሥልት ረገድ ሴቶቹ (ሽሌዎቹ) ስለወንዱ ተሸራሚጭ የሚተርኩት ትዝብት አክል ገድለ ወሲብ ብቻ ሳይሆን ወንዱ ተሸራሚጭ በአንዛሩ የሚተርከው መልክዓ ወሲብ ድርጊትም ተጣምረው የሚያመለክቱት ሁነት ምንድን ነው ብለን በመጠየቅ የምናገኘው ምላሽ በፍካሬ ነጥሮ ሲወጣ ማህበረሰባዊ ህመም ያልኩትን አመለካከት የሚያጠናክሩ አስረጂዎች ናቸው። የሴተኛ አዳሪዋን የኢ-ሰብአዊነት መጠንና ልክ ምን ያህል የከፋ መሆኑን የምንረዳው እራሷ ሴተኛ አዳሪዋ ወንዱ ተሸራሚጭ የሚያደርስባትን ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊት በምታወራው ለጓደኛዋ በምትተርከው ድርሳነ ካዛንችስ ገድለ ወሲብ ለመረዳት ይቻላል። የሚገርመውና የሚያስደንቀው ወንዱ ተሸራሚጭ በአካሏም በመንፈሷም ሌሊት ሲያደርስባት ያደረውን ሁነት ተቀብላ ከመተረክ የዘለለ ሌላ ሁኔታውን ለመለወጥ የሚያስችል ሀሳብ ሲነገር/ስትናገር አይሰማም። ድርጊቱን በፍርሀት ተቀብላ ብቻ የተፈጸመባትን "በፀጋ" በማግስቱ አንዷ ለሌላዋ እነሆ የዛሬው ሌሊት የአዳር ወሲባዊ ድርሳኔ ትላለች። ሴቷ ሽሌ ወንዱ ተሸራሚጭ የፈፀመባትን ኢ-ስነምግባራዊ የሆነ ወሲባዊ ድርጊት "በፀጋ" የተቀበለችው መስላ በ "ነፃነት" (ያለምንም ሀፍረት) መተረኳ የሷን ነፃ ባርነት የሚፈክርበት ሁኔታ ያለመሆኑን በአንዛራዊነት የሚጠቁመን ነው። የዚህ ሀሳብ ማንጸሪያው "የሽሌዎቹ የድርሳንና የገድል ምንጩ ወንዱ ተሸራሚጭ ነው" (ገጽ፣ 10) የሚለው ነው። ጥያቄው እነዚህ ሁለት "አማጺያን" ተሸራሚጮች በእርግጥ ነፃ ናቸው ወይ? የሚል ነው። ሴቷ ሽሌ ሀሳቧን ሳታፍር መግለፅ መቻሏ ወንዱ ሽሌ የሚፈፅምባትን ኢ-ሰብአዊ ድርጊት በነፃነት ጧት ለጓደኞቿ መተርኳ ሀሳቧን ያለምንም የባህል ገደብ መግለፅ መቻሏ "ነፃነት" አላት ሊያስብላት ይችላል? ወንዱ ተሸራሚጭስ? በምሽት አገግሞ? በሌሊት የሚፈፅመው ኢ-ባህላዊ የወሲብ ድርጊትና ከስነምግባር የወጣ ወሲባዊ ተግባር ባህሉ የነፈገውን የግልፅነት ችግር በነፃ እና በነፃነት ተገበረ ለማለት የሚያስችል ሁነት ነው? እነዚህንስ ሁለት ባህልና ኃይማኖት የቀየዳቸው ፍጡራን በተለያየ ገፅታ ከካዛንችስ አንዱ በበላይነት ድርጊት ፈፃሚ ሌላዋ በበታችነት ድርጊት ተቀባይ ሁነው የሚከናወነው ኢ-ባህላዊ ሁኔታ የሚያመላክተን እውነትስ ምንድን ነው? ሴትዋ ሽሌ የምታወራው የባህሉን ገደብ ጥሳ አይባሌ ቃሎችን (Taboo words) ያለምንም "መቀባባት" እንዳሉ የምታወርዳቸው ነፃ ስለሆነች አይደለም። የወንዱንም "ሽሌ" ኢ-ስነምግባራዊ የአወሳሰብ ድርጊት ያለምንም ሀፍረት የምትደስኩረው ለነፃነቷ መግለጫ አስባ ወይም በድርጊቱና በሁኔታው ተደስታበት አይደለም። ለዚህ የሰብአዊነት መንጠፍ ክስተት የዳረጋትን ማህበረሰብ መናቋን የሚጠቁመ እንጂ። "ሽርመጣ" "ሽሌ"፣ ወዘተ እያለ

የሚያንቋሽሻትን ማህበረሰብ ባህል እንዴት አድርጋ ልታክብረው ትችላለች? "አስቦና አዙሮ የሚመለከት ፍጡር ሁሉ፣ (ሴተኛ አዳሪም ብትሆን) መታማትን፣ መነቀፍንና መሳቂያ መሳለቂያ መሆንን ስለማይፈቅድ" (ሴተኛ አዳሪ፣ ገፅ፣ 5) እንዳላቸው እናነ ያላከበራትን ማህበረሰብ የነቀፋትን ማህበረሰብ ባህልና ልማድ ባታክብር አይፈረድባትም። በዚህ ምክንያት ንግግሯ ሁሉ ቡና ቤት ገብታ የተገናፀፈችው "ነፃነታዊ ባርነት" እንጅ ከሰው እኩል የሚያደርግ "ክብራዊ ነፃነት" አለመሆኑን አመላካች ነው። ይህም ነጥሮ የሚወጣው የወንዱ ተሸራሚጭ የሚፈፅምባትን ከሰዋዊ ተራክቦ የወጣ እንግዳና ያልተለመደ ወሲባዊ ተግባር ስንመለከት ነው።

ለዚህ ሁነት ምስክር ማቆም ይቻላል፣ ያውም ሶስት አንደኛው ምስክር ሴቷ ሽሌ ራሷ ናት።

አንዷ፡-

"ለሊት ሲተፋብኝ አያድር መስለሽ" ... ፊትዋን ከስክሳ

"ወይ! እና አደርሽለት ..." እሷም ፊትዋን ከስክሳ ... በናትሽ ደንበኛዬ ነ

ነው ... በዛ ላይ ሁሌ ቼንቶ ይበጥስልኛል" በረዥሙ ተንፍሳ "... እና ሶስት

ወደው አይሆኑ ... ጠረኩለት ..." አምርራ ፊቷን ከስከሰች

"መጥኔ ላንቺ ... እና በትውከት አፉ ጎመሽ ..."

"አ -ህ ተጉመጠመጠ። ተፋ። የተረፈኝን ቢራ ጨለጠና ተከለ ... ወይ![7]

የማይሰለቸው እሱን አየሁ ..." ገድሉ ቀጣለ። (ገፅ፣ 4)

ሌላዋ፡-

"ሌሊቱን ሲንጠኝ አደረ" ... ታይት ያደረገኘው ወደላ እኔነ ጂን ቶኒክን

ሲደጋግም ፈርቻልሽ ነበር። ውይ! ውይ! ሶኬት! ሶኬት! ... ሌሊትማ ልጮህ

ምንም አልቀረኝም"

" ... አትወረውሪውም ነበር..."

"አይ አንቺ! ያን ወደል አህያ በምን ጉልበቱ ... በዛ ላይ ከወንድ መጣላት

ሰልችቶኛል ..."

"... እያወቅሽ ... ሥራ ካጣሁ ሳምንቱ ... በረሃብ ልሞት ምንም አልቀረኝም

... ስለዚህ ምርጫ አልነበረኝም ..." (ገፅ፣ 4-5)

[7] በመጽሐፉ የተገለፀው ቃል "ሀራም" የተባለው በመሆኑ ለመፃፍ "ፀያፍ" ስለሆነብኝ ነው።

ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት ገድለ ወሲብ ገለፃዎች የምንረዳው የሴት ሽሌዋን ውርደት ነው። አንዷ "ሽሌ" ለሊት በወንዱ ተሸራሚጭ የደረሰባትን ክብር የሚነካ፣ ሞራልን የሚሰብር ድርጊት በራሷ በተበዳያዋ አንደበት ሲተረክ ነው። ትርካውን ስትናገር ያለምንም ሀፍረት ሲሆን የሁኔታውን አስከፊነት "ፊትዋን ከስክሳ" ከሚለው ሐረግ ለመረዳት ይቻላል። ገድሉ በዚህ ሁኔታ የሚቀጥል ነው። በመሆኑም በነፃነት የምትገልፃቸው "ሀራም" የተባሉ ቃላት የሚያመላክቱት ሴተኛአዳሪዋ ነፃነት ያላት መሆኑን ሳይሆን "ነፃ ባርያ" መሆኗ ነው።

የሴቷ ሽሌ "ነፃነት" የተፈፀመባትን ኢ-ስነምግባራዊ የሆነ ወሲባዊ ተራክቦ ያለምንም እፍረት "በነፃነት" መግለጿ ነው። ባርነቷን የሚያመላክተው ደግሞ ወንዱ ተሸራሚጭ እንደሰው ሳይሆን እንደዕቃ በመቁጠር፣ ገንዘብ ሳላወጣባት ብቻ እንደፈለገው በሰውነቷ ማዘዝ መቻሉ ነው። "ሁሌ ቼንቶ ይበጥስልኛል" የሚለው አባባል የሚጠቁመው ገንዘብ የወጣባት ስለሆነች ወንዱ የፈለገውን ሊያደርጋት የተገዛች "ባርያ" መሆኗን ያሳያል። ለዚህም ለዘመናዊ ባርነት የዳረጋት ደግሞ ምን እንደሆነ "... ሥራ ካጣሁ ሳምንቱ ... በርሃብ ልሞት ምንም አልቀረኝም ..." የሚለውን አባባሏን ስንሰማ በርሃብ ከመሞት ክብሯን ለወንዱ ተሸራማጭ አሳልፋ መስጠቷን እንረዳለን። ይህንን የሚያውቀው ወንዱ "ሽሌ" የሴቷን የሴትነት ገላ እንዳሻው ከስነምግባር ውጭ በሆነ መልኩ "ሊዝናናበት" ይችላል። ለዚህ ነው " ... ስለዚህ ምርጫ አልነበረኝ ..." ስትል እያወቀች ክችግር አንባር ራሷን ለባርነት አሳልፋ ትሰጣለች። ይህ የሚጠቁመን ነፃነቷ የሚፈጸምባትን ድርሳነ ወሲብ በመተረክ ላይ ብቻ የተመሠረተ ሲሆን በገንዘቡ የፈለገውን ኢ-ሰባዊነት ተግባር ወንዱ ሊፈፅምባት የሚችል በመሆኑ እና እሷም አምና የተቀበለችው ስለሆነ ባርነቷን ያመላክታል። ስለዚህ ነፃነት የሚያስብል አለመሆኑን ከራሷ አንደበት እንረዳለን።

ሁለተኛው፣ ወንዱ ተሸራሚጭ ራሱ የሚያወራው ገድለ ወሲብ ሴቷን ሽሌ ምን ያህል ዝቅ አድርገው እንደሚመለከቷት እና ምን ዓይነት ኢ-ባህላዊ የሆነ የወሲብ ተግባር ሊፈፀምባት እንደሚቻል የሚገልፅበት ሁኔታ ነው። ወንድ ተሸራሚጭ ጓደኞሞች ስለወሲብ አደራረግ፣ ወሲባዊ ምርጫን ሲወያዩ አንዱ ለሌላው ሲተርክ ከገፅ 42 እስከ 49 ድረስ ተገልጿል። የወሬያቸው ወሲባዊ ሁኔት ወንዱ ሴቷን እንዴት ዓይነት የወሲብ ድርጊት በፈጽመባት ሊረኩ እንደሚችሉ የሚያስረዳ ነው። ወሲባዊ ምርጫውም የግሉ የወንዱ ፍላጐት እንጂ የሴቷ ፍላጐት ያልተካተተበት ነው። ወንዱ ተሸራሚጭ በሴቷ ሽሌ ላይ ከጓደኛው የሰማውን ወይም ከሌላ ሰው የቃረመውን የአወሳሰብ ድርጊት በገንዘቡ "ገዝቶ" በሚወስዳት ሽሌ ላይ መፈጸሙን ለጓደኛው ያወራል። ሴቷ ሽሌም የሰጠችውን ተግባራዊ

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

ምላሽ ሁሉ ሳያፍር ድርጊቱን የባህልን ደንብ በጣሱ ሀራም ቃላት ኢ-ስነምግባራዊ አፈፃፀሙን ይገልፃል። የሚጠቀምባቸው ቃላት፣ የሚገልፀው ሀሳብ እና በሴት ላይ የፈፀመው ወሲባዊ ተራክቦ በባህል ያልተለመዱ ብቻ ሳይሆኑ ድርጊቶቹ እንግዳ የሆኑ ናቸው። ይህ ነው በዚህ አሀድ የምናበው ድርሳነ ካዛንችስ ... መልክዓ ወሲብ አዲስ የሆነ "ያመንዝራ ገሪ" እየተከሰተ መምጣቱን የምንገነዘብበት። ወንዱ ተሸራሚጭ ወይም "ሴት ሸሌ" ከሚደሰኩሩት ድርሳነ ወሲብ በስተጀርባ ሌላ የምንገነዘበው ሁነት መኖሩን ነው። ከዚህ "የአመንዝራ ገሪ" በስተጀርባ ማህበረሰባዊ ህመሙ ቀስ በቀስ እየተስፋፋ ባህላችንን እያነቀዘ፣ ማንነታችንን ሰልቦ እኛነታችንን ጥያቄ ውስጥ የከተተ ሁነት ሆኗል።

እነዚህ ሁለት ምስክሮች ብቻ ሳይሆኑ ሶስተኛው ደግሞ ተራኪው ራሱ "የሸሌዎቹ የድርሳንና የገድል ምንጭ ወንዱ ተሸራሚጭ ነው" ብሎ ሁኔታውን የሚተረጉምበት ጣልቃ ገብ ወግ ነው። አጽንኦቱ ያለው የሴተኛ አዳሪዋን ምፀታዊ ነባ ንግግር ከማንሳቱ ላይ ነው። ስልቱ አሉታዊ ነው። የወንዶቹ ተሸራማጭ ስነምግባራዋ ወሲብ በማንፀርያነቱ የሚያመለክተው። እሷ የሌላትን ነገር እንጂ በወንዶቹ ተሸራሚጮች ዘንድ አዎንታዊ ክስተት ያለውን ነገር አይደለም። የሴት ሸሌ አካላዊ ብቻ ሳይሆን ህሊናዋ እና ልቡናዋም ቆስሏል። አመለካከቷም ነብሏል፤ ጠልቆ አያስተውልላትም። የተፈጥሮ የሆነውን ወሲባዊ ተራክቦ የምትፈፅመው በገንዘብ በተገዛ የግዴታ ስሜት ነው። የድርሳነ ወሲባዊ ገድል ምንጮቿ ወንድ ሸሌዎች ቢሆኑም የሷ ጭንቅ ገድለ ወሲብ ሳይሆን ለመኖር መብላት ስላለባት ነው። ወንዱ ወሲብን የሚፈፅመው "ፍትወት" አስገድዶት፣ የተወጣጠረ ስሜቱን ለማስተንፈስ፣ የተፈጥሮ አጋሩን ፈልጎ ነገር ግን ኢ-ስነምግባራዊ በሆነ ተራክቦ ለመርካት ነው። ከዚህ አንፃር ስንመለከተው "የሴት ሸሌ" የወሲብ ወሬ ብሶትን፣ በምፀት አጅባ፣ የሥጋዊው አካሏ በወሲብ መድቀቁን፣ በወንዱ ተሸራሚጭ ኢ-ስነምግባራዊ ወሲባዊ ተራክቦ መጉዳቱን ከመጠቆሟ ባሻገር፣ የዚህ ወሲባዊ ድርጊት ያልተለመደና ከባህል ያፈነገጠ መሆን ደግሞ ህሊናዋን ሰቅዞ ይዞ ለስነልቡና ስብራት የዳረጋት መሆኑን የሚዳስስ ነው። ምናልባት ማለት የምንችለው ሴት ሸሌ በዚህ ሁኔታዋ የተፈጥሮ የሆነውን ወሲባዊ ተራክቦ በአግባቡ ባለመፈፀሙ የደረሰባት የወንድ የበላይነት ድርጊት የተፈፀመባት ጥቃት የነፍሷን መምከን የሰውነቷን ጨርሶ መረገጥ የሚያመለክት እንጂ ባህሉን ለመበቀል "ንግግራዊ ነፃነት" በአዎንታዊ መልኩ የሚተረጉም አለመሆኑን ነው። ዘለቅ ብለን ስንፈክር ደግሞ ሌላ አንፃር አለ።

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

"ኧረ ስንት አይነት ወንድአለ መስለህ ..."

"ምስጢሩ ምን ነበር ...?"

"እህ ... ወንድ አምጭልኝ አለኝ"

"ወ - ን - ድ?"

"አዎ! ወንድ"

"ሰክርሽ ..."

"ኧረ ባክህ ስንት ወንደ አለ ..."

"እንዴት?"

"በቃ ቡሽቲ መሆኑን ወዲያው አወቅኩ" (ገፅ፣ 16-17)

ሴታ ሽሌ በወንዱ ተሸራሚጭ የተነጠቀችው አካላዊ ነፃነቷን ብቻ አይደለም። በገንዘቡ ስለገዛት ፍትወታዊ ተራክቦውን (ምንም እንኳ የሰለቻት በመሆኑ ባትሻውም) ወንዱ በፈለገው እንጂ በሴታም ጭምር የሚካሄድ አለመሆኑ አንዱ በደሏ ነው። ከዚህ የባሰ የሚከፋው ግን የሱን ምስጢር ለመሸፈን እሷን በገንዘብ ደልሎ ወንዱ ሌላ ወንድ ለፍትወት ማርኪያ እንድታመጣለት መደረጓ ነው። ሁኔታውን ስትተርክለት አድማጭዋ ራሱ ሊቀበላት (ሊያምናት) አልቻለም። የነገረችው እውነት ስላልመሰለው አድማጩ የሰማውን ቃል ማመን አቅቶት "ወ - ን -ድ?" በማለት እያንዳንዷን ድምፅ ለያይቶ አጽንኦት ሰጥቶ ረገጥ በማድረግ መጠየቁ የወሲባዊ ክስተቱ እንግዳነት አሳስቦትም አስገርሞትም ለመሆኑ አሌ የማይበል ነው። ለሷ ግን ምንም ያልመሰላት ይመስላል። "አዎ! ወንድ" በማለት "አዎ" የሚለውን አጉልታ "ወንድ" የሚለውን ቃል ደግሞ ቀለል አድርጋ የገለፀችው። ለምን? የድርጊቱ ሁነት ለሷ አዲስ አይደለም። ፍላሬው ግን የወደፊት "እድሏ" እየታያት "ኧረባክህ ስንት ወንድ አለ ..." የምታዝንበትም የቀቢጸ ተስፋ ሁኔታ ያሳያል። በተለይ ወንድ ልታመጣለት ወጥታ "ቡሺቲዎች" ይገኙበታል የተባለውን ቦታ ሁሉ አስሳ አጥታ ከተመለሰች በኋላ ከሰውየው ጋር የፈፀመችው ሁኔታ አዕምሯዋን የሚያቆስል ስሜቷን የሚገዳ ድርጊት ነበር።

"መጨረሻ ... እጄን ደክመኝ ... ተናደድኩ ... ስሜቱ መጣ መሰለኝ ... አሁን አሁን ... ሲል ... በቃ ሳላስብ ... እስከመጨረሻ ... በኃይል ጠርሙሱን ገፋሁት ..." (ገፅ፣ 20) የሚለው አገላለፅ የሴቷን ስሜት የገዳ መሆኑን ሲያመላክት በሌላ መልኩ ደግሞ ለባህላችን እንግዳ የሆነ ወሲባዊ ክስተት ወደሀገራችን እየገባ መሆኑን የሚያጠይቅ ነው።

የሴታን ሽሌ አካላዊ እና ስነልቡናዊ የጐዳ ከመሆኑ በተጨማሪ በካዛንችስ የሚካሄደው ገድለ
ወሲብ መጠኑና ዓይነቱ የበዛ የአመንዝራው "ጐራ" ዘረፈ ብዙ መሆኑን ያመላክታል።

"የሴታ ሽሌ" ድርሳነ ካዛንችስ፣ ወሲባዊ ድርጊት ተረክ አቀራረቡ ምፀት ለበስ ነው።
ስልቱ በአሽሙር የታጀበ ነው። "የወንዱ ተሸራሚጭ እና ሴታ ሽሌ ተጎዳኝተዋል። ሴታ
ሽሌ ራሷን በወንዱ ተሸራማጭ ውስጥ ታይበታለች። "ወንዱ ተሸራሚጭ" በካዛንችስ
የሚፈፅመው ኢ-ባህላዊ እና ኢ-ስነምግባራዊ ገድለ ወሲብ የሚፈፀምባት ራሷ ናት።
የወንዱን ተሸራሚጭ ገድለ ወሲብ ስትተርክ ራሷ የታሪኩ አንዱ አካል መሆኗን
አልዘነጋችውም። ከላይ ከፍ ሲል በተጠቀሰው "ኧረ ስንት አይነት ወንድ አለ መሰለህ ..."
በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ በካዛንችስ ውስጥ በሴተኛአዳሪነት ስትሠራ "የወንዱን
ተሸራሚጭ" የሽርሙጥና ባህርይ ምን ዓይነት ገጽታ ያለው መሆኑን ከልምዷ ለይታ
ታውቀዋለች። ለዚህ ነው ስለቱ በአሽሙር የታጀበ ነው ያልኩት። ስለወንዱ ስትተርክ
የትረካው ማዛጊያ ወይም ማጓጓጉ እሷ መሆኗን ስለምታውቅ ራሷንም እየታዘበች ነው
ስለወንዱ የምታወራው። "እንዲህ አይነት ወንዶችን በደንብ አውቃለሁ ... ብዙ ጊዜ
አጋጥመውኛል ..." (ገፅ፣ 17) በማለት ስትናገር የወንዱን ተሸራሚጭ የልዩ ልዩ የአወሳሰብ
ባህርይ በስራው ከመቆየታ የተነሳ አውቃለች። ይህንንም የበለጠ ለማሳመን ተራኪዋ
"ድንግሌን የሰጠሁት - ካዛንችስ፣ የሸረሞጥኩት - ካዛንችስ፣ ... ቡና ቤት ስሠራ
የወለድኳት ልጄ ሰላሳ አመት ሆኗታል ..." (ገፅ 17) ትላለች። ይህን የሷን የሽርሙጥና
የረኸርም ዘመን ቆይታ በዋቢነት ስናቀርብ ከላይ የተገለፀውን የሴታን ሽሌ ስለወንዱ ሽሌ
የምትተርከውን የራሷንም ሁኔታ በምፀት የምትገልጸበት መሆኑን አመላካች ነው። በሌላ
ገጹ ደግሞ በካዛንችስ የሚከናወነው ልዩ ልዩ ኢ-ባህላዊ እና ኢ-ስነምግባራዊ ወሲባዊ
ድርጊቶች ዛሬ የተጀመሩ ሳይሆኑ ቆየት ያሉ መሆናቸውን ከተራኪዋ ለመረዳት ይቻላል።
ነገሩ ሴታ ሽሌ የወንዱን ተሸራሚጭ ገደለ ወሲብ ሁኔታ በመተረክ ብቻ የሚቆም
አይደለም። ይህን ተገንዝባ ከራሷ እጣ ፈንታ ጋር አጣጥማ የወንዱን (ቡሽቲ) ሁኔታ
በትዝብት እንዲህ ትላለች።

> "... አይ <u>የሰው ነገር</u> ... ወንበሩ ላይ የነበረውን
> አምቦ ውሃ አነሳና ከነብርጭቆው ወደታች
> ዘቀዘቀው ..."
> "ባዶውን ጠርሙስ ሰጠኝና ... እያቃሰተ ...
> <u>ክተቺው</u> አለኝ ..." (ገፅ፣ 197 አጽንኦቱ የኔ)

"የሰው" የሚለውን የወል ስም "የወንድ" በሚለው እንተካው። የሴታ ሽሌ ምፀታዊ ትዝብት የሚያርፈው እዚህ ላይ ነው። በወንዱ ተሸራሚጭ ገድለ ወሲብ ራሷን ያየችበት። ተፈጥሮ ውሷን የሳተች ይመስል "ድርጊት" የተለዋወጠበት ሁነት። ተፈጥሮአዊ ክስተትን፣ ኢ-ልማዳዊ ድርጊት የሻረበት መሆኑን የታዘበችበት ነው። የሴታ ተፈጥሮአዊ የወሲብ "ልምድ" ተሸሮ አዲስ የሆነ የወሲብ ተፈጥሮአዊ ፍልሰት እየታየ መሆኑን ሴታ ሽሌ በወንዱ ተሸራሚጭ በማየታ "አይ የወንድ ነገር ..." በማለት ተፈጥሮዋን የተነጠቀች መሆኑን በምፀት ትገልፃለች። የዚህ ፍካሬ ሴታን በአካል ብቻ ሳይሆን በመንፈስም ሰሜታን አድርቆታል። ምንም እንኳ ከተሰማራችበት "የመ.ያ" ሁኔታ አንፃር ወሲብን ፈቅዳ (ፍትወት ፈልጋ) ባትወጣም የወሲባዊ ድርጊት ተፈጥሮአዊ ውሉን መሳቱ ሴትነቷን ያጣች ያህል ሳያስቆጫት እንዳልቀረ አገላለጿ ይጠቁማል። ይህ ነው የሰብእናዋ መንጠፍ ሁኔታ ምን ያህል ዓይነቱና መጠኑ የሰፋ መሆኑን የሚያስገነዝበን። "የወንዱ ተሸራሚጭ" ወሲባዊ ልማድ ዓይነቱ እየበዛ አያሌ ያልተለመዱ እንግዳ ሁነቶች በተከሰቱ ቁጥር የሁነቶቹ፣ የሁኔታ አፈፃፀም ተቀባይ እሷ መሆኗ ደግሞ የሰብአዊነቷ ክብር ማጣት አስከፊ እየሆነ መምጣቱን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

ሴታ ሽሌ ሽቀጥ ናት። "ወንዱ ተሸራሚጭ" ሲፈልግ በገንዘቡ ገዝቶ እሱ በፈለገው ሁኔታ የተወጣጠረ ስሜቱን ያበርድባታል። አንድም ርቃኗን አቁሞ ተክለሰውነቷን በማየት ብቻ ያለምንም ተራክቦ በብርድ ገትሮ ሲፈልግ በማየት፣ ሲሻው በመዳሰስ "በርቃነ ስጋዋ" ብቻ ይረካል። የሷ ተግባር አድርጊ የተባለችውን ማድረግ ብቻ ነው። በገጽ 23 ላይ ተራኪዋ የምትነግረን በእድሜ የገፉ አዛውንት 100 ብር ከፍለው ከወሰዷት በኋላ ርቃነ ስጋዋን አልጋ ጠረዝ ላይ ያለምንም ልብስ አስቀምጠው "ብልቷን" እየተመለከቱ የብልቱን ስም እየጠሩ የሚፎክሩና የሚሸልሉ፤ በዚህም ለሰላሳ ደቂቃ ያህል ርቃኗን አስቀምጠው በመንቆራጠጥ ፎክረው የረኩ እንደገጠሟት ትገልፃለች። ይህ ሁኔታ ሽማግሌውን ቢያረካቸውም የሴታን ማንነት ግን ቅስም የሚሰብር ድርጊት ነው። ርቃኗን በመሆኗ ብርድ አካሏን ሲገዳ መንፈሷን ደግሞ በእጅጉ ያደቀቀ ሴትነቷን ወደ ፍጹም ሽቀጥነት የለወጠ ነው። " ... 100 ብሬ ትዝ እያለችኝ ... አንድ ግማሽ ሰዓት ከፎከሩ በኋላ ተገለፍልፎ ... ወደቀ ..." (ገፅ፣ 23) የሚለውን ስናነብ የሴታን ለወንዱ <u>የሸቀጥ</u> ዕቃ መሆኗን ያስገነዝበናል።

ምዕራፍ አራት

ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት ዐቢይ ትኩረት የተሰጠው የሴተኛ አዳሪ የሰብአዊነት መንጠፍ (Dehumanization) ነው። ይህንን የሴተኛ አዳሪነትና የሰብአዊነት ጥያቄ ሁኔታ ለማሳየት ትንነታኔ የተደረገባቸው ሦስት የአማርኛ ልቦለዶች ናቸው። እነዚህም ልቦለዶች ሴተኛ አዳሪ፣ ሌቱም አይነጋልኝ እና መነልየ መነልይ ዘካዛንችስ ናቸው። በእነዚህ ልቦለዶች ውስጥ የሴተኛ አዳሪነት የሰብአዊነት መንጠፍ መጠንና ልክ ከማህበራዊ ባህላዊ አመለካከቶች አንፃር አቆራኝቶ በመመልከት በየልቦዶቹ ሰብረው የሚወጡትን በሴተኛ አዳሪነት ላይ የሚደርሰውን የኢ-ሰብአዊነት ሁነት በትንታኔው አሳይቷል።

በሴተኛ አዳሪዎች ላይ የሚደርሰው የኢ-ሰብአዊነት ድርጊት በልቦለዶቹ ውስጥ ነጥረው የሚወጡት በፍካሬ ነው። ፍካሬውም ትኩረቱ (1) ከማህበረ ባህላዊ እና ከስነልቡናዊ ምክንያቶች የመነጨነው። ልቦለዳዊ ትረካ የማህበራዊ ባህል አንድ ዐቢይ ገፅታና የማህበራዊ ባህላዊ ክንዋኔዎች ውጤት ነው። ይህም ውጤት ከማህበራዊ ለውጥ ተለይቶ ሊታይ አይችልም። በየልቦለዶቹ የታየው የሴተኛ አዳሪ የሰብአዊነት መንጠፍ በአንድምታ ጐልቶ ሲወጣ ምክንያት ሆኖ የተገኘው የወንዱ ግብዝነት ነው። የእዚህ ግብዝነት ስሩ ደግሞ ባህሉ ነው። በፍካሬው ሴተኛ አዳሪዋ የወንዱ ግብዝነት ስሩ "ነቱ" (ምንጩ) የበቀለበት ባህል መሆኑን በምዕት አሳይታለች። በማህበረሰቡ የተዛባ አመለካከት ሳቢያ ሴተኛ አዳሪዋን ወንዱ ተሸራሚጭ እንኳ ሳይቀር ከሰው እኩል የማይመለከታት መሆኑን በሦስቱም ልቦለዶች የታየ ሁነት ነው። ይህንን የተዛባ አመለካከት ሴተኛ አዳሪዋ ከግብዝ ወንዶች ጋር በምታደርገው ክርክር ርቃኑን ያስቀረችበት መሆኑን በትንታኔው ተመልክቷል።

(2) ስነልቡናዊ ተፅእኖው በሴተኛ አዳሪዋ ላይ እንዲከሰትባት አስተዋፅኦ ያደረገው ሌላው ማህበረ - ባህላዊ ምክንያት ነው። ለሴተኛ አዳሪዋ የሰብአዊነት መንጠፍ ሌላው ምክንያት የወንዱ ተፈጥሮአዊ ባህርይ በባህሉ ተቃኝቶ ከማደግ የመነጨ ነው። የሴተኛ አዳሪዋን የሰብአዊነት መንጠፍ ሁነት ለመመርመር ከፍ ብለን ያነሳናቸውን ማህበራዊ ባህላዊ እና ስነልቡናዊ ሁኔታዎች ከልቦዶቹ አውድ ጋር አገናዝቦ መተንተን አስፈላጊ ነው።

በሶስቱ ልቦለዶች እየሰበሩ የሚወጡት የሴተኛ አዳሪነትና የሰብአዊነት ጥያቄ ሲሆኑ እነዚህም ሁነቶች የሚከሰቱበት ሁኔታዎች የሴተኛ አዳሪዋን የጠቅላላ የሰብአዊነት መንጠፍ የሚያሳዩ ናቸው። እነዚህም ሁነቶች በትንታኔው በፍካሬ ነጥረው የወጡት መናቅ፣ መገለል እና ባይታወርነት ናቸው። እነዚህ በትንታኔው የታዩት ሁነቶች በሴተኛ አዳሪነት ላይ ያስከተሉት ባዶነትን፤ ተስፋ መቁረጥንና የነገን አለማለምን እንደሆነ በትንታኔው የተገኙ ውጤቶች ናቸው። በሴተኛ አዳሪነት "ሙያ" የተሰማራቸው ሴት መናቋ፣ መገለሏ እና ባይታዋር መሆኗ ብቻ ሳይሆን እነዚህን ሁነቶች እራሷ አምና እንድትቀበል ባህሉ ያስገደዳት መሆኑም ታይቷል።

ማህበረ - ባህላዊ ተፅእኖው ቅርንጫፈ ብዙ ነው። በሴተኛ አዳሪነት "ሙያ" ተሰማሩ ሴተኛ አዳሪዎች ላይ የሚያደርሰው የኢ-ሰብአዊነት ድርጊት በማህበራዊ እና ባህላዊ ሁኔታዎች ላይ ብቻ ተወስኖ የሚያቆም አይደለም። ልማዳዊ ሥርዓቱ ሃይማኖታዊ እና ርእዮተዓለማዊ መሠረት እንዲኖረው በማድረግ የሴተኛ አዳሪነትን የሰብአዊነት መንጠፍ ሁነት የከፋ ያደርገዋል። ይህም በሃይማኖቱ "ኃጢያተኛ"፣ በመንገሥታዊ ህጉ ደግሞ ወንጀለኛ በማድረግ ፍጹም እንጥፍጣፊ የሌለው የሰብአዊነት ድርቀትን ያላብሳታል። ሴትነት ባተለይም ሴተኛ አዳሪነት እዳ ነው። ይህ ሁነት በሶስቱም ልቦለዶች የታየ ተመሳሳይ እውነታ ነው።

በትንታኔው የታየው ሌላው ሁነት በወንዱ "ተሸራሚጭ" የሚፈፀመው ካዛንችሳዊ ሁኔታ ነው። <u>በመጎልየ መጎልይ ዘካሳንችስ</u> ውስጥ በፍካሬ ነጥሮ የወጣው ሁነት የማህበረሰባዊ ህመም ሁኔታ ነው። ይህም "ህመም" ባህላዊ እሴትን የተፈታተነ፣ ማህበረሰባዊ ማንነትን ጥያቄ ውስጥ የጨመረ ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊት ነው። የወንዱ 'ተሸራሚጭ" ምግባረ ብልሹ መሆን በሴተኛ አዳሪነት ላይ ያሳይ የነበረው ንቀት የአታላይነት፣ የግብዝነት እና የአስመሳይነት መሆኑን ያሳየ ሁነት ነው። በባህሉ እና በማህበረሰቡ ውስጥ ትልቅ ኢ-ስነምግባራዊ ሁኔታዎች እየተከሰቱ ለመምጣታቸው በዚህ መጽሐፍ ላይ ታይቷል። ልቦለዱ ራሱ በቅራኔ የተመላ የነፍስና የሥጋ ሕይወት እየተጣሉ፣ እየተዛመዱ እና እየተለያዩ ግን እንደገና ተመልሰው እየተቃቀፉ የሚሄዱበት መሆኑን የታየበት ነው። <u>መጎልየ መጎልይ ዘካዛንችስ</u> ድርሰት ድርሳነ ወሲብ ገድለ ሽርሙጥና እና ገድለ ስካር ይመስላል እንጂ በአንድምታ ነጥሮ የወጣው ሁነት "የማህበረሰባዊ ህመም" በማህበረ-ባህላዊ ኑሮው ውስጥ ቀስ እያለ እየገባ ቁንቁን እንዳነከተው እንጨት በቁም መድረቁን የሚያሳይ ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

በልቦለዶቹ ውስጥ በሴተኛ አዳሪነት "ሙያ" ተሰማርታ የምትገኘው "ሴት" መናቅ፣ መገለል እና ባይታወር መሆን ተከታታይ እና ቋሚ ሁነቶች ናቸው። እነዚህ ሁነቶች በየልብ ወለዶቹ ውስጥ ተከታታይነት እና ወጥነት ያላቸውን ትርጉሞች ከማስገኘት በተጨማሪ የየልብወለዶቹን "ፈር" ሰብረው የሚወጡ ድርሰቶቹ ከተፀነሱበት ዘመንና ቦታ ጋር የሚተረጐሙ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ አንድምታዎችንም ፈጥረዋል። ልቦለዶቹ ማህበረሰቡን የሚወቅሱ እየተከሰተ ባለው ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊት ላይ የሚያዝኑ፣ የሚቆዝሙ ብቻ አይደሉም። በዋናነት መጪውን የሚተነብዩ ናቸው። ልቦለዶቹ በጥቅሉ የማህበረ-ባህላዊ አመለካከት በሴተኛ አዳሪነት ላይ የተዛባ መሆኑን፣ የወንዱን "ተሸራሚጭ" ባህርይ እና ግብዝነት እያመጣው ያለው ኢ-ሞራላዊ ሁነት ሥጋትንና ጭንቀትን አቆራኝቶ የያዘ በመሆኑ እነዚህ ሁኔታዎች ተቀይጠው የቀረበባቸው ሥራዎች ናቸው ለማለት ይቻላል።

በምዕራፍ ሦስት በስፋት እንደተመለከትነው ልብ ወለዶቹ የሴተኛ አዳሪነትን የሰብአዊነት መንጠፍ ሁነት በሚያሳዩ ስነልቡናዊ ስብራትን በሚፈጥሩ ኢ-ሞራላዊ ትእይንቶች የተሞሉ ናቸው። በሦስቱም ልብ ወለዶች ውስጥ የሚታዩ፣ በተቀሩት የየልብ ወለዶች ሁነቶች እና ትእይንቶች ላይ መጥፎ ድባባቸውን ማጥላት የሚችሉ፣ በተለይ ሁለት ኢ-ሞራላዊ ትእይንቶች አሉ። እነዚህም ትእይንቶች አንደኛ፣ ሴታ "ሽሌ" እና ወንዱ "ተሸራሚጭ" የተገናኙበት ሴተኛ አዳሪነት እና የወንዱ አመንዝራነት የተፋጠጡበት የቡና ቤት ትእይንት፣ ሁለተኛ የሴተኛ አዳሪዋ የተፈጥሮ ሴትነት በወንዱ "ተሸራሚጭነት" ስትቀማ እያየች ስለወደፊት እጣ ፈንታዋ የውስጥ እንባ ያነባችባቸው ናቸው። በሁለቱም ትእይንቶች ውስጥ የሚታይ የብርሃን እና ሞራላዊ ግዴታዎች የሉም። በሁለቱም ትእይንት ውስጥ የሴተኛ አዳሪነት የሰብአዊነት ጥያቄ እና የወደፊት እጣ ፈንታ ወደ አስፈሪ ስነልቡናዊ ቅዠትና እና አሳፋሪ ኢ-ምግባራዊነት ተለውጧል። በመሆኑም በሁለቱም ትእይንቶች ውስጥ የማህበረሰባዊ ህመም ዋዜማ "ጣር" ይቀነቀናል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁነቶች እና ሁኔታዎች በጥናቱ የተገኙ የጥናቱ ፍሳሬ ንባብ ድምር ውጤቶች ናቸው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ማጣቀሻ ጽሑፎች

መጽሐፍ ቅዱስ። የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ። የኢትዮጵያ ቅዱስ ማህበር፣ አዲስ አበባ፣ 1980 ዓ.ም.።

ስለ ዝሙት አዳሪዎች በብሔራዊ ደረጃ የተደረገ ጥናት። ጥቅምት 1967 ዓ.ም.

ስብሐት ገብረእግዚአብሔር። ሴቱም አይነጋልኝ። ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፣ አዲስ አበባ፣ 1993 ዓ.ም.።

ተድባበ ጥላሁን። መጎልየ መጎልይ ዘካዛንችስ። (አሳታሚ ስንዱ አበበ)፣ አዲስ አበባ፣ 1996 ዓ.ም.።

አልማዝ ደጀኔ። ሴተኛ አዳሪነት በኢትዮጵያ። እቴመላምቺ። በኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የሴቶች ኮሚቴ የተዘጋጀ፣ 1967/68 ዓ.ም.።

አስካለ ለማ። ገፀ-ሴት በአማርኛ ልቦለድ አ.አ.ዩ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነጽሑፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፣ 1974 ዓ.ም.።

አሰፋ መሉጌታ። የከተማ ሕይወት በአምስት ደራሲያን የልቦለድ ሥራዎች አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፣ 1980 ዓ.ም.።

አንዳርጋቸው ተስፋዬ። የሴተኛ አዳሪነት የሚያስከትለው ችግር። በዩንቨርስቲ ከየቀድሞ ተማሪዎች ማኅበር መጽሔት፣ 1959 ዓ.ም.።

እናኑ አጎናፍር። ሴተኛ አዳሪ። ብርሃንና ሰላም የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1956 ዓ.ም.።

ንጉሤ ተፈራ እና አለማየሁ ፀጋዬ። "ማህበራዊ ችግሮችና መፍትሔያቸው በአብዮት ሂደት።" መስከረም። በኢሠፓ አኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ርእዮተ ዓለም መምሪያ የሚዘጋጅ። ቅፅ፣ ቁጥር 12፣ መጋቢት 1975 ዓ.ም.።

ደጀኔ ማንደፍሮ። የሴተኛ አዳሪዎች የስምለውጥ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ለአርትስባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፣ 1987 ዓ.ም.።

ደጀኔ ወልደ ትንሣኤ። ማህበረሰባዊ እውነታና የአቀራረብ ቴክኒክ በአሥራ ዘጠኝ ሃምሳዎቹ የአማርኛ ቤሣልቦለዶች ውስጥ አ.አ.ዩ.፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፣ 1979 ዓ.ም.።

ALS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

ደምሰው ገ/ኢየሱስ። ሴተኛ አዳሪነት በአራት የአማርኛ ረዥም ልቦለዶች ውስጥ። አ.አ.ዩ.። ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ 1996 ዓ.ም.።

ደስታ ተክለወልድ። ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ፣ 1962 ዓ.ም.።

የዝሙት አዳሪነት ጠባይ፣ መነሻና ችግር። በኢትዮጵያ አስር ከተሞች የተደረገ የመስክ ጥናት በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የማህበራዊ ጉዳይ መምሪያ የተዘጋጀ፣ 1968 ዓ.ም.።

ዮሐንስ አድማሱ። አስኪተጠየቁ። ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1990 ዓ.ም.

ዮናስ አድማሱ። "አስረኛነኩዋ!፣ ሀዲስ አለማየሁና የማህራዊ ሂስ ስልታቸው"፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል፣ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ በምርምርና ህትመት ክፍል፣ የተዘጋጀ መድበል፣ አ.አ.ዩ፣ አዲስ አበባ፣ 1992 ዓ.ም.።

ፀዳለ ዘውዴ። ዝሙት አዳሪነት በአርባና ሀምሣ ዐሥርታት የአማርኛ ልቦለዶች አ.አ.ዩ. በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፣ 1976 ዓ.ም.።

ፀጋዬ ገብረመድህን። እሳት ወይ አበባ። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1966 ዓ.ም።

ዘሪሁን አስፋው። የስነጽሑፍ መሠረታውያን። ንግድ ማተሚያ ድርጅት አዲስ አበባ፣ 1992 ዓ.ም.

ኃይለገብርኤል ዳኜ። "የኢትዮጵያ የትምህርት ፍልስፍና"፣ ውይይት። በኢትዮጵያውያን ዩኒቨርስቲ መምህራን ማህበር የሚታተም መጽሄት፣ ቅፅ 2፣ ቁጥር 2፣ (ታህሳስ፣ 1961)።

Comba, P. List of Books in Amharic. In the Ethiopian Collection of the University College, Addis Ababa 1961.

Gerard, A. Amharic Creative Literature. The Early Phase: In the Journal of Ethiopian Studies, vol. VI No.2, July 1968

Getachew Araya. The Municipality and the Brother Legalized vs Illegal Prostitution. Senior Essay, H.S.I.U. may 1968

Kane, L. Thomas. Ethiopian Literature in Amharic. Wiesbaden: Otto Harrassomitez, 1975.

Laketch Dirasse. The Socio Economic Position of Women in Addis Ababa (the case of Prostitution.) Boston University Graduate School, P.H.D. 1978.

Lema Gutema. Problems of Prostitution in the Urban Areas of Ethiopia. Law school H.S.I.U., Addis Ababa 1968.

Molvaer, R.K. Tradition and Change in Ethiopia. Leiden. E.J. Brill. 1980.

Maxim Gorki. Literature and Life. Trans by Edith Bone. London Hutchins an International Authors Limited. 1946.

Pankhurst, Richard. The History of Prostitution in Ethiopia. Journal of Ethiopian Studies VS. XII No. 2. Addis Ababa General Press. July 1974.

Rene wellek and Austin warren. Theory of Literature. London: Pelican Books. 1980.

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ማረጋገጫ

ይህ ቲሲስ የእኔ መሆኑን፣ በውስጡም የተገለገልኩባቸውን ማቴሪያሎች ምንጭ ሙሉ በሙሉ መጥቀሴን በፊርማዬ አረጋጋጣለሁ።

ስም	አያሌው አስፋው
ፊርማ	
የማስረከቢያ ሥፍራ	አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ
የማስረከቢያ ጊዜ	ሰኔ 1999 ዓ.ም